

# የነቢዩ

-በእሳቸው ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይሁን-

# ፈለጎችና እለታዊ አዝካሮች

አዘጋጅ
ዶ/ር ዐብዱላህ ቢን ሐሙድ
አል-ፉረይሕ

መቅድም
ፕሮፌሰር ኻሊድ ቢን ዐሊይ
አል-ሙሸይቂይሕ

# የነቢዩ

## -በእሳቸው ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይሁን-

# ፈለጎችና እለታዊ አዝካሮች

አላህ (ሱ.ወ) በሐዲሡ-ልቁድሲይ ላይ እንዲህ ይላል፤

‹‹እስከወደው ድረስ ባሪያዬ በውዴታ የሚተገበሩ በሆኑ
ሰላቶች ወደኔ ከመቅረብ አይታክትም፡፡››


አዘጋጅ

ዶ/ር ዐብዱላህ ቢን ሐሙድ አል-ፉረይሕ

መቅድም

ፕሮፌሰር ኻሊድ ቢን ዐሊይ አል-ሙሸይቂይሕ

ይህ መጽሐፍ ከአስር ቋንቋዎች በላይ ተተርጉሟል


ከአዘጋጁ ጋር ከተገናኙ በኋላ የዚህ መጽሐፍ የማሳተም መብት  ለጽድቅ ተግባር ለማዋል  ወይም ወደሌሎች ቋንቋዎች ለመተርጎም ለፈለጉ ሁሉ የተፈቀደ ነው

بسم الله الرحمن الرحيم

# የመጽሐፉ ርዕሶች ማውጫ


| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| የአዘጋጁ መቅድም | 21 |
| መግቢያ | 24 |
| የነቢያዊ ፈለግ ትርጓሜ | 24 |
| የቀደምት-ተምሳሌታዊ ትውልዶች ለነቢያዊ ፈለግ የነበራቸው ጉጉት ምሳሌዎች መካከል | 24 |
| ነቢያዊ ፈለግን በመከተል ካለው ትሩፋቶች መካከል | 26 |


## በጊዜ የተወሰኑ ነቢያዊ ፈለጎች




| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| አንደኛ፡- ከንጋት በፊት ያለው ወቅት | 30 |
| የመጀመሪያው ክፍል፡- | 30 |
| 1. አፋቸውን በመፋቂያ ይሟጩ ወይም ይፍቁ ነበር | 30 |
| 2. ከእንቅልፍ መንቃት በኋላ የሚባለውን ዚክር ይሉ ነበር | 31 |
| 3. እንቅልፋቸውን ከፊታቸው ላይ ያብሱ ነበር | 31 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ④ ወደሰማይ ይመለከቱ ነበር | 31 |
| ⑤ ከኣል-ዒምራን ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን አስር አንቀጾች ያነቡ ነበር | 31 |
| ⑥ እጆቻቸውን ሶሰት ሶስት ጊዜ ያጥቡ ነበር | 32 |
| ⑦ ውሃ ወደአፍንጫቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ይስቡና ውሃውን ከአፍንጫቸው ያስወጡ ነበር | 32 |
| ⑧ ከዚያ በኋላ ዉዱእ ያደርጉ ነበር | 32 |
| ከዉዱእ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል | 33 |
| ① መፋቂያ | 33 |
| ② የአላህን ስም ማውሳት | 34 |
| ③ መዳፎችን ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠብ | 34 |
| ④ እጆችንና እግሮችን ሲያጥቡ ቀኙን ማስቀደም | 34 |
| ⑤ በመጉመጥመጥና ውሃን ወደአፍንጫ ውስጥ በመሳብ መጀመር | 34 |
| ⑥ ጾመኛ ላልሆ ሰው በመጉመጥመጡና ውሃን ወደአፍንጫ በመሳቡ ሂደት ድንበር ማለፍ | 35 |
| ⑦ በአንድ መዳፍ እፍኝ ውሃ መጉመጥመጥና ውሃን ወደአፍንጫ ስበ ማውጣት | 35 |
| ⑧ የራስ ቅልን በማበስ ላይ ነቢያዊ ፈለግን መከተል | 35 |
| ⑨ የዉዱእ አካላትን ሶሰት ሶስት ጊዜ ማጠብ | 36 |
| ⑩ ከዉዱእ በኋላ የሚባሉ ዱዓዎችን ማለት | 36 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ◆ ሁለተኛው ክፍል፡- የሌሊትና የዊትር ሰላቶች፡፡ በውስጡ የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በርካታ ፈለጎችን አካቷል፡፡ | 38 |
| 1 የሌሊት ሰላትን በላጭ በሆነው ወቅት መስገድ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 38 |
| 2 አሰራ አንድ ረከዐዎች መስገድ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 40 |
| 3 የሌሊት ሰላቱን ቀለል ባሉ ረከዐዎች መ መር ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው | 41 |
| 4 ሐዲሥ ላይ በሰፈሩ ነቢዊ ፈለግ በሆኑ የሌሊት ሰላት መክፈቻዎች መጀመር ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 41 |
| 5 መቆሙ፣ ሩኩዑና ሱጁዱ የረዘመ መሆኑና ሁሉም የሰላት ተግባራዊ የሆኑ ምሰሶዎች ተቀራራቢ መሆናቸው ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ናቸው | 42 |
| 6 በሐዲሥ የተዘገቡ ነቢያዊ ፈለጎችን በቁርአን ንባቡ ውስጥ ማምጣት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 42 |
| 7 በየሁለቱ ረከዐዎች ሰላቱን በሰላምታ ማጠናቀቁ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 43 |
| 8 በሶስቱ የመጨረሻ ረከዐዎች ላይ የተወሰኑትን የቁርአን ምዕራፎች መቅራት (ማንበብ) ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው | 43 |
| 9 ግለሰቡ አንዳንድ ጊዜ በዊትር ሰላቱ ላይ ቁኑት ማድረጉ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 44 |
| 10 በመጨረሻው የሌሊቱ አንድ ሶሰተኛ ክፍል ዱዓእ ማድረግ | 45 |
| 11 የዊተር ሰላቱን በሰላምታ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ሶስት ጊዜ ‹‹ሱብሓነ መሊከ-ል-ቁዱስ›› /የተቀደሰው ንጉሥ በእሱ ላይ ከሚባለው ከንቱና ውድቅ የሆነ ነገር ሁሉ ጠራ፡፡/ ይልና ሶስተኛው ላይ ድምጹን ከፍ ያደርጋል | 46 |
| 12 ቤተሰቡን ለሌሊት ሰላት መቀስቀሱ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 46 |
| 13 ለሌሊት ሰላት የሚነሳ ሰው በሰላቱ ውስጥ ያለው ተመስጥኦ ላይ ተጽእኖ እንዳትፈጥር ለነፍሱ የሚራራ ሰው መሆን አለበት | 46 |
| 14 ሌሊት ላይ የሌሊት ሰላት ያመለጠው ሰው ቀን ላይ ይተካው ዘንድ ይሰግዳል | 47 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| ሁለተኛ፡- የፈጅር ወቅት | 48 |
| አዛን፤ በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ | 48 |
| 1 አዛንን መከታተል | 48 |
| 2 የሚከተለውን ዚክር ከሸሃደተይን በኋላ ማለት | 49 |
| 3 ከአዛን በኋላ በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ ሰላዋት ማድረግ | 49 |
| 4 ከአዛን በኋላ የሚባሉ ዱዓዎችን ማለት | 49 |
| 5 ከአዛን በኋላ ዱዓእ ማድረግ | 50 |
| የፈጅር ሰላት ነቢያዊ ፈለግ | 50 |
| 1 እነዚህ ነቢያዊ ፈለጎች ቤት ውስጥ መሰገዳቸው በላጭ ነው | 50 |
| 2 ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ጠበቅ ያለው ነቢያዊ ፈለግ | 51 |
| ወደመስጂድ መሄድ | 52 |
| 1 ወደመስጂድ በጊዜ መሄድ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 52 |
| 2 እርምጃዎቹ ይመዘገቡ ዘንድ ከቤቱ ወዱእ አድርጎ መውጣት አለበት | 53 |
| 3 ወደሰላት በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ መውጣት አለበት | 53 |
| 4 መስጂድ ውስጥ ሲገቡ ቀኙ እግርን ማስቀደም፣ ሲወጡ ደግሞ ግራ እግርን ማስቀደም | 53 |
| 5 መስጂድ ሲገባ ከመስጂድ ሲወጣ የሚባለውን ዘክር ማለት | 54 |
| 6 ሁለት ረከዐህ ተሒየቱ-ል-መስጂድ መስገድ | 54 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| 7 ለወንዶች በመጀመሪያው ሰልፍ ላይ መቻኮላቸው ነቢያዊ ፈለግ ነው | 54 |
| 8 ኢማሙን ተከትሎ ለሚሰገድ ሰው ለኢማሙ ቀረብ ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 55 |
| ሰላት በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች ያሉት ሲሆን ከእነርሱ መካከል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፡- | 56 |
| ግርዶሽ፡- በዚህ ሥር የሚከተሉት መፈጸም ነቢያዊ ፈለግ ነው | 56 |
| 1 ግርዶሽ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 56 |
| 2 ወደግርዶው መጠጋቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 57 |
| 3 ከሰጋጁ ፊት ለፊት የሚያልፍን ሰው መመለስ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 57 |
| 4 በእያንዳንዱ ሰላት መፋቂያ መጠቀም ነቢያዊ ፈለግ ነው | 58 |
| ለሰላት በሚቆምበት ጊዜ የሚከተሉትን መፈጸም ነቢያዊ ፈለግ ነው | 58 |
| 1 በተክቢረተ-ል-ኢሕራም ላይ እጆችን ከፍ ማድረግ | 58 |
| 2 እጆችን በሚያነሱበት ወቅት ጣቶችን ማራራቅ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 59 |
| 3 እጆችን ነቢያዊ ፈለግ በሆነበት ሥፍራ ላይ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 59 |
| 4 የሚሰግድ ሰው ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ ማድረጉ ነቢያ ፈለግ ነው | 60 |
| 5 በቀኝ እጁ የግራ እጁን አጥብቆ መያዝ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 60 |
| 6 የሰላት መክፈቻ ዱዓእ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 60 |
| 7 ከሸይጣን ተንኮልና ጉትጎታ በአላህ መጠበቅ | 61 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| 8 በአላህ ሥም መጀመር | 62 |
| 9 ከኢማም ጋር አሚን ማለት | 62 |
| 10 ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ በኋላ አንድ የቁርአን ምዕራፍ ማንበብ | 62 |
| ◆ በሩኩዕ ላይ የሚከተሉትን ነቢያዊ ፈለጎች መፈጸም | 63 |
| 1 በሁለቱ መዳፎች ጉልበትን በመያዝ፣ ጣቶችንም በማራራቅ ሁለቱን መዳፎች ጉልበት ላይ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 63 |
| 2 ሩኩዕ የሚያደርግ ሰው ወገቡን ቀጥ አድርጎ መዘርጋቱ ነቢያዊ ፈልግ ነው | 63 |
| 3 ሩኩዕ የሚያደርግ ሰው ረኩዕ ላይ ክርኖቹን ከጎኖቹ ማራራቁ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 64 |
| 4 ረኩዕ የሚደርገው ሰው በረኩዕ ላይ የሚባሉ ዚክሮችን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 64 |
| ◆ ከሩኩዕ መነሳት፤ በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ | 65 |
| 1 ይህን የሰላት ሩኩን (መሠረት፣ አምድ) ማስረዘም | 65 |
| 2 “ረብበና ወለከልሐምድ” የሚለውን አገላለጽ በሚከተለው አኳኋን መለያየት | 65 |
| 3 ከሩኩዕ ከተነሱ በኋላ የሚበሉ ነቢያዊ  ፈለጎችን ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 66 |
| ◆ ሱጁድ፡- በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ | 67 |
| 1 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው ክርኖቹን ከጎኖቹ እንዲሁም ሆዱን ከጭኖቹ ማራራቁ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 67 |
| 2 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው የእግሮቹን ጣቶች ወደቂብላህ አቅጣጫ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 67 |
| 3 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው ነቢያዊ ፈለግ የሆነ አዝካሮችን ሱጁድ ላይ ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 68 |
| 4 ሱጁድ ላይ ዱዓእ ማብዛት ነቢያ ፈለግ ነው | 69 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| ◆ በሁለት ሱጁዶች መካከል ባለው መቀመጥ ላይ ያሉ ነቢያዊ ፈለጎች | 70 |
| ① አንድ የሚሰግድ ሰው በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ለማረፍ ሲቀመጥ ግራ እግሩን በማንጠፍ በእሱ ላይ መቀመጡና የቀኝ እግሩን ደግሞ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 70 |
| ② ይህን የሰላት መሰረት ማርዘም | 70 |
| ③ ለሁለተኛ ወይም ለሶስተኛው ወይም ለአራተኛው ረከዐህ መነሳት የፈለገ ከመነሳቱ በፊት ቀለል ያለ መቀመጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 70 |
| ◆ ተሸሁድ ውስጥ ያሉ ነቢያዊ ፈለጎች | 71 |
| ① የሚሰግደው ሰው ተሸሁድ ላይ ግራ እግሩን ማንጠፉ፤ ቀኝ እግሩን ደግሞ ቀጥ አድርጎ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 71 |
| ② የሚሰግድ ሰው በተሸሁድ ላይ የእጆቹን የአቀማመጥ ሁኔታ መቀያየሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 71 |
| ③ ተሸሁድ ላይ የጣቶችን አቀማመጥ ሁኔታ ማለዋወጥ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 72 |
| ④ የሚሰግደው ሰው የተሸሁድ ዓይነቶችን መለዋወጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 72 |
| ⑤ ሶስት ወይም አራት ረከዐህ በሚሰገድባቸው ሰላቶች ውስጥ በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ የሚሰግደው ሰው በመቀመጫው ላይ መቀመጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 73 |
| ⑥ የሚሰግደው ሰው በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ ሰለዋት በሚያደርግበት ወቅት የሰለዋት ዓይነቱን መለዋወጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 74 |
| ⑦ የሚሰግደው ሰው ሰላቱን በሰላምታ ከማጠናቀቁ በፊት ከአራት ነገሮች በአላህ ጥበቃን መጠየቁ ነቢያዊ ፈለገ ነው | 75 |
| ◆ በሐዲሥ የተዘገቡ አዝካሮችን ግዴታ የሆኑ ሰላቶችን በሰላምታ ካጠናቀቁ በኋላ ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 77 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ◆ ከፈጅር ሰላት በኋላ ጸሐይ እስክትወጣ ድረስ በመስገጃው ላይ መቀመጥ | 79 |
| ▶ የጠዋት አዝካሮች፡- | 80 |
| ◆ የጠዋትና የማታ አዝካሮች | 81 |
| ◈ ሶስተኛ፡- የአድ-ዱሓ ሰላት ወቅት | 86 |
| ◆ ማስረጃው፡- | 86 |
| ◆ ወቅቱ | 87 |
| ◆ በላጩ ወቅት | 87 |
| ◆ የረከዐዎቹ ብዛት | 87 |
| ◈ አራተኛ፡- የዙህር ሰላት ወቅት | 89 |
| ◆ አንደኛው ከዙህር በፊትና በኋላ የሚሰገዱ ሱንናዎች | 89 |
| ◆ ሁለተኛ የዙህር ሰላት ላይ የመጀመሪያውን ረከዐህ መቆም ከሁለተኛው ረከዐህ መቆም ማስረዘም ከነቢ.ያዊ ፈለጎች መካከል ነው | 89 |
| ◆ ሶስተኛ በጣም ሞቃትማ በሚሆንበት ጊዜ ሙቀቱ ጋብ እስከሚል ድረስ ማዘግየት ነቢ.ያዊ ፈለግ ነው | 90 |
| ◈ አምስተኛ፡- የዐስር ሰላት ወቅት | 92 |
| ◆ የንጋትና የምሽት አዝካሮች | 93 |
| ◆ የንጋት አዝካር ወቅት | 93 |
| ◆ የምሽት አዝካር ወቅት | 93 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ስድስተኛ፡- የመግሪብ ሰላት ወቅት | 94 |
| የመጀመሪያው ነጥብ፡- በመግሪብ የመጀመሪያ ወቅት ላይ ሕጻናትን መሰብሰብ | 94 |
| ሁለተኛው ነጥብ፡- በመግሪብ የመጀመሪያው ወቅት ላይ በሮችን መዝጋትና -በእጅጉ የላቀውን- አላህን ማውሳት፡፡ | 94 |
| ሶስተኛው ነጥብ፡- ከመግሪብ ሰላት በፊት ሁለት ረከዐዎችን መስገድ | 95 |
| አራተኛው ነጥብ፡- ከዒሻእ ሰላት በፊት መተኛት ይጠላል | 96 |
| ሰባተኛ፡- የዒሻእ ሰላት ወቅት | 97 |
| አንደኛ ከዒሻእ ሰላት በኋላ ንግግርና ተሰብስቦ መቀመጥ ይጠላል | 97 |
| ሁለተኛ ተከትለው በሚስግዱ ሰዎች ላይ ምንም ችግር የማያስከትል እስከሆነ ድረስ በዒሻእ ሰላት ላይ በላጩ ሰላቱ መዘግየቱ ነው | 98 |
| የመኝታ ነቢያዊ ፈለጎች | 99 |
| 1 በመኝታ ወቅት በሮችን መዝጋት | 99 |
| 2 ከመተኛት በፊት እሳትን ማጥፋት | 99 |
| 3 ከመተኛት በፊት ዉዱእ ማድረግ | 100 |
| 4 የሚተኛበትን ፍራሽ ከመተኛቱ በፊት ማራገፍ | 100 |
| 5 በቀኝ ጎን መተኛት | 100 |
| 6 መዳፉን በቀኝ ጉንጩ ሥር ማስቀመጥ | 100 |
| 7 የመኝታ አዝካሮችን ማለት | 101 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ◆ ለመኻታ ከቁርኣንና ነቢያዊ ፈለግ የተወሰዱ አዝካሮች | 101 |
| ◆ የአል-ኢኽላስንና የአል-ሙዐውዊዘተይን በመዳፎች ላይ መቅራት፣ በመዳፎቹ ላይም እትፍ እትፍ ማለት ከዚያ ሶሰት ጊዜ በእነሱ (በመዳፎቹ) ሰውነትን ማበስ | 102 |
| ◆ ሌሊት ላይ ከእንቅልፉ የነቃ ሰው ይህን ዚክር ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 108 |

## በጊዜ ያልተገደቡ ነቢያዊ ፈለጎች





| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| አንደኛ፡- የአመጋገብ ሱንናዎች | 112 |
| 1 በምግቡ መጀመሪያ ላይ የአላህን ስም ማውሳት | 112 |
| 2 ከፊት ለፊት መመገብ | 113 |
| 3 የወደቀችውን ቁራሽ ማንሳትና በላዩዋ ላይ ያለውን ጎጂ ነገር ማስወገድና መመገብ | 113 |
| 4 ጣቶችን መላስ | 114 |
| 5 የመመገቢያ ትሪውን ማጽዳት | 114 |
| 6 በሶስት ጣቶች መመገብ | 115 |
| 7 ከእቃው ውጭ ሶስት ጊዜ መተንፈስ | 115 |
| 8 ከምግብ በኋላ -በእጅጉ የላቀውን- አላህን ማመስገን | 116 |
| 9 በምግብ ላይ መሰብሰብ | 116 |
| 10 አንድ ሰው ምግቡ ደስ ካለው ማወደስ | 117 |
| 11 ለምግቡ ባለቤት ዱዓእ ማድረግ | 117 |
| 12 የሚጠጣ ሰው ከግራው ይልቅ በቀኙ በኩል ያለውን ሰው ማጠጣቱ የተወደደ ተግባር ስለመሆኑ | 118 |
| 13 ሰዎችን የሚያጠጣ ሰው መጨረሻ ላይ የሚጠጣ ስለመሆኑ | 118 |
| 14 በሚመሽበት ወቅት እቃዎችን መክደንና የአላህ ስምን ማውሳት | 119 |

| ማውጫ | ርዕስ |
|---|---|
| ሁለተኛ፡- በሰላምታ፣ በመገናኘትና አብሮ በመቀመጥ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች | 120 |
| 1 ሰላምታ ማቅረብ ከነቢያዊ ፈለጎች ነው | 120 |
| 2 ችግር እስካስገደደ ድረስ ሰላምታን ሶስት ጊዜ መደጋገም | 121 |
| 3 በምታውቀውም ሆነ በማታውቀው ሰው ላይ ሰላምታን ማዳረስ | 122 |
| 4 ሰላምታን መጀመር ነቢያዊ ፈለግ የሚሆነው መጀመሩ በነቢያዊ ፈለግ ላይ በሰፈረው ሁኔታ ሲጀመር ነው | 122 |
| 5 ለሕጻናት ሰላምታ ማቅረብ ነቢያዊ ፈላግ ነው | 122 |
| 6 ወደቤት ሲገቡ ሰላምታ ማቅረብ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 123 |
| 7 ሰዎች ተኝተው ሳለ አንድ ሰው ወደሰዎች ሲገባና ሰላምታ ሲያቀርብ ድምጹን ዝግ ማድረጉ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡ ፡ | 124 |
| 8 ሰላምታን ማድረስ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 124 |
| 9 በአንድ ስብሰባ ሥፍራ ላይና በመለያየት ወቅት ሰላምታ ማቅረብ እንዲሁ ነቢያዊ ፈለግ የሆነ ተግባር ነው | 124 |
| 10 ሲገናኙ ከሰላምታ ጋር መጨባበጥ ነቢያዊ ፈከለግ ነው | 125 |
| 11 ሲገናኙ ፈገግ ማለትና መልካም ገጽታ ማሳየት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 125 |
| 12 መልካም ንግግር ሰደቃህ (ምጽዋት) በመሆኑ መተግበሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 125 |
| 13 በስብሰባ ሥፍራ -በእጅጉ የላቀውን- የአላህን ስም ማውሳት ስለመወደዱ | 126 |
| 14 ስብሰባን በስብሰባ ማካካሻ ማጠናቀቅ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 126 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| ሶስተኛ፡- በአለባበስና የመዋብ ያሉ ሱንናዎች | 127 |
| 1 ጫማ ሲጫሙ በቀኝ መጀመር ነቢያዊ ፈለግ ነው | 127 |
| 2 ነጫጭ የሆኑ ልብሶችን መልበስ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 128 |
| 3 ሽቶ መቀባት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 128 |
| 4 ሽቶን መመለስ ይጠላል | 129 |
| 5 ጸጉርን በሚያበጥሩበት ወቅት በቀኝ መጀመር ነቢያዊ ፈለግ ነው | 129 |
| አራተኛ፡- በማነጠስና በማፋሸግ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች | 130 |
| የማነጠስ ነቢያዊ ፈለጎች | 130 |
| 1 አንድ የሚያነጥስ ሰው ካስነጠሰው በኋላ “አልሐምዱሊላህ” ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 130 |
| 2 አንድ ሰው አነጥሶት አላህን ካላመሰገነ አላህ ይማርህ አለለት ነቢያዊ ፈለግ ነው | 131 |
| የማፈሽግ ነቢያዊ ፈለጎች | 132 |
| አምስተኛ፡- ሌሎች እለታዊ ሱንናዎች | 134 |
| ወደመጸዳጃ ቤት ሲገቡና ሲወጡ በሐዲሥ የተዘገቡ ዚክችን ማለት | 134 |
| ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣ ሰው የሚከተለውን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 135 |
| ኑዛዜን መጻፍ ነቢያዊ ፈለግ ነው | 135 |
| በግብይት ላይ ልስላሴንና መልካምነት መላበስ | 136 |

| ማውጫ | ርዕስ |
| --- | --- |
| ◆ ከእያንዳንዱ ዉዱእ በኋላ ሁለት ረከዐህ ሰላት መስገድ | 136 |
| ◆ ሰላትን መጠባበቅ | 137 |
| ◆ መፋቂያ | 137 |
| ◆ ለእያንዳንዱ ሰላት ዉዱእን ማደስ | 138 |
| ◆ ዱዓእ | 138 |
| ◆ በእጅጉ የላቀውን አላህ ማውሳት እለታዊ ከሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው | 143 |
| ◆ ዚክር በውሰጡ ለልቦና ሕይወት አለው | 143 |
| ◆ -በእጅጉ የላቀውና የተከበረው- አላህ እሱን በማውሳት ላይ በበርካታ ሥፍራዎች ላይ አደራ ብሏል | 144 |
| ◆ ዚክርን አስመልክቶ ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእ ሳቸው ላይ ይሁን- በሐዲሥ የተዘገቡ በርካታ ናቸው | 145 |



بسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله وحده والصلاة والسلام على من لا نبي بعده، وبعد:

فقد قرأت في هذا المؤلف للشيخ عبدالله بن حمود

الفريح (المنح العلية في بيان السنن اليومية)

فقد ألفيته مؤلفاً مفيداً حمل على استقصاء السنن

اليومية الفعلية والقولية في الليل والنهار، المنفردة

والتابعة لغيرها مما ثبت بالدليل جزاه الله خيراً،

ونفع بمؤلفه آمين، وبالله التوفيق.

كتبه

د/خالد بن علي المشيقح

٧/١١/١٤٣٤هـ

## መቅድም

### ዶ/ር ኻሊድ ቢን ዓሊ አል-ሙሸይቂሕ

ምስጋና ለአላህ ይሁን ከእሳቸው በኋላ ነቢይ በሌለባቸው ነቢይ ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን፡፡
በመቀጠል፤
በእርግጥ ሸይኽ ዐብዱላህ ቢን ሐሙድ አል-ረይሕ **‹‹አል-መንሑ-ል-ዐሊየህ ፊ በያን አስ-ሱነኑ-ል-የውሚይየህ››**
በሚል ርእስ ያዘጋጁትን መጽሐፍ በሚገባ አንብቤዋለሁ፡፡ በሌሊትና በቀን የሚተገበሩ ቃላዊና ተግባራዊ እለታዊ የነቢያዊ ፈለጎችንና ከሌሎች በማሰረጃ የተገኙትንም በማከል በልዩ ሁኔታ አሰናድተው ጽፍውታል፡፡
አላህ መልካም ምንዳ ይመንዳቸው፣ ባዘጋጁትም መጽሐፍ ሰዎች የሚጠቀሙበት ያድርግላቸው ኣሚን፡፡ ስኬትም በአላህ ነው፡፡

**ዶ/ር ኻሊድ ቢን ዓሊ አል-ሙሸይቂሕ**

በአል-ቀሲይም ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር፣ በመካና መዲና
መስጂዶች ውስጥ የዲን መምህር


ادخلوها بسلام آمنين
KING FAHD GATE
TO ROOF

# የአዘጋጁ መቅድም

***‹‹ለእናንተ÷ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለኾነ ሰው ÷ አላህንም በብዙ ለሚያወሳ ÷በአላህ መልክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፤››*** (አል-አሕዛብ) በማለት ለተናገረው አላህ ምስጋና ይሁን፡፡ ከመልክተኞቹ ሁሉ መልካም የሆኑትን መልክተኛ ለላከልን፣ የላቀ መጽሐፉን ላወረደልን፣ መለኮታዊ ርእዮቹን ይሸከሙ ዘንድ ከመልከተኛው ባልደረቦችና እነሱን በመልካም ሁኔታ ከተከተሏቸውና መለኮታዊ ርእዮቹን በቃላቸው ካደረሱት ከነዚያ ቀደምት መልካም ትውልዶች ከነዚያ ታሪክ ተግባሮቻቸውን በድርሳኑ ውስጥ ከከተበላቸውና ለተሸከሙት መልካም ነገር መልካም ተሸካሚ የሆኑትን፣ ነቢያቸውን (የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን) ውዴታ በመግለጽ አንጸባራቂ ተምሳሌት የተዘገበላቸውን ሰዎች ላዘጋጀው አላህ ምስጋና ይገባው፡፡

አንባቢያን ሆይ! ከእንቅልፋቸው ከነቁበት እስከሚተኙበት ጊዜ ድረስ ያሉትን የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ነቢያዊ ፈለጎችን በጊዜ የተወሰኑትን በቅድም ተከትል ከዚያ በኋላ በጊዜ ያልተወሰኑትን ነቢያዊነ ፈለጎችን በማሰሰት የተወሰኑትን አስቀምጫለሁ፡ **፡ ተወዳጅ የሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች ስል ድንጋጌውን ያሰፈረው አላህ በግዴታነት ያላስቀመጣቸውን በተቃራኒው በማሚያነትና ታዛዥነትን ለመጨመር ለማስቻል የሚረዱ ብሎ ያስቀመጣቸውን ተግባራት ለማለት ፈልጌ ነው፡፡** ይህ መጽሐፍ **‹‹አል-ሚነሑ-ልዐሊይየህ ፊ በያኒ ሱነኒ-ልየውሚይየህ››** ከሚለው መጽሐፍ ላይ የተወሰኑ ጥያቄዎችንና ፋይዳዎችን በማውጣት በማሳጠር ያቀረብኩት መጽሐፍ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ላይ ለነቢያዊ ፈለጎቹ ማስረጃዎቹን ብቻ አስፈሬያለሁ፡፡ ይህም ለአንባቢያን ንብባ ይቀል ዘንድና በሕትመት ረገድም ለበርካታ ሰዎችና የዳዕዋ ተቋማት እንዲዳረስ በማሰብ ነው፡፡ ነቢያዊ ፈለጎች ላይ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ምዕራባዊያን ያጠለሹትን የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስተምህሮዎች ይፋ ለማውጣት ካለኝ ፍላጎት በመነሳት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነቢያዊ ፈለጎችን (ሱንናዎችን) ባለመፈጸም ምንም ቅጣት አያስከትልም በሚል እሳቤ ከነቢያዊ ፈለጎች

(ሱንዎች) እየራቁና እየተዘናጉ ያሉ ሰዎችን የያዙትን አቋም እንዲተዉና በዚህ እሳቤ እያጡ ያሉትን ታላላቅ ምንዳዎችን እንዲያገኙ በማሰብም ነው፡፡ በዚህ መሰረት ትክክለኛና እለታዊ በሆኑት ነቢያዊ ፈለጎች ላይ ብቻ ከማስረጃዎቻቸው ጋር በማቅረብ ላይ ትኩረት አድርጌያለሁ፡፡ እኔና እናንተን ነቢያዊ ፈለግ ከሚከተሉት፣ ውስጡ በሰፈሩት ንግግሮቻቸው፣ ተግባሮቻቸውና በሁሉም ሁኔታዎቻቸው ላይ የምንጸና ያደርገን ዘንድ -ልእልና- የተገባውን- አላህን በመልካም ስሞቹና በላቁ መገለጫዎቹ እጠይቀዋለሁ፡፡

ይህን መጽሐፍ የጌታውን የአላህን ምሕረት በጽኑ ፈላጊ
የሆነው

**ዶ/ር ዐብዱላህ ቢን ሐሙድ አል-ፉረይሕ**

በኢ-ሜይል በኩል ለማግኘት

eqtidaa@gmail.com

## መግቢያ



### የነቢያዊ ፈለግ ትርጓሜ

ነቢያዊ ፈለግ በቃሉ ቀጥተኛ ትርጉም ረገድ በጣም የተወደደና የተፈቀደ ተግባር ማለት ነው፡፡

በቃሉ አገባባዊ  ትርጉም ረገድ ደግሞ ኢስላም በግዴታነት ያለስቀመጠው ተግባራዊ ድንጋጌ ነው፡፡ አዎንታዊ ተጽእኖው የተገበረው ሰው መልካም ምንዳ ሲያገኝ የተወው ሰው ደግሞ አይቀጣም፡፡

### የቀደምት-ተምሳሌታዊ ትውልዶች ለነቢያዊ ፈለግ የነበራቸው ጉጉት ምሳሌዎች መካከል፡-

1 ሙስሊም ትክክለኛ በሆነው የሐዲሥ ዘገባቸው ከአን-ኑዕማን ቢን ሳሊም እንደዘገቡት ዐምር ቢን አውስ -አላህ የሁለታቸውንም መልካም *ሥራዎች* ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፡ «ዐንበሳህ ቢን አቢ ሱፍያን እንዲህ አሉኝ፡ "ኡምሙ ሐቢበህ እንዲህ ሲሉ ሰምቻሉ፡-- የአላህ መልእክተኛ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን- እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፤ ***‹‹በቀንና በማታ አስራ ሁለት ረከዐዎችን የሰገደ፤ በእነርሱ ሰበብ ጀነት ውስጥ ቤት ይገነባለታል፡ ፡››*** ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (1727) ዘግበውታል፡፡ ኡምሙ ሐቢባህ እንዲህ ብለዋል፤ «ይህን ከአላህ መልእክተኛ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን- ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ ፈጽሞ አልተውኳቸውም፡፡» ዐንበሳህም እንዲህ ብለዋል፤ «ከኡምሙ ሐቢባህ ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ ፈጽሞ አልተውኳቸውም፡፡»

ዐምር ቢን አውስ ደግሞ እንዲህ ብለዋል፤ «ከዐንበሳህ ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ ፈጽሞ አልተውኳቸውም፡፡»

አን-ኑዕማን ቢን ሳሊም ደግሞ እንዲህ ብለዋል፤ «ከዐምር ቢን አውስ ሰማሁበት ጊዜ አንስቶ ፈጽሞ አልተውኳቸውም፡፡»

2 ከዐሊይ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- እንደዘገበው፤ «ከእለታት አንድ ቀን ፈጢማህ መጅ በእጇ ላይ የሚያስከትለውን ችግር አስመልክታ ቅሬታ አቀረበች፡፡ ወደነቢዩ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን- ዘንድ የጦር ምርኮኞች መጡ፡፡ እሷ ወደእሳቸው ዘንድ ሄደች፡፡ አላገኘቻቸውም፡፡ ዓኢሻህን አገኘቻትና ቅሬታውን ነገረቻት፡፡ ነቢዩ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን- ወደቤታቸው ሲመጡ ፈጢማህ ወደእሷ ዘንድ እንደመጣች ዓኢሻ ነገረቻቸው፡፡ እሳቸወም ወደኛ ዘንድ መጡ፡፡ በእርግጥ ለመተኛት መኝታችንን ይዘናል፡፡ ካለንበት ልንነሳ ስንል፣ ነቢዩ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላም ይሁን- «በቦታችሁ ላይ ሁኑ» አሉን፡፡ የእግራቸውን ቅዝቃዜ ደረቴ ላይ እስካዳምጥ ድረስ መጥተው በመካከላችን ተቀመጡና፤ ***‹‹ከጠየቃችሁት ነገር የተሸለን ነገር ላስተምራችሁን? ለመተኛት መኝታችሁን ስትይዙ ሰላሳ አራት ጊዜ ተክቢራ ታደርጋላችሁ፡፡ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ተስቢሕ ታደርጋላችሁ፡፡ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አል-ሐምዱሊላህ ትላላችሁ፡፡ ይህ ለናንተ ካገልጋይ የተሻለ ነው፡፡››*** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ቀጥር (3705) ሙስሊም ደግሞ በሐዲሥ ቁጥር (2727) ዘግበውታል፡፡

በሌላ ዘገባ ዐሊይ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ፤ «ይህን ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከሰማሁ አንስቶ አልተውኩትም፡፡» አሉ፡፡ «የሲፍፊይ ሌሊት ላይም ቢሆን እንኳ?» ተባሉ፡፡ እቸውም፤«የሲፍፊይ ሌሊት ላይም ቢሆን እንኳ» አሉ፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5362) ሙስሊም ደግሞ በሐዲሥ ቁጥር ዘገባ (2727) ዘግበውታል፡፡

እንደሚታወቀው የሲፍፊይን ሌሊት ጦርነት የተካሄደበት ሌሊት ነበር፡፡ በዚህ ጦርነት ላይም ዐሊይ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ጦር መሪ ነበሩ፡፡ ይሁን ቢሆን ከዚህ ዓይነቱ ነቢያዊ ፈለግ ጦርነቱ እንዲዘናጉ አላደረጋቸውም፡፡

3 ኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- አስክሬን ላይ ይሰግዱ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ ነቢያዊ ፈለጉን ማሟያ ነው ብለው ስለሚጠረጥሩ ነበር፡፡ ይህን የሚያደርጉት አስክሬንን እስከሚቀበር ድረስ የመሸኘትን ትሩፋት አስመልከቶ የተነገረውን የነቢያዊ አስተምህሮ ፈጽሞ ስለማያውቁ ነበር፡፡ ይህን አስመልከቶ በአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የተላለፈው ነቢያዊ አስትምህሮ ሲደርሳቸው ነቢያዊ ፈለጉን በመተዋቸው በጣም ተጸጸቱ፡፡ ታዲያማ ምን እንዳሉ ታውቃላችሁ? እስኪ አስተውሉ፡፡

በእፍኛቸው ይዘዋቸው በነበረው ጠጠሮች መሬቱን መቱና፣ «በርግጥ በበርካታ ድልቦች ላይ ተዘናግተናል፡፡» አሉ፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1324) እንዲሁም ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (945) ላይ ዘግበውታል፡፡

ኢማም አን-ነወዊይ -አላህ ይዘንላቸው-፤ «ሰሓቦች ትእዛዛት ሲደርሷቸው ለመተግበር ምን ያህል ፍላጎት እንደነበራቸውና ከተእዛዛቱ አንዱ ሲያመልጣቸው ምን ያህል እንደሚያዝኑ እንዲሁም ሁኔታውን አለማወቃቸውን ሲረዱ ሁኔታቸው ምን ያህል እንደሚገዝፍ በዚህ ክስተት ውስጥ እንረዳለን፡፡» ብለዋል፡፡

## ነቢያዊ ፈለግን በመከተል ካለው ትሩፋቶች መካከል፡-

### ውድ አንባቢያን ሆይ! ነቢያዊ ፈለግን መከተል በርካታ ትሩፋቶች አለው፡፡ ከእርሱም መካከል፡-

1 የውዴታን ደረጃ ያቀዳጃል፡፡ ግዴታ ባልሆኑ ተግባራት እጅጉን ወደላቀውና ልእልና ወደተገባው አላህ ዘንድ መቃረብ እጅግ የላቀውና ልእልና የተገባው አላህ ለባሪያው የሚሰጠውን ውዴታ ያስገኛል፡፡

ኢብን አል-ቀይዩም -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ « በይፋም ሆነ በድብቅ በእሱ ዘንድ ተወዳጅ የሆኑትን ነቢይ እስካልተከተልክ፣ መልእክታቸውን እውነት እስካላላልክ፣ ጥሪያቸውንና ፈለጋቸውን እስካልተከተልክ፣ በፍርዳቸው የሌሎችን ፍርዶች፣ በውዴታቸው የሌሎች ፍጡራንን ውዴታ እንዲሁም ትእዛዞቻቸውን በመታዘዝ ለሌሎች ያለህን መታዘዝ እንካላጠፋህ ድረስ አላህ አይወድህም፡፡ ይህ ካልሆነ በከንቱ አትድከም፡፡ ወዳሻህ ስፍራም ተመለስ፡፡ በአንዳች ነገር ላይ ስላልሆንክ ብርሃንን ፈልግ፡፡» መዳሪጁ-ስሳሊከይን ቅጽ፡ 3 ገጽ ፡ 37ን ይመልከቱ፡፡

2 የላቀው አላህ ለባሪያው የሚሰጠውን እገዛ ያቀዳጃል፡፡ ነቢያዊ ፈለጎችን የሚከተልን ሰው አላህ መልካም ነገሮች ይገጥመዋል፡፡ ጌታው ከሚውደው ነገር ውጭ ከንቱና ውድቅ የሆኑ ተግባራት ከእሱ ዘንድ አይፈልቁም፡፡ ምክንያቱም ይህ ዓይቱ ሰው የአላህን ውዴታ በርግት ካገኘ የአላህን እርዳታንም እንዲሁ አግኝቷል፡፡

3 ተወዳጅነትን የተቀዳጀ ሰው የሚያደርገው ዱዓእ ተቀባይነት ያለው ለመሆኑ ዋስትና አለው፡፡ ግዴታ ባልሆኑ ተግባራት ወደላቀውና ልእልና ወደተገባው አላህ ዘንድ የተቃርበ የአላህን ውዴታ ያገኛል፡፡ የአላህን ውዴታ ያገኘ ሰው ደግሞ የዱዓውን ተቀባይነት ያገኛል፡፡

### እነዚህን ትሩፋቶች ሶስት ሐዲሦች ያረጋግጣሉ፡-

አቡ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸወን ይቀበላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ - የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፤ ‹‹***በርግጥ አላህ እንዲህ ብሏል፣- “ለእኔ ባላንጣ ያደረገን ሰው በርግጥ በጦርነት እጋፈጠዋለሁ፡፡ ባሪያዬ እኔ ግዴታ ካደረግኩበት ነገር ውጭ በእኔ ዘንድ ተወዳጅ በሆነ ነገር አይቃረብም፡፡ ባሪያዬ እከምወደው ድረስ ግዴታ ባልሆኑ ተግባራት ወደኔ ከመቃረብ አይታክትም፡፡ ከወደድኩት የሚሰማበትን መስሚያ ጆሮ፣ የሚያይበትን ዓይን፣ የሚዳስስበትን እጅ፣ የሚራመድበትን እግር እሆንለታለሁ፡፡ ከጠየቀኝ በርግጥ እሰጠዋለሁ፡፡ ጥበቃ ከጠየቀኝም በርግጥ እጠብቀዋለሁ፡፡ እኔ ክፉውን ነገር እንደምጠላለትና ሞትን ከሚጠላው የሙእሚን ነፍስ ይበልጥ ከምፈጽመው አንዳች ነገር ወደኋላ አልልምም፡፡”***›› ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6502) ላይ ሐዲሡን ዘግበውታል፡፡

4 ግዴታ የሆኑ ተግባራት ሲጓደሉና ያልተሟሉ ሲሆኑ ግዴታ ያልሆኑ ተግባራት እነዚህን ያልተሟሉ ግዴታ የሆኑ ተግባራትን ይሞላሉ፡፡

### ይህንንም የሚያረጋግጥልን ማረስጃ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ማለታቸውን ሰምቻለሁ ብለዋል፣«በትንሳኤ እለት አንድ የአላህ ባሪያ ከሥራዎቹ መካከል በቅድሚያ የሚተሳሰብበት ነገር ሰግዴቱ ነው፡፡ ስግደቱ ከተስተካከለች በርግጥ ነጻ ወጥቷል፡፡ ድልም ተቀዳጅቷል፡፡ ስግደቱ ከተበላሸችበት በርግጥ ከንቱ ሆነ ከሰረም፡፡ ግዴታ ከሆነበት ተግባሩ አንዳች ነገር ከጎደለ እጅግ የላቀውና ልእልና የተገባው አላህ ፤ “ባሪያዬ በፈቀደኝነት የፈጸመው ተግባር አለን? እስኪ ተመልከቱ፡፡” ይላል፡፡ በፈቀደኝነት በሰራው ሥራ የጎደለው ይሟላለታል፡፡ ከዚያ ቀሪዎቹ ሥራዎቹ በዚያ ሁኔታ ላይ ይሆናሉ፡፡» አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (864) እንዲሁም አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (413) ሐዲሡን የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒ በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ ድርሳናቸው ላይ ትክክለኛነቱን አጽድቀዋል፡፡ (ሰሒሑ-ል-ጃሚዕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 405)





# በጊዜ የተወሰኑ ነቢያዊ ፈለጎች

በጊዜያት የተወሰኑ ነቢያዊ ፈለጎች ስንል በቀንና በሌሊት ውስጥ ውስን በሆኑ ጊዜያት የተወሰኑ የሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ አነዚህን ነቢያዊ ፈለጎች ለሰባት ወቅቶች ከፋፍያቸዋለሁ፡፡ እነርሱም፡- ከንጋት በፊት፣ የንጋት ወቅት፣ የጎሕ መውጣት ወቅት፣የአዝ-ዙህር ወቅት፣ የአል-ዐስር ወቅት፣ የመግሪብ ወቅትና የአል-ዒሻእ ወቅት ናቸው፡፡

## አንደኛ፡- ከንጋት በፊት ያለው ወቅት



ይህ ወቅት ከእንቅልፍ ሲነቁ የመጀመሪያው ወቅት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ ወቅት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይተገብሯቸው የነበሩ በርካታ ተግባራትን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ተዘግበዋል፡፡ በዚህ ወቅት የሚተገበሩ ነቢያዊ ፈለጎችን ለሁለት ክፍሎች መከፈል ይቻላል፡፡

### የመጀመሪያው ክፍል፡-

ከእንቅልፍ መንቃትና ይህን አስከትለው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይተግብሯቸው የነበሩ ተግባራት፡-



### 1 አፋቸውን በመፋቂያ ይሚጩ ወይም ይፍቁ ነበር፡፡

ከሑዘይፋህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተወራው «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሌሊት ላይ ከእንቅልፍ ሲነቁ አፋቸውን በመፋቂያ ይሚጩ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ገባ ቁጥር (245)፣ ሙስሊም

ደግሞ በቁጥር (255) ሐዲሡን ዘግበውታል፡፡ በሌላ የሙስሊም ዘገባ፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሌሊት ላይ ለመስገድ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ አፋቸውን በመፋቂያ ይሟጩ ነበር፡፡» የሚል ተዘግቧል፡፡ ይህን ሐዲሥ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (255) ላይ ዘግበውታል፡፡ መሟጨት ማለት ጥርስን በመፋቂያ በአግድሞሽ መፋቅ ማለት ነው፡፡

## 2 ከእንቅልፍ መንቃት በኋላ የሚባለውን ዚክር ይሉ ነበር፡፡

بِاسْمِكَ اللَّهُمَّ أَمُوتُ وَ أَحْيَا

الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَحْيَانَا بَعْدَ مَا أَمَاتَنَا وَإِلَيْهِ النُّشُورُ

ይህ ቡኻሪ ከሑዘይፋህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ላይ ሑዘይፋህ፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንቅልፍ ለመተኛት ሲፈልጉ ፣ ***‹‹አላህ ሆይ! በስምህ ሕያው እሆናለሁ፣ በስምህም እሞታለሁ፡፡›› ይሉ ነበር፡፡ ከእንቅልፍ ሲነቁ ደግሞ፣ ‹‹ለዚያ ከገደለን በኋላ ሕያው ላደረገን አላህ ምስጋና ይገባው፡፡ ከሞት በኋላ መቀስቀስም ወደርሱ ነው፡፡››*** ይሉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6324) ሲገቡ ሙስሊም ደግሞ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2711) ከአል-በራእ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

## 3 እንቅልፋቸውን ከፊታቸው ላይ ያብሱ ነበር፡፡

## 4 ወደሰማይ ይመለከቱ ነበር፡፡

## 5 ከአል-ዒምራን ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን አስር አንቀጾች ያነቡ ነበር፡፡

እነዚህ ሶስት ነቢያዊ ፈለጎች ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ተዘግቧል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ይሁን- ለኢብን ዐብባስ አክስታቸው ከሆኑትና ለነቢዩ ሚስት ከሆኑት ዘንድ አደሩ፡፡ እኔ በትራሱ አግድሞሽ ስተኛ፣ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ይሁን- እና ባለቤታቸው በትራሱ ቁመት ላይ ተኙ፡፡ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ይሁን- ሌሊቱ እስከተጋመሰ ወይም ለመጋመስ ትንሽ እስከሲቀረው ወይም ትንሽ እሰኪጋመስ ድረስ ተኙ፡፡ ከዚያም የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ይሁን- ከእንቅልፋቸው ነቁና ተቀምጠው በእጆቻቸው ፊታቸው ላይ ያለውን እንቅልፍ ያብሱ ጀመር፡፡ ከዚያ ከአል-ዒምራን ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን አስር አንቀጾች አነበቡ፡፡ ከዚያም ተሰቅሎ ወደነበረው የውሃ እቃ ሄደው ከእሷ ዉዱእ አደረጉ፡፡ ዉዱኣቸውንም አሳመሩ፡፡ ከዚያ ተነስተው ይሰግዱ ጀመር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (183) ሲዘግቡ ሙስሊም ደግሞ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (763) ዘግበውታል፡፡

ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (256) በዘገቡት ሌላ ዘገባ፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የሌሊት የመጨረሻ ክፍል ላይ ከእንቅልፋቸው ነቁና ወደውጭ ወጡ፡፡ ከዚያም ሰማይን ተመለከቱ፡፡ ከዚያ ኣል-ዒምራን ምዕራፍ ውስጥ የሚገኘውን ይህን አንቀጽ አነበቡ፡፡ ***((ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር÷ ሌሊትንና ቀንም በመተካካት÷ ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አልሉ፡፡...))*** (ኣል-ዒምራን ፡ 190) የሚል ተዘግቧል፡፡

-እንቅልፋቸውን ከፊታቸው ላይ ይዳብሱ ነበር ማለት የእንቅልፍ ምልክትን ዓይናቸውን በማሸት ያስወግዱ ነበር ማለት ነው፡፡

በሌላ የሙስሊም ዘገባ ይህን ነቢያዊ ፈለግ ተግባራዊ ማድረግ ለሚፈልግ ሰው የሚያነበው የቁርኣን አንቀጽ በግልጽ ሰፍሯል፡፡ ይኸውም ሰውየው ሲያነብ((ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር፥ ሌሊትንና ቀንም በመተካካት፥ ለባለ አእምሮዎች በእርግጥ ምልክቶች አልሉ፡፡...)) ከሚለው አንቀጽ ጀምሮ እስከ የኣል-ዒምራን ምዕራፍ መጨረሻ ድረስ ያነባል፡፡

### 6 እጆቻቸውን ሶስት ሶስት ጊዜ ያጥቡ ነበር፡፡

ይህ ነቢያዊ ፈለግ አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***‹‹አንዳችሁ ከእንቅልፉ ሲነቃ እጆቹን ሳያጥባቸው በፊት እቃ ውስጥ አያስገባ፡፡ በርግጥ እጆቹ የት እንዳደሩ አያውቅምና ነው፡፡››*** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (182) ላይ ሲዘግቡ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (278) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 7 ውሃ ወደአፍንጫቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ይስቡና ውሃውን ከአፍንጫቸው ያስወጡ ነበር፡፡

ይህ ነቢያዊ ፈለግ አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***‹‹አንዳችሁ ከእንቅልፉ ሲነቃ ሶስት ጊዜ ውሃ በአፍንጫው ውሃ በመሳብ ያስወጣ፡፡ በርግጥ ሸይጣን በላንቃው ውስጥ ያድራልና፡፡››*** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3295) ላይ ሲዘግቡ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (238) ላይ ዘግበውታል፡፡ በቡኻሪ ሌላ ዘገባ፣ ***‹‹አንዳችሁ ከሕልሙ ሲነቃ ዉዱእ ያድርግ፣ሶስት ጊዜ ውሃ በአፍንጫው ውሃ በመሳብ ያስወጣ፡፡...››*** የሚል በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3295) ላይ ተዘግቧል፡፡

### 8 ከዚያ በኋላ ዉዱእ ያደርጉ ነበር፡፡


ይህ ነቢያዊ ፈለግ ከዚህ በላይ ባሳለፍነው «ወደተንጠለጠለች የውሃ እቃ ሄደው ከእሷ ዉዱእ አደረጉ፡፡» በሚለው የኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ሐዲሥ ተዘግቧል፡፡

## ከዉዱእ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል፡-



ዉዱእን አስመልክቶ ላፍታ ቆም እንበልና ሳናሰፋ አጠር ባለ መልኩ የዉዱእ ነቢያዊ ፈለጎችን እናብራራ፡፡ ምክንያቱም የዉዱእ ነቢያዊ ፈለጎች የሚታወቁ ናቸውና ነው፡፡ እዚህ ላይ የምንጠቅሳቸው ነቢያዊ ፈለጎችን እናሟላ ዘንድ ነው፡፡

### 1 መፋቂያ



ከዉዱእ ወይም ከመጉመጥመጥ በፊት መፋቅ፡፡ ይህ ነቢያዊ ፈለግን የተከተለ ጥርስን የመፋቂያ ወቅት ነው፡፡ -ይህን ርዕስ ከዚህ በላይ አሳልፈንዋል-፡፡ ዉዱእ ማድረግ የፈለገ ሰው ጥርሱን መፋቅ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህም ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተላለፈው ሐዲሥ ነቢ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ‹‹በሕዝቦቼ ላይ ባላስቸግር ኖሮ ከሁሉም ዉዱእ ጋር መፋቂያን ባዘዝኳቸው ነበር፡፡›› ብለዋል፡፡ ኢብን ኹዘይማህ በሐዲሥ ዘገባ መድብላቸው (ቅጽ፡ 1፣ ሐዲሥ ቁጥር፡ 73፣ ገጽ፡140)፣ አል-ሓኪም በሐዲሥ ዘገባ መድብላቸው ( ቅጽ፡ 1 ገጽ፡ 245) ላይ ዘግበውታል፡፡ ቡኻ ‹‹እርጥብና ደረቅ መፋቂያ›› በሚል ርእስ በሐዲሡ ላይ አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፣ ***‹‹መፋቂያቸውንና ዉዱእ የሚያደርጉበትን ውሃ እናዘጋጅላቸው ነበር፡፡ አላህ ሊያነቃቸው የሻው ሌሊት ላይ ያነቃቸዋል፡፡ ጥርሳቸውን ይፍቃሉ፣ ዉዱእ ያደርጋሉ፣ ይሰግዳሉም፡፡…››*** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (746) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 2 የአላህን ስም ማውሳት

ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***‹‹የአላህን ስም ላላወሳ ዉዱእ የለም፡፡››*** ብለዋል፡፡ አሕመድ አቡ ዳዉድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (11371)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (101) እንዲሁም ኢብን ማጀህ በቁጥር (397) ዘግበውታል፡፡

## 3 መዳፎችን ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠብ



የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የዉዱእ አደራረግ አስመልከቶ ከዑሥማን ኢብን ዐፍፋን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው፣ ዑሥማን ዉዱእ የሚያደርጉበት ውሃ እንዲመጣላቸው አደረጉ፡፡ ዉዱእ አደረጉ፡፡ መዳፎቻቸውንም ሶሰት ሶስት ጊዜ አጠቡ…፡፡ ከዚያም፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይህን ዉዱዬን በመሰለ ሁኔታ ዉዱእ ሲያደርጉ ተመልክቻለሁ፡፡» አሉ፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (164)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (226) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 4 እጆችንና እግሮችን ሲያጥቡ ቀኝን ማስቀደም፡፡



ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሚጫሙበት፣ ጸጉራቸውን በሚያበጠሩበት፣ በዉዱአቸውና በሁሉም ሁኔታቸው ቀኝን ማስቀደም ይወዱ ነበር፡፡»ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (168)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (268) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 5 በመጉመጥመጥና ውሃን ወደአፍንጫ ውስጥ በመሳብ መጀመር፡፡

ከዑሥማን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው ‹የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የዉዱእ አደራረግ ሲገልጹ፣ «…ተጉመጠመጡ ከዚያ ውሃ ወደአፍንጫቸው ስበው አስወጡ ከዚያም ፊታቸውን ሶሰት ሶስት ጊዜ አጠቡ፡፡…» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (199) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (226) ዘግበውታል፡፡ ዉዱእ የሚያደርገው ሰው ፊቱን ከታጠበ በኋላ መጉመጥመጡንና ውሃ ወደአፍንጫው ስቦ ማስወጣቱን ቢያዘገይም ይፈቀዳል፡፡



### 6 ጾመኛ ላልሆነ ሰው በመጉመጥመጡና ውሃን ወደአፍንጫ በመሳቡ ሂደት ድንበር ማለፍ፡፡

ከለቂጥ ኢብን ሰቡረህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ አሏቸው፣ ***‹‹ዉዱእን አሟላ፤ በጣቶች መካከል ፈልፍል፣ ጾመኛ ካልሆንክ በስተቀር ውሃን ወደአፍንጫ በማስገባቱ ድንበር እለፍ፡፡››*** አሕመድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (17846)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (142) ዘግበውታል፡፡ ኢብን ሐጀር፣ «ይህ ሐዲሥ ትክክል ነው፡፡» ብለዋል፡፡ አል-ኢሳበህ (ቅጽ፡ 9 ገጽ፡ 15)፡፡ በመጉመጥመጥ ላይ ድንበር ማለፍ የተወሰደው ***‹‹ወዱእን አሟላ፡፡››*** ከሚለው ቃል ነው፡፡



### 7 በአንድ መዳፍ እፍኝ ውሃ መጉመጥመጥና ውሃን ወደአፍንጫ ስቦ ማውጣት፡፡

ዐብዱላህ ኢብን ዘይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዉዱእ አደራረግ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፣ «እጃቸው የውሃ እቃው ውስጥ አስገቡ በአንድ እፍኝ ውሃም ተጉመጠመጡ፣ ውሃ ወደአፍንጫቸው ስበው አስወጡ፡፡ ይህንንም ሶስት ጊዜ ፈጸሙ፡፡» ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (192) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (235) ላይ ዘግበውታል፡፡



### 8 የራስ ቅልን በማበስ ላይ ነቢያዊ ፈለግን መከተል ተገቢ ነው፡፡

ግለሰቡ የራስ ቅሉን በሚያብስበት ወቅት እጆችን በራሱ ቅሉ ፊት ለፊት ላይ ያስቀምጣል፡፡ ከዚይም ከፊት ለፊት ጀምሮ ወደአናቱ ያብሳል፡፡ ከዚያው ወደተበሳበት ስፍራ ይመልሳቸዋል፡፡ ሴትም እንዲሁ ይህኑ ነቢያዊ ፈለግ በዚሁ ዓይነት ትፈጽማለች፡፡ ከአንገት በታች የወረደው የሴት ጸጉር አይታበስም፡፡

**ይህን የሚያመለክተው ማስረጃ፡-**

ዐብዱላህ ኢብን ዘይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዉዱእ አደራረግ ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፣ «... ከራስ ቅላቸው መጀመሪያ ጀመሩ ከዚያ ወደአናታቸው ደርሰው ወደጀመሩበት እስኪመለሱ በእጆቻቸው አበሱ፡፡» ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (185) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (235) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 9 የዉዱእ አካላትን ሶስት ሶስት ጊዜ ማጠብ

የመጀመሪያው እጥበት ግዴታ ሲሆን ሁለተኛውና ሶስተኛው ደግሞ ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ ከሶስት በላይ አይጨመርም፡፡

**ይህን የሚያመለክተው ማስረጃ፡-**

በቡኻሪ በተዘገበውና ከኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አንድ ጊዜ ወዱእ አደረጉ፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (157) ሲዘግቡ ከዐብዱላህ ኢብን ዘይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ደግሞ፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሁለት ሁለት ጊዜ ወዱእ አደረጉ፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (159) ዘግበውታል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ከዑሥማን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሶስት ሶስት ጊዜ ዉዱእ አድርገዋል፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (159) ላይ ዘግበውታል፡፡ ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ መቀያየሩ ይበልጥ ተመራጭ ነው፡፡ ይኸውም እንዳንድ ጊዜ አንድ ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ሁለት ጊዜ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሶስት ሶስት ጊዜ ይትቡ ነበር፡፡ ልክ በዐብዱላህ ኢብን ዘይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተላለፈው ሐዲሥ መሰረት አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ለምሳሌ ፊታቸውን ሶስት ሶስት ጊዜ ሲያጥቡ እጆቻቸውን ሁለት ጊዜ እንዲሁም እግሮቻቸውን አንድ ጊዜ ያጥቡ ነበር፡፡ ዛዱ-ል-ሚዓድ (ቅጽ፡ 1 ገጽ፡ 192)፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ሶስት ሶስት ጊዜ በማሟላት ዉዱእ ያደርጉ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስተምህሮ ነው፡፡

## 10 ከዉዱእ በኋላ የሚባሉ ዱዓዎችን ማለት

أَشْهَدُ أَنَّ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ ، وَأَنَّ مُحمَّداً عَبْدُ اللهِ وَرَسُولُهُ

ከዑመር ኢብን አል-ኸጣብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹***ከመካከላችሁ ማናችሁም ወዱእ አድርጎና ዉዱኡን አዳርሶ - ወይም አሟልቶ- ከዚያ ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፣ ሙሐመድም የእሱ ባሪያና መልእክተኛ ናቸው ብየዬ እመሰክራለሁ አይልም ለእሱ ሰምንቱ የጀነት በሮች የተከፈቱለትና ከእነሱም መካከል በፈለገው የገባ ቢሆን እንጂ፡፡***›› ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (234) ዘግበውታል፡፡

سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ، أَشْهَدُ أَنْ لا إِلَهَ إِلاَّ أَنْتَ، أَسْتَغْفِرُكَ وأَتُوبُ إِلَيْكَ

ከአቢ ሰዒድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- እንደተላለፈው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ *‹‹ወዱእ አድርጎና ወዱኡን ካጠናቀቀ በኋላ፣ “ጥራት የተገባህ አላህ ሆይ! በምስጋናህ ይሁን ካንተ በስተቀር አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ምህረትን እጠይቃለሁ ወዳንተም በንሰሐ እመለስልሃለሁ” ያለ ይህችን ቃሉን አላህ ማሕተም ይመታባታል፡፡ ከዚያም ከዐርሽ ሥር እስክትደርስ ድረስ ክፍ ትደረጋለች፡፡ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ አትሰበርም፡፡››* አን-ነሳኢይ ዐመሉ-ል-የውሚ ወልለይለህ (ገጽ ፡ 147፣ እንዲሁም አል-ሓኪም በሐዲሥ ዘገባ መድብላቸው (ቅጽ፡ 1 ገጽ፡ 752) ላይ ዘግበውታል፡፡ ኢብን ሐጀር -አላህ ይዘንላቸው- የዘገባውን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ ነታኢጁ-ል-አፍካር ቅጽ፡ 1 ገጽ ፡ 246፡፡





**ሁለተኛው ክፍል፡-** የሌሊትና የዊትር ሰላቶች፡፡ በውስጡ የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ተግባረት የሆኑ በርካታ ፈለጎችን አካቷል፡፡

## 1 የሌሊት ሰላትን በላጭ በሆነው ወቅት መስገድ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡

### ‹‹በላጩ የሌሊት ሰላት ወቅት የትኛው ነው?›› ከተባለ፡-

ምላሹ፡- እንደሚታወቀው የዊትር ሰላት ወቅት ከዒሻእ ሰላት በኋላ ጀምሮ ጎሕ እስከሚቀድ ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ የዊተር ሰላት ወቅት በዒሻእና በፈጅር ሰላት መካከል ነው፡፡

**ይህን የሚያመለክተው ማስረጃ፡-**

ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው እንዲህ ብለዋል፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን- የዒሻእን ሰላት በማጠናቀቃቸውና እስከፈጅር ሰላት ድረስ ባለው ጊዜ መካከል አስራ አንድ ረከዐዎችን ይሰግዱ ነበር፡፡ በየሁለቱ ረከዐዎችም ያሰላምታሉ፡፡ በአንድ ረከዐህም ዊትር ያደርጋሉ፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2031) ሙስሊምመ ደግሞ በቁጥር (736) የዘገቡት ሲሆን ሁለቱም ተስማምተውበታል፡፡

### የሌሊት ሰላት ወቅት ደግሞ ከእኩለ-ሌሊት በኋላ ያለው የሌሊቱ ሲሶ (አንድ ሶስተኛው) ክፍል ነው፡፡

ይህም ማለት ማንኛውም ሰው ሌሊቱን ለተለያዩ ክፍሎች ይከፍለዋል፡፡ ከዚያ ከሁለተኛው አጋማሽ በኋላ ባለው የሌሊቱ ሲሶ ክፍል ተነስቶ ይሰግዳል፣ ከዚያም በሌሊቱ የመጨረሻ ክፍል ይተኛል ወይም ደግሞ የሌሊቱን የአራተኛና የአምስተኛ አንድ ስድሰተኛ የሌሊት ክፍል ቆሞ ሲሰግድ የስድስተኛ አንድ ስድስተኛ ክፍል ደግሞ ይተኛል፡፡

***ይህንም የሚያረዳ ማስረጃ*** ደግሞ ከኢብን ዑምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- የተላለፈው ሐዲሥ ሲሆን የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፤ ***‹‹በአላህ ዘንድ ተወዳጅ የሆነው ጾም የዳዉድ -በእሳቸው ላይ ሰላም ይሁን- ጾም ነው፡፡ በአላህ ዘንድ ተወዳጁ ሰላት ደግሞ የዳዉድ ሰላት ነው፡፡ ግማሹን ሌሊት ይተኙ፤ ሲሶው ላይ ተነስተው ይሰግዱ፤ አንድ ስድስተኛውን ይተኙ ነበር፡፡ አንድ ቀን ይጾማሉ አንድም ቀን ያፈጥሩ ነበር፡፡››*** ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3420) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (1159) ዘግበውታል፡፡

### አንድ ሰው ይህን ነቢያዊ ፈለግ ለመተግበር ከፈለገ የሌሊት ስሌቱ እንዴት ነው የሚሆነው?

ሌሊት የሚባለው ፀሐይ ከጠቀለችበት ጎሕ እስከሚቀድበት ጊዜ ድረስ እንደሆነ ያስባል፡፡ ከዚያ ይህን ጊዜ ለስድስት ይከፋፍለዋል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሶስት ክፍልፋዮች የሌሊቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ሲሆን ከዚያ በኋላ በአራተኛው የስድስተኛው ክፍልና በአምስተኛው የስድስተኛው ክፍል ተነስቶ ይሰግዳል፡፡ ይህ ደግሞ የሌሊቱ ሲሶ (አንድ ሶስተኛ) ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚያ በመጨረሻው የስድስተኛው ክፍል ይተኛል፡፡ ለዚህም ነው ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ፣ « «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እኔ ዘንድ የተኙ ካልሆኑ በስተቀር አገኛቸው ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1133) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (742) ዘግበውታል፡፡

በዚህ መንገድም በላጩ የሌሊት ሰላት ውስጥ ይሆናል፡፡ ይህም ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የዐብዱላህ ኢብን ዐምር -አላህ ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደሰፈረው ነው፡፡

### የርዕሱ ማጠቃለያ፡- የሌሊት ሰላት በላጭ ወቅት በሶስት ደረጃዎች ይመደባል፡፡ እነርሱም፡-

***የመጀመሪያው ደረጃ፡-*** የሌሊቱን የመጀመሪያ አጋማሽ ከተኛ በኋላ ከዚያ በኋላ ከእንቅልፉ በመንቃት አንድ ሶስተኛውን ይሰግዳል፡፡ ከዚያ -ልክ እንዳሳለፍነው- አንድ ስድስተኛውን ይተኛል፡፡

***ይህን የሚያመለክተው ማስረጃ፡-*** ከዚህ በላይ ያሳለፍነው የዐብዱላህ ኢብን ዐምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ነው፡፡

***ሁለተኛው ደረጃ፡-*** የመጨረሻውን የሌሊቱን የመጨረሻ አንድ ሶስተኛ ክፍል ከእንቅልፉ ነቅቶ ይሰግዳል፡፡

***ይህን የሚያመለክተው ማስረጃ፡-***

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፤ ***‹‹እጅግ የተባረከውና የላቀው ጌታችን የሌሊቱ የመጨረሻ ሲሶ ላይ ወደምድራዊው ሰማይ ይወርዳል፡፡ “ማነው የሚለምነኝ ልመናውን የምቀበለው፤ ማነው የሚጠቀኝ የሚጠይቀኝን የምሰጠው? ማነው ምህረት የሚጠይቀኝና ምህረት***

***የማደርግለት?"*** ይላል፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1145) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (758) ዘግበውታል፡፡ ከዚህ ሌላ ጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ያስተላለፉት ሐዲሥ ይገኛል፡፡ ይህን ሐዲሥ ወደፊት እንመለከተዋለን፡፡

የመጨረሻውን ሌሊት እንደማይነሳ የፈራ ሰው የመጀመሪያው ሌሊት ወይም የገራለትን የሊሊቱን ክፍል ይስገድ፡፡ ይህ ሶስተኛው ደረጃ ነው፡፡

**ሶስተኛው ደረጃ፡-** የመጨረሻውን ሌሊት እንደማይነሳ የፈራ ሰው የመጀመሪያው ሌሊት ወይም የገራለትን የሊሊቱን ክፍል ይስገድ፡፡

**ይህን የሚያመለከተው ማስረጃ፡-**

ጁቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፡- ***‹‹በመጨረሻው የሌሊት ክፍል መነሳትን የፈራ በመጀመሪያው ዊትር ይስገድ፡፡ የመጨረሻውን ለመነሳት የጓጓ በመጨረሻው ሌሊት ዊትር ያድርግ፡፡ በርግጥ የመጨረሻው ሌሊት -መላክት- የሚታደሙበት የሆነ ነው፡፡ ይህ በላጩ ነው፡፡››*** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (758) ዘግበውታል፡፡

በዚህም የአላህ መልእክተኛ -የአላህ መልእክተኛ እዘነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ለአቢ ዘር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የለገሷቸውና አን-ነሳኢይ በአስ-ሱነኑ-ል-ኩብራ የሐድሥ መድብል በቁጥር (2712) እንዲሁም አል-አልባኒይ በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ መጽሐፋቸው በቁጥር (2166) የዘገቡት ምክር፣ ለአቢ ደርዳእ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- የለገሷቸውና አሕመድ በቁጥር (27481)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (1433) እንዲሁም የአቢ ዳዉድ ትክክለኛ ሐዲሦች በማለት አል-አልባኒይ ባዘጋጁት መጽሐፍ ቅጽ ፡ 5 ገጽ ፡ 177 ምክር፣ ለአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የለገሷቸውና ሙሰሊም በቁጥር (737) በዘገቡት ምክር ሁሉም፣ «ወዳጄ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሶስት ነገሮች ላይ አደራ አሉኝ፡፡» ካሉ በኋላ ከጠቀሷቸው አደራዎች መካከል፣ «ከመተኛቴ በፊት ዊትር እንድሰግድ» የሚለው ይገኝበታል፡፡

## 2 አሰራ አንድ ረከዐዎች መስገድ ነቢያዊ ፈለግ ነው

ይህ ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው- ያስተላለፉት ሐዲሥ ይበልጥ ማስረጃ ነው፡፡ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነታና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ረመዳን ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ ከአስራ አንድ ረከዐዎች አይጨምሩም ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1147) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር (738) ዘግበውታል፡፡

የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስራ ሶስት ረከዐዎች መስገዳቸውን ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው- ሐዲሥ ተላልፏል፡፡

አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው በገሃድ የሚታየው ይህ ርዕስ የዊትርን የተለያየ ሁኔታ ያመለክታል፡፡ በአብዛኛው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የዊትር ሰላት አስራ አንድ ረከዐህ እንደነበርና አንዳንድ ጊዜም በአስራ ሶስት ረከዐዎች ይሰግዱ ነበር፡፡ በዚህም ሁለቱን ከዚህ በላይ የሰፈሩ ሐዲሦችን በእንዲህ መልክ አንድ ልናደርጋቸው እንችላለን፡፡

### 3 የሌሊት ሰላቱን ቀለል ባሉ ረከዐዎች መጀመር ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው

ይህ ዓኢሻህ --አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ መሰረት የሚፈጸም ነው፡፡ ዓኢሻህ --አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ሌሊት ላይ ሊሰግዱ ከተነሱ ሰላታቸውን ቀለል ባሉ ረከዐዎች ይጀምሩ ነበር፡፡» ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (767) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 4 ሐዲሥ ላይ በሰፈሩ ነቢዊ ፈለግ በሆኑ የሌሊት ሰላት መክፈቻዎች መጀመር ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል፡-



1 اللَّهُمَّ رَبَّ جَبْرَائِيلَ وَمِيكَائِيلَ وَإِسْرَافِيلَ فَاطِرَ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ، عَالِمَ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ، أَنْتَ تَحْكُمُ بَيْنَ عِبَادِكَ فِيمَا كَانُوا فِيهِ يَخْتَلِفُونَ، اهْدِنِي لِمَا اخْتُلِفَ فِيهِ مِنَ الْحَقِّ بِإِذْنِكَ إِنَّكَ تَهْدِي مَنْ تَشَاءُ إِلَى صِرَاطٍ مُسْتَقِيم

በሙስሊም ትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ ከዓኢሻህ --አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይወደድላቸው-- እንደተላለፈው፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሌሊት ላይ ለሰግዱ ከተነሱ ሰላታቸውን፣ ***“የጂብረል፣ የሚካኢልና የኢስራፊል ጌታ የሆንከው፣ ሰማያትና የምድር ፈጣሪ የሆንከው፣ ሩቁንም ቅርቡንም በእጅጉ ዐዋቂ የሆንከው አላህ ሆይ! በሕዝቦች መካከል ይለያዩበት በነበረው ነገር ላይ አንተ በእውነት ትፈርዳለህ፡፡ በፈቃድህ ከሚለያዩበት ጉዳይ ወደእውነተኛው ምራኝ፡፡ አንተ የምትሻውን ወደቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ትመራለህ፡፡››*** በሚለው ይጀምሩ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (770) ዘግበውታል፡፡

2 اللَّهُمَّ لَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ نُورُ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ، وَلَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ قَيِّمُ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ، وَلَكَ الْحَمْدُ أَنْتَ رَبُّ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ وَمَنْ فِيهِنَّ، أَنْتَ الْحَقُّ، وَوَعْدُكَ الْحَقُّ، وَقَوْلُكَ الْحَقُّ، وَلِقَاؤُكَ الْحَقُّ، وَالْجَنَّةُ حَقٌّ، وَالنَّارُ حَقٌّ، وَالنَّبِيُّونَ حَقٌّ، وَالسَّاعَةُ حَقٌّ، اللَّهُمَّ لَكَ أَسْلَمْتُ، وَبِكَ آمَنْتُ، وَعَلَيْكَ تَوَكَّلْتُ، وَإِلَيْكَ أَنَبْتُ، وَبِكَ خَاصَمْتُ، وَإِلَيْكَ حَاكَمْتُ، فَاغْفِرْ لِي مَا قَدَّمْتُ، وَمَا أَخَّرْتُ وَمَا أَسْرَرْتُ وَمَا أَعْلَنْتُ أَنْتَ إِلَهِي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ

ቡኻሪና ሙስሊም ትክክለኛ በሆነ የሐዲሥ ዘገባ ከኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ፣ ‹‹ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሌሊት ላይ ሲሰግዱ፣ ***“አላህ ሆይ! አንተ የሰማያትና የምድር***

*ብርሃን ነህ፡፡ ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ አንተ የሰማያትና የምድር አስተናባሪ ነህ፡፡ ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ አንተ የሰማያት፣ የምድርና በውስጣቸውም ያሉ ነገሮች ሁሉ ጌታ ነህ፡፡ አንተ እውነት ነህ፡፡ ቃል-ኪዳንህም እውነት ነው፡፡ ንግግርህም እውነት ነው፡፡ መገናኘትህም እውነት ነው፡፡ ጀነትም እውነት ነው፡፡ ጀሀነምም እውነት ነው፡፡ ሰአቷም እውነት ነች፡፡ አላህ ሆይ! ላንተ እጅ ሰጠሁ፣ ባንተም አመንኩ፣ ባንተም ላይ ተመካሁ፣ ወዳንተም ተመለስኩ፣ ባምተም ተፋረድኩ፣ ወዳንተም ፍርድ ሰጠሁ፣ ያሳለፍኩትን ያዘገየኹትን፣ የደበቅኩትንም ሆነ ይፋ ያደረግኩትን ወንጀሌን ማርልኝ፡፡ አንተ አምላኬ ነህ፡፡ ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡"* ይሉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (7499) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (768) ሐዲሡን ዘግበውታል፡፡

5 **መቆሙ፣ ሩኩዑና ሱጁዱ የረዘመ መሆኑና ሁሉም የሰላት ተግባራዊ የሆኑ ምሰሶዎች ተቀራራቢ መሆናቸው ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ናቸው፡፡**

6 **በሐዲሥ የተዘገቡ ነቢያዊ ፈለጎችን በቁርኣን ንባቡ ውስጥ ማምጣት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ከእነዚህም መካከል፡**

1. ረጋ ብሎ ማንበብ አለበት፡፡ ይህ ማለት መቸኮል የለበትም፡፡
2. ንባቡን አንቀጽ በአንቀጽ መለያየት አለበት፡፡ ይህ ማለት ሁሉንም ሳያቋርጥ ሁለት፣ ሶስት አንቀጾችን አንድ ላይ እያያዘ ማንበብ የለበትም፡፡ ስለዚህ በእያንዳንዱ አንቀጽ መቆም አለበት፡፡
3. አላህን በሚያጠራ አንቀጽ ላይ ሲደርስ አላህን ከሚባሉና ከሚነገሩ ነገሮች ማጥራት፣ አላህን በሚጠይቁ አንቀጽ ላይ ሲደርስ አላህን መጠየቅ እንዲሁም በአላህ መጠበቅን በሚጠይቁ አንቀጾች ላይ ሲደርስ በአላህ መጠበቅን መጠየቅ አለበት፡፡

**ከዚህ በላይ ላሳለፍነው ሃሳብ ማስረጃው፡-**

**سُبْحَانَ رَبِّيَ الْعَظِيمِ - سمِعَ اللهُ لِمَنْ حَمِدَهُ - سُبْحَانَ رَبِّيَ الأَعْلَى**

ሑዘይፋህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ከእለታት አንድ ቀን ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ጋር አንዲት ሌሊት ሰገድኩ፡፡ ሰላታቸውን በአል-በቀራህ ምዕራፍ ጀመሩ፡፡ መቶኛው አንቀጽ ላይ ረኩዕ ያደርጋሉ አልኩ፡፡ ከዚያ -ንባባቸውን- ቀጠሉ፡፡ በዚያው ሌላ ረከዐህ ይሰግዳሉ አልኩ፡፡ አሁንም ቀጠሉ፡፡ አሁንም ሩኩዕ ያደርጋሉ አልኩ፡፡ የአን-ኒሳእን ምዕራፍ ጀመሩ፡፡ ከዚያ የአል-ዒምራንን ምዕራፍ ጀመሩና አነበቡት፡፡ ረጋ ብለው ያነቡ ነበር፡፡ አላህን ከሚባሉ ነገሮች በሚያጠራ ቦታ ላይ ሲያልፉ አላህን ከሚባሉት ነገሮች ያጠራሉ፡፡ አላህን በሚጠይቅ አንቀጽ ላይ ሲያልፉ አላህን ይጠይቃሉ፡፡ ከአላህ ጥበቃን በመጠየቅ አንቀጽ ላይ ሲያልፉ በአካህ ይጠበቃሉ፡፡ ከዚያ ሩኩዕ አደረጉና፣ ***"በእጅጉ የላቀው ጌታዬ ጥራት ተገባው፡፡"*** አሉ፡፡ ረኩዐቸው ልክ እንደመቆማቸው ዓይነት ነበር፡፡ ከዚያም ***"አላህ ለሚያሰመሰግነው ምስጋናውን ሰማ፡፡"*** አሉና ከሩኩዐቸው ተነሱ፡፡ ከዚያም ልክ ከሩኩዐቸው ጋር የቀረበ መቆምን ቆሙ፡፡ ከዚያ ሱጁድ አደረጉና ***"እጅግ ልእልና የተገባው ጌታዬ ጥራት ተገባው"*** አሉ፡፡ ሱጁዳቸው ከመቆማቸው ጋር የተቀራረበ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (772) ላይ ዘግበውታል፡፡

{بِسْمِ اللهِ الرَّحْمنِ الرَّحِيمِ الحَمْدُ للهِ رَبِّ الْعَالَمِينَ الرَّحْمنِ الرَّحِيمِ مَالِكِ يَوْمِ الدِّينِ}

አሕመድ -አላህ ይዘንላቸው- ሙስነድ በተሰኘው የሐዲሥ ዘገባቸው ከኡምሙ ሰለመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ስለየአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የቁርአን አነባብ (አቀራር) ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም «ንባባቸው አንቀጽን ከአንቀጽ ይለያይ ነበር፡፡ {በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ አዛኝ በኾነው፥ ምስጋና ለአላህ ይገባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፥ እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ፥ የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው፥ አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ ርዳታን እንለምናለን፥ ቀጥተኛውን መንገድ ምራን፥ የነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን፥ በነሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን፤ በሉ)፡፡} አሕመድ አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (26538) የዘገቡት ሲሆን አድ-ዳረልቁጥኒይ በሐዲሥ ዘገባቸው "የዘገባ ሰንሰለቱ ትክክል ነው፡፡ አስተላላፊዎቹ ሁሉም እምነት የሚጣልባቸው ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡ አን-ነወዊም ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (አል-መጅሙዕ ገጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 333)፡፡

## 7 በየሁለቱ ረከዐዎች ሰላቱን በሰላምታ ማጠናቀቁ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡ ፡



ኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «አንድ ሰው ተነሳና ለአላህ መልእክተኛ ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የሌሊት ሰላት እንዴት ነው?› አላቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም- የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፤ **‹‹የሌሊት ሰላት ጥንድ፤ ጥንድ ነው፡ ፡ ሱብሒን ከፈራሕ በአንድ ረከዐህ ዊትር አድርግ፡ ፡ ››** አሉ፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (990)፤ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (749) ላይ ዘግበውታል፡፡

**(ጥንድ፤ ጥንድ)** ማለት ሁለት፤ ሁለት ረከዐህ ይሰገዳል፡፡ በየሁለቱ ረከዐህ ሰላቱን በሰላምታ ያጠናቅቃል፡፡ አራት ረከዐዎችን አንድ ላይ አጣምሮ አይሰግድም ማለት ነው፡፡

## 8 በሶስቱ የመጨረሻ ረከዐዎች ላይ የተወሰኑትን የቁርአን ምዕራፎች መቅራት (ማንበብ) ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው፡ ፡

በመጀመሪያው ረከዐህ ላይ፤ **‹‹ሰብቢሒ-ስመ ረብቢከ-ል-አዕላ››**ን፤ በሁለተኛው ረከዐህ ላይ፤ **‹‹ቁል ያ አይዩሃ-ል-ካፊሩዉን››**ን እንዲሁም በሶሰተኛው ረከዐህ ላይ፤ «ቁል ሁው-ልላሁ አሐድ»ን ያነባል፡፡

**ለዚህም ማስረጃው**

{سَبِّحِ اسْمَ رَبِّكَ الْأَعْلَى} - {قُلْ يَا أَيُّهَا الْكَافِرُونَ} - {قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ}

ኡበይ ኢብን ከዕብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳአው ላይ ይሁን- **በሰብቢሒ-ስመ ረብቢከ-ል-አዕላ፤ በቁል ያ አይዩሃ-ል-ካፊሩዉን** እና **በቁል ሁው-ልላሁ አሐድ**

ዊትር ይሰግዱ ነበር፡፡» አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1423)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (1733) እና ኢብን ማጀህ በቁጥር (1171) ሐዲሡን የዘገቡት ሲሆን አን-ነወዊይ ( በአል-ኹላሰህ ቅጽ፡ 1 ገጽ፡ 556) እንዲሁም አል-አልባኒይ (በአን-ነሳኢይ ትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ ቅጽ፡ 1 ገጽ ፡ 273) መጽሐፎቻቸው ላይ የሐዲሡን ትክክለኛነት አስፍረዋል፡፡

### 9 ግለሰቡ አንዳንድ ጊዜ በዊትር ሰላቱ ላይ ቁኑት ማድረጉ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡



ቁኑት ማለት ዱዓእ ማለት ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው የአል-ኢኽላስን ምዕራፍን በሚያነብበት ሶስተኛው ረከዐህ ላይ ነው፡፡

ቁኑትን የዊትር ሰላት ላይ አንዳንድ ጊዜ ማድረጉ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መተዉ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ሸይኹ-ል-ኢስላም ኢብን ተይሚይየህ -የአላህ ይዘንላቸው- የመረጡትና ቅድሚያ የሚሰጠው ከማድረጉ አብዛኛውን ጊዜ መተዉን ነው፡፡

#### ጥያቄ፡- በዊትር ቁኑት ላይ እጆቹን ከፍ ያደርጋልን?

**ትክክለኛው፡፡** በርግጥ እጆችን ያነሳል የሚለው ነው፡፡ ይህንንም አብዛኞቹ ዑለሞች ደግፈውታል፡፡ ይህም ከኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የተረጋገጠ በመሆኑና በአል-በይሀቂይ መጽሐፍ ውስጥ የሰፈረ በመሆኑ ነው፡፡

አል-በይሀቂይ -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰሓቦች -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በቁኑት ላይ እጆቻቸውን ከፍ አድርገዋል፡፡» (አስ-ሱነኑ-ል-ኩብራ ቅጽ፡ 2 ገጽ፡ 211ን ይመልከቱ)

#### ጥያቄ፡- ዊትር ላይ የሚያደርገውን ቁኑቱን በምን ይጀምራል?

ተመራጩ የዑለሞች አስተያየት -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፤ አላህን በማመስገንና በማወደስ፣ ከዚያም በነቢዩ ላይ የአላህን እዝነትና ሰላምታ በማቅረብ መጀመሩ ነው፡፡ ከዚያ ዱዓእ ያደርጋል፡፡ ይህ ለጥያቄው በጣም የቀረበ መልስ ነው፡፡

**ለዚህም ማስረጃው፡-**

ፉዳለህ ኢብን ዑበይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ የአላህን እዝነትና ሰላምታ ሳያወርድ ዱዓእ ሲያደርግ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰሙትና፣ **“ይህ ሰው ተቻኮለ፡፡››** አሉና ሰውየውን ጠርተዉት ለእሱና ለሌሎችም እንዲህ አሉ፣ **“አንዳችሁ ዱዓእ ካደረገ አላህን በማመስገንና በማወደስ**

***ይጀምር፡፡ ከዚያ ነቢዩ ላይ የአላህን እዝነትና ሰላምታ ያወርድ፡፡ ከዚያ በኋላ ያሻውን ዱዓእ ያድርግ"*** አት-ቲርሚዚይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3477) ላይ ሐዲሡን የዘገቡ ሲሆን፤ «ይህ በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኝ ትክክለኛ ሐዲሥ ነውም» ብለዋል፡፡

ኢብን አል-ቀይዩም -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «በዱዓእ ላይ የሚወደደው ዱዓእ አድራጊው አላህን በማመስገን መጀመሩ፣ በጉዳዮች መካከል አላህን ማወደሱ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ በፉዳለህ ኢብን ዑበይድ ሐዲሥ ላይ እንደተወሳው ጉዳዩን ይጠይቅ፡፡» (አል-ዋቢሉ-ስሰይዩብ ገጽ፡- 110)

### ጥያቄ፡- ከቁኑት ዱዓእ በኋላ ፊቱን በመዳፎቹ ያብሳልን?

ትክክለኛው፡- ትክክለኛ የሆነ ሐዲሥ ባለመኖሩ ምክንያት ከዱዓእ መጠናቀቅ በኋላ ፊትን ማበስ ነቢያዊ ፈለግ አይደለም የሚለው ነው፡፡

ኢማም ማሊክ -አላህ ይዘንላቸው- በዱዓእ ወቅት ፊቱን በመዳፎቹ ፊቱን ስለሚያብስ ሰው ሁኔታ ተጠየቁ፡፡ እሳቸውም ይህን አስተባበሉና፣ «አላወቅኩም፡፡» አሉ፡፡ አል-መርወዚይ አል-ዊትር ገጽ፡ 236፡፡

ሸይኹ-ል-ኢስላም -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ፊቱን በመዳፎቹ ማበስን አስመልክቶ ማስረጃ የሚሆን አንድ ወይም ሁለት ሐዲሦች ፈጽሞ አልተዘገቡም፡፡» አል-ፈታዋ ቅጽ፡ 22 ገጽ፡ 519፡፡

## 10 በመጨረሻው የሌሊቱ አንድ ሶስተኛ ክፍል ዱዓእ ማድረግ



በነቢዩ ይዘወተሩ ከነበሩ የሌሊት ሰላት ነቢያዊ ፈለጎች መካከል ዱዓእ ማድረግ አንዱ ነው፡፡ በመጨረሻው ላይ ዱዓእ ባያደርግም በሌሊቱ መጨረሻ ላይ ቁኑት ላይ የሚያደርገው ዱዓእ ለአንድ ሰው በቂው ነው፡፡ በዚህ ወቅት ዱዓእ ማድረግ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ወቅት ዱዓእ ምላሽ እንደሚያገኝ የተረጋገጠበት ወቅት ከመሆኑ ባሻገር ልእልና የተገባው የክብር ባለቤት አላህ ወደምድራዊ ሰማይ የሚወርድበት ወቅትም በመሆኑ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ቡኻሪና ሙስሊም ከአቢ ሁረይረህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ ***‹‹የተባረከውና ልእልና የተገባው ጌታችን የመጨረሻው ሌሊት አንድ ሶስተኛ ሲቀር ወደምድራዊው ሰማይ ይወርዳል፡፡ "ማነው የሚለምነኝ ምላሽ የምሰጠው፣ ማነው የሚጠይቀኝ የጠየቀኝን የምሰጠው፣ ማነው ምህረትን የሚጠይቀኝ ምህረትን***

***የምለግሰው፡ ፡”*** ይላል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1145) ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (758) ላይ ዘግበውታል፡፡

**11 የዊተር ሰላቱን በሰላምታ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ሶስት ጊዜ ‹‹ሱብሓነ መሊከ-ል-ቁዱስ›› /የተቀደሰው ንጉሥ በእሱ ላይ ከሚባለው ከንቱና ውድቅ የሆነ ነገር ሁሉ ጠራ፡ ፡/ ይልና ሶስተኛው ላይ ድምጹን ከፍ ያደርጋል፡ ፡**

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ኡበይ ኢብን ከዕብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «የአላህ መልእከተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዊትር ሰላት ላይ፣ {***ሰብቢሒ-ስመ ረብቢከ-ል-አዕላ***}ን፣ {***ቁል ያ አይዩሀ-ል-ካፊሩዉን***}ንና {*ቁል ሁወ-ልላሁ አሐድ*}ን ይቀሩ ነበር፡፡ ሰላታቸውን በሰላምታ ካጠናቀቁ በኋላ ሶሰት ጊዜ፣ **“ሱብሓነ መሊከ-ል-ቁዱስ”** ይሉ ነበር፡፡» አን-ነሳኢይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1702) ሐዲሡን ሲዘግቡ ከዚህ በላይ እንዳሳለፍነው አል-አልባኒይ የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ ከዐብዱራሕማን ኢብን አብዛ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተላለፈው ሐዲሥ ደግሞ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **‹‹ሱብሓነ መሊከ-ል-ቁዱስ››** ሲሉ በሶስተኛው ላይ ድምጻቸውን ከፍ ያደርጉ ነበር፡፡ አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (15354)፣ አን-ነሳኢይ ደግሞ በቁጥር (1734) ሐዲሡን ሲዘግቡ  አል-አልባኒይ የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ ተሕቂቁ ሚሽካቱ-ል-መሳቢሕ ቅጽ፡ 1 ገጽ ፡ 389፡፡

**12 ቤተሰቡን  ለሌሊት ሰላት መቀስቀሱ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡ ፡**

አንድ ሰው ቤተሰቡንና ሚሰቱን ለሌሊት ሰላት መቀስቀሱ እንዲሁም አንዲት ሴት ለሌሊት ሰላት ባሏንና  መቀስቀሷ ከነቢያዊ ፈለግ መካከል ነው፡፡ ይህ በመልካም ነገር ላይ የመተበባር አንዱ ምዕራፍ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እኔ በእሳቸውና በቂብላህ መካከል ተኝቼ የሌሊት ሰላታቸውን ይሰግዱ ነበር፡፡ ዊትር ሊሰግዱ ሲፈልጉ ይቀሰቅሱኛል እኔም ተነስቼ ዊትር እሰግዳለሁ፡፡» ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (512)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (512) ዘግበውታል፡፡

ኡምሙ ሰለመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን- ከእንቅልፋቸው ነቁና፤ ***“ከሚባለው ከንቱና ውዳቂ የሆነ ነገር አላህ ጠራ ከሃብቱ ምንድን ወረደ፣ ከፈተናዎች ምንስ ወረደ፣ -ሚስቶቻቸውን ለመጥቀስ ፈልገውም- እስኪሰግዱ ድረስ የቤቶቹን ባለቤቶች ማነው ከእንቅልፋቸው የሚያነቃቸው ምናልባት በምድር ላይ የለበሰች የሆነች በወዲያኛው ዓለም እርቃን ትሆናለች፡ ፡”*** አሉ፡፡» ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (618) ዘግበውታል፡፡

**13 ለሌሊት ሰላት የሚነሳ ሰው በሰላቱ ውስጥ ያለው ተመስጥኦ ላይ ተጽእኖ እንዳትፈጥር ለነፍሱ የሚራራ ሰው መሆን አለበት፡ ፡**

**ድካም ከተሰማው ተቀምጦ ይሰግዳል፡ ፡**

አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ ‹‹የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደመስጂድ ገቡ፡፡ በምሰሶዎች መካከል ገመድ ተዘርግቶ ነበር፡፡ “ይህ ምንድን ነው?” አሉ፡፡ ሰሓቦችም፤ ‹ለምትሰግደዋ ዘይነብ ነው፡፡ከተሳነፈች ወይም ከደከመች ትይዘዋለች፡፡› አሏቸው፡፡ እሳቸውም፤ **“ፍቱት፡፡ አንዳችሁ በንቃት ውስጥ በሚሆንበት ወቅት ይስገድ፡፡ ከተሳነፈ ወይም ከተዳከመ ይቀመጥ፡፡»** አሉ፡፡›› ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (784) ዘግበውታል፡፡

**እንቅልፍ ካንጎላጀው ንቁ ይሆን ዘንድ ይተኛ፡፡ ተኝቶ ሲነሳ የቻለውን ይስገድ፡፡**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፤ **“አንዳችሁ ሰላት ውስጥ ካንጎላጀ እንቅልፉ እስኪሄድለት ድረስ ይቀመጥ፡፡ አንዳችሁ እያንጎላጀ ከሰገደ ምናልባት አላህን ምህረት ለመጠየቅ ይሄድና ራሱን ሊሰድብ ይችላል፡፡”** ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (212)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (786) ዘግበውታል፡፡

**ሌሊት ላይ ቁርኣን ሲቀራ ማንጎላጀት ወይም አንዳች የመሰለ ነገር ከተሰማው ብርታት ያገኝ ዘንድ መተኛቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አንዲህ ብለዋል፤ **“አንዳችሁ ሌሊት ላይ ተነስቶ ሲሰግድ ቁርአን አንደበቱ ላይ ባይተዋር ከሆነበትና ምን እንደሚል የማያውቅ ከሆነ ይተኛ፡፡”** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (787) ዘግበውታል፡፡

## 14 ሌሊት ላይ የሌሊት ሰላት ያመለጠው ሰው ቀን ላይ ይተካው ዘንድ ይሰግዳል፡፡

በሶስት ረከዐህ ዊትር መስገድ ልማዱ ከሆነና ዊትር ሳይሰግድ ከተኛ ወይም ከታመመና በዚህ ምክንያት መስግድ ካልቻለ ቀን ላይ አራት ረከዐህ አድርጎ ይሰግደዋል፡፡ ዊትርን አምስት ረከዐህ አድርጎ መስገድ ልማዱ ከሆነና ዊትር ሳይሰግድ ከተኛ ወይም ከታመመና በዚህ ምክንያት መስግድ ካልቻለ ቀን ላይ ስድሰት አድርጎ ይሰግዳል፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነበር ነበዩ - የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይፈጽሙ የነበረው፡፡ ነቢዩ - የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በአስራ አንድ ረከዐዎች ዊትር መስገድ ልማዳቸው ነበር፡፡ይህን በተመለከተ ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ ‹‹እንቅልፍ ወይም ሕመም ከሌሊት ሰላት ካሸነፉቸው ቀን ላይ አስራ ሁለት ረከዐዎችን ይሰግዱ ነበር፡፡›› ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (746) ዘግበውታል፡፡



## ሁለተኛ፡- የፈጅር ወቅት



**በዚህ ወቅት የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈለጎች የሆኑ በርካታ ተግባራት ተዘግበዋል፡፡**

### አዛን፤ በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ፡-

### 1 አዛንን መከታተል

لا حول ولا قوة إلا بالله

አዛንን የሚሰማ ሰው ሐይየ ዐለ-ስሰላህና ሐይየ ዐለ-ል-ፈላሕ ከሚለው በስተቀር ሙአዚኑ እንደሚለው ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ሐይየ ዐለ-ስሰላህና ሐይየ ዐለ-ል-ፈላሕ ላይ ግን **‹‹ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ››** ይላል፡፡

ዐብዱላህ ኢብን ዐምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **“ሙአዚንን ከሰማችሁ እንደሚለው ዓይነት በሉ፡፡…”** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (384) ዘግበውታል፡፡ ከዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) እንደተወራው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ***“አንድ ሙአዚን ‹‹አላሁ አክበር አላሁ አክበር›› ሲል አንዳችሁ “ከልቡ አላሁ አክበር አላሁ አክበር” ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹አሽሀዱ አን ላኢላሀ ኢልለላህ›› ሲል (አንዳችሁ) ‹‹አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለላህ›› ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ›› ሲል (አንዳችሁ) ‹‹አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ›› ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹ሐይየ ዐለ-ስሰላህ›› ሲል (አንዳችሁ) “ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ” ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹ሐይየ ዐለል-***

***ፈላሕ›› ሲል (አንዳችሁ) ‹‹ላ ሐውላ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ›› ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹አላሁ አክበር አላሁ አክበር›› ሲል (አንዳችሁ) ‹‹አላሁ አክበር አላሁ አክበር›› ካለ፣ (ሙአዚኑ) ‹‹ላ ኢላሀ ኢልለላህ ሲል (አንዳችሁ) ላ ኢላሀ ኢልለላህ›› ካለ ጀነት ገብቷል፡፡”*** ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (385) ዘግበውታል፡፡

ለፈጅር ሰላት በማነሳሺያ ቃላት ወቅት አዛኑን የሚከታተል ሰው ሙአዚኑ እንደሚለው ***‹‹አስ-ሰላቱ ኸይሩን ሚነ-ንነውም››*** ይላል፡፡

## 2 የሚከተለውን ዚክር ከሸሃደተይን በኋላ ማለት፡-

**أَشْهَدُ أَنْ لاَ إِلهَ إِلاَّ الله وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ، وَأَنَّ مُحَمَّداً عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ، رَضِيتُ بِالله رَبَّاً، وَبِمُحَمَّدٍ رَسُولاً، وَبِالإِسْلاَمِ دِيناً**

ሙአዚኑ ሁለተኛው ላይ «አሽሀዱ አን-ላ ኢላሀ ኢልለላህ» ካለ በኋላ ከሰዕድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የተላለፈውና የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ያሉትን ዚክር ማለት ነቢያ ፈለግ ነው፡፡ ***“አንድ ሙአዚን አዛን ሲያደርግ የሰማ ሰው ከዚያም “አሽሀዱ አን ላ ኢለሀ ኢልለላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ወአንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ ረዲይቱ ቢልላሂ ረብበን ወቢ ሙሐመደን ረሱለን ወቢል ኢስላሚ ዲይነን” ያለ ሃጢአቱ ተምሮለታል፡፡”*** ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (386) ዘግበውታል፡፡

## 3 ከአዛን በኋላ በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ ሰላዋት ማድረግ፡፡

ከዐብደላህ ኢብን ዐምር ኢብን አልዓስ (ረ.ዐ) እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ “አንድ አዛን የሚያደርግ ሰው (ሙአዚን) አዛን ሲያደርግ ከሰማችሁ (እሱ) እንደሚለው በሉ፡፡ ከዚያ በእኔ ላይ ሰለዋት አድርጉ፡፡ በርግጥ በእኔ ላይ አንድ ሰለዋት ያደረገ አላህ በእርሱ ላይ አስር ሰለዋት ያደርግለታል፡፡ ከዚያ የላቀውን ደረጃ (ከአላህ) ጠይቁልኝ፡፡ ይህች ደረጃ ከአላህ ባሪያዎች መካከል ለአንዱ ካልሆነች በስተቀር ለማንም የተገባች አይደለችም፡፡ ስለዚህ ይህ የአላህ ባሪያ እኔ እሆን ዘንድ እሻለሁ፡፡ ይህችን የላቀች ደረጃ ለእኔ የጠየቀልኝ ሰው በእርሱ ላይ አማላጅነቷ ተረጋገጠችለት፡፡ ” ሲሉ በርግጥ መሰማታቸውን ተናግረዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (384) ዘግበውታል፡፡

**اللهم صلّ على محمد وعلى آل محمد ، كما صليت على إبراهيم**


በላጭ የሆነው ሰለዋት፡- ሰላቱ አል-አብራሂሚይየህ ነው፡፡ ይኸውም፡- **‹‹አላህ ሆይ! በሙሐመድ ላይና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነት አድርግ፡፡ በኢብራሂም ላይና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነት እንዳደረግከው ሁሉ…››**

## 4 ከአዛን በኋላ የሚባሉ ዱዓዎችን ማለት

**اللَّهُمَّ رَبَّ هَذِهِ الدَّعْوَةِ التَّامَّةِ، وَالصَّلَاةِ الْقَائِمَةِ، آتِ مُحَمَّدًا الْوَسِيلَةَ وَالْفَضِيلَةَ، وَابْعَثْهُ مَقَامًا مَحْمُودًا الَّذِي وَعَدْتَهُ**

ከጃቢር ኢብን ዐብዱላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተወራው የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) “ጥሪውን በሚሰማ ጊዜ፤ «አልላሁምመ ረብበ ሀዚሂ-ድዳዕወቲ አት-ታምመህ ወስ-ሰላቲ-ል-ቃኢመህ ኣቲ ሙሐመደኒ-ል-ወሲለተ ወል ፈዲይለህ ወብዐሥሁ-ልላሁምመ መቃመ መሕሙውደኒ-ልለዚይ ወዐድተህ» /የዚህች ምሉዕ የሆነች ጥሪና የምትሰገደው ስላት ጌታ የሆንከው አላህ ሆይ! ለሙሐመድ ከፍ ያለ ደረጃንና ልቅናን ስጣቸው፡፡ የተመሰገነችውን የላቀች ስፍራም ቃል በገባህላቸው መሠረትም ቀስቅሳቸው፡፡ ያለ በትንሳኤ እለት አማላጅነቴ ተረጋገጠችለት፡፡” ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (614) ዘግበውታል፡፡

### 5 ከአዛን በኋላ ዱዓእ ማድረግ፡-



ዐብዱላህ ኢብን ዐምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፤ «አንድ ሰው ፣ «የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ሙአዚኖች ይበልጡናል፡፡» አላቸው፡ ፡ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **“እንደሚሉት በል፡፡ ከጨረስክ በኋላም ጠይቅ ይሰጥሃል፡፡”** አሉ፡፡ አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (524) ሐዲሡን ሲዘግቡት ኢብን ሐጀር የዘገባው ደረጃ ጥሩ ነው ብለዋል፡፡ (ነታኢጁ-ል-አፍካር ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 367) አል-አልባኒይም ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ሰሒይሑ-ል-ከሊሙ-ጥጠይብ ገጽ ፡ 73)

አነስ ኢብን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “በአዛንና በኢቃማህ መካከል የሚደረግ ዱዓ ተመላሽ አይሆንም፡፡” ብለዋል፡፡ አን-ነሳኢይና በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (9895) የዘገቡት ሲሆን ኢብን አል-ኹዘይመህ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 221 እና 425)

### የፈጅር ሰላት ነቢያዊ ፈለግ፡- በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉበት


የፈጅር ሰላት ነቢያዊ ፈለግ አንድ የአላህ ባሪያ በቀኑ መጀመሪያ የሚፈጸማቸው ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ በውስጡም በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህን ነቢያዊ ፈለጎች ከመዘርዘራችን በፊት ነቢያዊ ፈለጎቹን በተመለከተ አንዳንድ ነገሮችን እንመለከት፡፡ እነዚህ ነቢያዊ ፈለጎች ቋሚ የሆኑና ግዴታ የሆኑ ሰላቶችን ተከትለው የሚመጡ ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ በቁጠር አስራ ሁለት ረከዐዎች ናቸው፡፡

ከኡምሙ ሐቢባህ -አላህ መልካም ሠራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተወራው፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“በቀንና በሌሊት ውስጥ አስራ ሁለት ረከዐዎችን የሰገደ በእነሱ ሰበብ ጀነት ውስጥ ቤት ተገንብቶለታል፡፡”** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (728) ላይ ዘግበውታል፡፡ ይህንኑ ሐዲሥ አት-ቲርሚዚይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (415)፣ **“ከአዝ-ዙህር በፊት አራት፣ ከአል-ዐስር በፊት ሁለት፣ ከአል-መግሪብ በኋላ ሁለት፣ ከአል-ዒሻእ በኋላ ሁለትና ከአል-ፈጅር በፊት ሁለት ረከዐዎች ናቸው፡፡”** የሚለውን ጨምረው ዘግበዋል የሐዲሡን ዘገባም መልካም ነውም ብለዋል፡፡

### እነዚህ ነቢያዊ ፈለጎች ቤት ውስጥ መሰገዳቸው በላጭ ነው፡፡

ዘይድ ኢብን ሣቢት -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሰዎች ሆይ! ቤቶቻችሁ ውስጥ ስገዱ፡፡ በርግጥ ግዴታ ከሆኑት ሰላቶች በስተቀር ለአንድ ሰው በላጩ ሰላት ቤቱ የሚሰግደው ሰላቱ ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (7290)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (781) ላይ ዘግበውታል፡፡

### ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ጠበቅ ያለው ነቢያዊ ፈለግ



ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ጠበቅ ያለው ነቢያዊ ፈለግ የአል-ፈጅር ሰላት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃው የሚከተለው ነው:-

1. ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ከአስ-ሱብሕ በፊት ካሉት ሁለት ረከዐዎች በስተቀር በፍላጎት መፈጸሙ ሰላቶች ላይ አንዳችም ከእሳቸው ጋር ብርቱ ቃል-ኪዳን አልነበረም፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1196)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (724) ላይ ዘግበውታል፡፡
2. ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“የአል-ፈጅር ሁለት ረከዐዎች ከምድርና በእሷ ውስጥ ካሉት ነገሮች የተሻሉ ናቸው፡፡”** ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (725) ላይ ዘግበውታል፡፡

### ከአል-ፈጅር ሰላት በፊት የሚሰገዱት ሁለት ረከዐዎች በበረካታ ሁኔታዎች ከሌሎች ለይት ይላሉ፡-

**አንደኛ፡-** ከላይ እንዳሳለፍነው በጉዞ ላይ ሳሉ ወይም በአንድ ሥፍራ ላይ ዘውታሪ በሚኾንበት ወቅት መደንገጋቸው ነው፡፡ እንደ የአዝ-ዙህር፣ የአል-ዐስር፣ የአል-መግሪብና የአል-ዒሻእ ነቢያዊ ፈለግ የሆኑ ሌሎች ሰላቶችን በጉዞ ላይ ሳሉ ወይም በአንድ ሥፍራ ላይ ዘውታሪ በሚኾንበት ወቅት መተዉ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ሁለተኛ፡-** ከዚህ በላይ እንዳሳለፍነው ምንዳቸው ከምድርና በውስጧ ከሚገኙ ነገሮች በእጅጉ የሚበልጥ መሆናቸው ነው፡፡

**ሶስተኛ፡-** ከዚህ በላይ ባሰለፍነው ማስረጃ ላይ እንደተመለከተው እነሱን ቀለል አድርጎ መስገድ ነቢያዊ ፈለግ ይሆናል፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በውስጣቸው የአል-ፋቲሐን ምዕራፍ

አንብበዋልን ወይንስ አላነበቡም? እስከምል ድረስ የአል-ፈጅርን ረከዐዎች ቀለል አድርገው ይሰግዷቸው ነበር፡፡» ይሉ ነበር፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1171)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (724) ዘግበውታል፡፡

**ነገር ግን** ይህ ቀለል ማድረግ ግዴታ በሆነውን ነገር ላይ ክፍተት የሚፈጥር ወይም ሰላቱን ጎንበስ ቀና በማለት እንዲሰገድና ሰውየውን ክልክል በሆነ ነገር ላይ የሚጥር መሆን የለበትም የሚለው **በቅድመ-መስፈርትነት** ይቀመጣል፡፡

**አራተኛ፡-** ከአል-ፈጅር ሰላት በፊት በሚሰገዱት ሁለት ረከዐዎች ላይ ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ በኋላ በመጀመሪያው ረከዐህ ላይ፣ **‹‹ቁል ያ አይዩሃ-ል-ካፊረዉን››**ን በሁለተኛው ረከዐህ ላይ ደግሞ፣ **‹‹ቁል ሁወ-ልላሁ አሐድ››**ን ማንበብ ወይም ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ በኋላ በመጀመሪያው ረከዐህ ላይ፣

***‹‹ በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን)÷ ወደኢብራሂምም÷ ወደኢዕ,ስማዒልና ወደኢስሓቅም÷ወደያዕቁብና ወደነገዶቹም÷ በተወረደው÷ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት÷ በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት÷ ከነርሱ በአንድም መካከል ማንለይ ስንኾን አምንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ፡፡››*** (አል-በቀራህ ፡ 136) የሚለውን የቁርአን አንቀጽ ሲያነብ፣

በሁለተኛው ረከዐህ ላይ ደግሞ፡-

***‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በኛና በናንተ መካከል ትክክል ወደኾነች ቃል ኑ፤ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ÷ በርሱ ምንንም ላናጋራ÷ ከፊላችንም ከፊሉን አማልክት አድርጎ ላይዝ ነው፤ በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡››*** (ኣል-ዒምራን ፡ 64) የሚለውን የቁርኣን አንቀጽ ያነባል፡፡ እነዚህ በተለያዩ ዓይነት ሁኔታዎች የተዘገቡ ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰውን ይፋጽማሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሁለተኛውን ይፈጽሙ ነበር፡፡

**አምስተኛ፡-** ከአል-ፈጀር ሱንና ሰላት በኋላ በቀኝ ጎን ጋደም ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሁለቱን የአል-ፈጅር ረከዐዎች ከሰገዱ በኋላ በቀኝ ጎናቸው ጋደም ይሉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1160)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (736) ዘግበውታል፡፡

### ወደመስጂድ መሄድ፡- በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች ይገኛሉ

የአል-ፈጅር ሰላት አንድ ሰው በቀኑ መጀመሪያ ላይ የሚሰግደውና ወደመስጂድም የሚሄድበት ሰላት ከመሆኑ አንጻር ይህ ሰው ወደመስጂድ ለመሄድ ሲነሳ ሊፈጸማቸው የሚገቡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

### 1 ወደመስጂድ በጊዜ መሄድ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ለሰላት በጊዜ መምጣት**

***ያለውን ነገር ብታውቁ ኖሮ ሰዎች በእሱ ላይ ይሽቀዳደሙ ነበር”*** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (615)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (437) ዘግበውታል፡፡

## 2 እርምጃዎቹ ይመዘገቡ ዘንድ ከቤቱ ወዱእ አድርጎ መውጣት አለበት፡፡




አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***“አንድ ሰው የጀማዐህ ሶላት ቤቱ ወይም መገበያያው ውስጥ ከሚሰግደው ሶላት በሃያ አምስት እጥፍ ይበልጣል፡፡ ይህም ውዱእ ካደረገ ውዱኡንም ካሳመረ ከዚያም ወደ መስጂድ ለሶላት ሲል ብቻ ከወጣ፣ አንድ እርምጃ አይራመድም በእሷ (በእርምጃዋ) ምክንያት አንድ ደረጃ ከፍ ያለለት አንዷት ሃጢአት የተሰረዘለት ቢሆን እንጂ፡፡ በሚሰግድ ጊዜ የሰገደበትን ቦታ እስኪለቅ ድረስ ውዱእ ሳያፈርስ (ሳያበላሽ) በመስገጃው ላይ ከሆነ መላኢኮች “አላህ ሆይ! ረድኤትህን በእሱ ላይ አውርድ፣ እዘንለትም፡፡” በማለት ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ (ከሰገደው ሶላት ሌላ) ሶላት እስከተጠባበቀ ድረስ ሶላት ውስጥ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡”*** ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (649) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 3 ወደሰላት በተረጋጋና በሰከነ መንፈስ መውጣት አለበት፡፡

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***“ወደሰላት የመግባት ጥሪን በሰማችሁ ጊዜ ወደሰላት ሂዱ፡፡ በሰከነና በተረጋጋ መንፈስ መሄድን አደራችሁን፡፡ ሰላትንም እስካገኛችሁ ድረስ አትቸኩሉ፡፡ ያለፋችሁን አሟሉ፡፡”*** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (636)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (602) ላይ ዘግበውታል፡፡

አን-ነወዊይ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «የሰከነ መንፈስ ማለት እርምጃዎችን በቀስታ ማምጣትና ጨዋታን መራቅ ማለት ሲሆን እርጋታ ማለት እይታን እንደመሰብሰብ፣ ድምጽን መቀነስና ከወዲያ ወዲህ እንዳለመዞር ዓይነት ነው፡፡» ብለዋል፡፡ አን-ነወዊይ፡- ሸርሑ ሙስሊም ሐዲሥ ቁጥር (602) «ወደሰላት በርጋትና በሰከነ መንፈስ መምጣት የመወደዱና እየሮጡ መምጣት የመጠላቱ ምዕራፍ»

## 4 መስጂድ ውስጥ ሲገቡ ቀኝ እግርን ማስቀደም፣ ሲወጡ ደግሞ ግራ እግርን ማስቀደም



አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «መስጂድ ውስጥ ስትገባ በቀኝ እግርህ መጀመር፣ ስትወጣ ደግሞ በግራ እግርህ መጀመርህ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው፡፡» ብለዋል፡፡ አል-ሐኪም በሐዲሥ ዘገባ መድብላቸው ቅጽ፡ 1 ገጽ፡ 338 ላይ ሲዘግቡ በሙስሊም የዘገባ መስፈርትነት የሐዲሡንም ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡


## 5 መስጂድ ሲገባካ ከመስጂድ ሲወጣ የሚባለውን ዘክር ማለት

اللّهُمَّ افْتَحْ لِي أَبْوَابَ رَحْمَتِكَ

اللّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ فَضْلِكَ

አቢ ሐሚድ ወይም አቢ ኡሰይድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ መስጂድ ከገባ፣ ‹‹አልላሁምመ ኢፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ፣››** /አላህ ሆይ! የምህረትህን በር ክፈትልኝ/ **ከወጣ ደግሞ ‹‹አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚን ፈድሊክ››** /አላህ ሆይ! ከችሮታህ እጠይቅሃለሁ፡፡/ ይበል፡፡” በለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (713) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 6 ሁለት ረከዐህ ተሒየቱ-ል-መስጂድ መስገድ አለበት፡፡



ይህ ለሰላቱ በጊዜ ከመጣ ነው፡፡ ከመጣም ሁለት ረከዐዎችን ሳይሰገድ መቀመጥ የለበትም፡፡ አቢ ቀታዳህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ መስጂድ ውስጥ ከገባ ሁለት ረከዐዎችን ሳይሰግድ አይቀመጥ፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1163)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (714) ላይ ዘግበውታል፡፡

እንደየአል-ፈጅር፣ አዝ-ዙህር ሰላቶች ከሰላቱ በፊት የሚሰገድ የሱንና ሰላት ካለ ፣ ወይም መስጂድ ውስጥ በጠዋት የአድ-ዱሓ ሰላት ለመስገድ የገባ ወይም ዊትርን ወይም ግዴታ የሆነን ሰላት መስጂድ ውስጥ ከሰገደ ለተሒየቱ-ል-መስጂድ በቂው ነው፡፡ ምክንያቱም የተሒየቱ-ል-መስጂድ ዓላማ፡- አንድ ሰው መስጂድ ከገባ በኋላ ሁለት ረከዐህ ሳይሰገድ እንዳይቀመጥና መሰጂድን በሰላት ማሳዋብና ከሰላት ውጭ መስጂድ እንዳይተው ነው፡፡

## 7 ለወንዶች በመጀመሪያው ሰልፍ ላይ መቻኮላቸው ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰልፍ በላጩ የሰላት ሰልፍ ነው፡፡ ለሴቶች በላጩ ሰልፍ ደግሞ የሰላቱ የመጨረሻ ሰልፍ ነው፡፡

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ከወንዶች ረድፎች መካከል በላጩ ረድፍ የመጀመሪያው ነው፡፡ መጥፎው ደግሞ የመጨረሻው ነው፡፡ ከሴቶች ረድፎች መካከል በላጩ ረድፍ የመጨረሻው ነው፡፡ መጥፎው ደግሞ የመጀመሪያው ነው፡፡”** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (440) ዘግበውታል፡፡ **በላጩ፡** - ማለት በርካታ ምንዳና ትሩፋትን የሚያስገኝ ማለት ሲሆን **መጥፎዋ፡** - ማለት ደግሞ ዝቅተኛ ምንዳና ትሩፋት የሚያስገኝ ማለት ነው፡፡

ይህ ሐዲሥ ወንዶችና ሴቶች ግርዶሽ በሌለበት ሁኔታ ሰላትን በሕብረት (ጀማዐህ) የሚሰግዱ ከሆነ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ለሴቶች የሰላቱ የመጨረሻ ረድፍ በላጭ ነው፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን ከወንድ ዓይኖች እንዲጠበቁ ምክንያት ይሆንላቸዋልና ነው፡፡ እንደግርግዳና ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ዓይነት ግርዶሽ ያለበት ሥፍራ ወይም ልክ ለሴቶች መስገጃ ይሆን ዘንድ ልዩ ክፍል እንደሚዘጋጅባቸው አብዛኛዎቹ መስጂዶቻችን ዓይነት ከሆነ ለሴቶች በላጩ ረድፍ የመጀመሪያው ነው፡፡ ይህም ከወንዶች እኩል ይሆኑ ዘንድ ለማስቻል ነው፡፡ በማንኛውም የመጀመሪያ የሰላት ረድፍን አስመልከቶ የተዘገቡ ሐዲሦች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነርሱም መካከል፡-

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሰዎች በአዛንና በመጀመሪያ ረድፍ ውስጥ ያለውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮና እሱ ላይ እጣ ከመጣጣል በስተቀር ሌላ የማያገኙ ቢሆን እጣ ይጣጣሉ ነበር፡፡ ሰዎች በመክፈቻው ተክቢራ ውስጥ ያለውን ቢያውቁ ኖሮ ወደርሱ ይሽቀዳደሙ ነበር፡፡ በምሽት -በዒሻእ- እና በሱብሒ ሰላቶች ውስጥ ያለውን ቢያውቁ ኖሮ እየዳሁም ቢሆን ይመጡ ነበር፡፡”** ብለዋል፡፡ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (615)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (437) ላይ ዘግበውታል፡፡


## 8 ኢማሙን ተከትሎ ለሚሰገድ ሰው ለኢማሙ ቀረብ ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደሳለፍነው ኢማሙን ተከትሎ ለሚሰግድ ሰው ለሰላቱ ተመራጩ ረድፍ የመጀመሪያው ረድፍ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ተከታዩ ለኢማሙ ቀረብ ለማለት መጣር ይኖርበታል፡፡ ለኢማሙ በቀኝ በኩልም ሆነ በግራ በኩል መሆን በላጭ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዐብዱላህ ኢብን መስዑድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ከናንተ መካከል የእውቀትና የአእምሮ ባሌቶች የሆኑ ይቅረቡኝ፡፡” ብለዋል፡፡ አቡ ዳዉድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (674)፣ አት-ቲርሚዚይ ደግሞ በቁጥር (228) ላይ ዘግበውታል፡፡ ይህ ሐዲሥ በማንኛውም አቅጣጫ በኩል ለኢማሙ ቅርብ መሆን ተፈላጊ ለመሆኑ ማስረጃ ነው፡፡

## በሰላት ውስጥ የሚገኙ ነቢያዊ ፈለጎች



መስጂድ ውስጥ በሕብረት ከመስገድ ወደኋለካ መቅረትህ በርካታ ትርፋቶችን ያስልጥሃል፣ እያንዳንዱ በሕብረት ለመስገድ ወደመስጂዱ መራመድህ በራሱ በአላህ ዘንድ ያለህን ደረጃ እጅጉን ከፍ ያደርግልሃል፣ ሃጢአቶችህም ይሰረዩልሃል፡፡

### ሰላት በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች ያሉት ሲሆን ከእነርሱ መካከል የሚከተሉትን እንጠቅሳለን፡-

### 1 ግርዶሽ፡- በዚህ ሥር የሚከተሉትን መፈጸም ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

### 1 ግርዶ ማድረግ

ግርዶሽ ማድረግ ለኢማም ሆነ ብቻውን ለሚሰግድ ሰው ነቢያዊ ፈለግ የሆነ ተግባር ነው፡፡ ተከታይ ለሆነ ሰው ግን የኢማሙ ግርዶሽ ለእሱም ግርዶሽ ነው፡፡ ግርዶሽ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

አቢ ሰዒይድ አል-ኹድሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ላይ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ከሰገደ ከሰዎች የሚከልለውን ግርዶሽ ያድርግ፡፡...”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (505) ላይ ዘግበውታል፡፡ ግርዶሽ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ በመሆኑ ላይ በርካታ ሐዲሦች ተዘግበዋል፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በአልጋ፣ በግርግዳ፣ በእንጨት፣ በጦር፣ በምርኩዝ፣ በእንስት ግመልና ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ግርዶ አድርገዋል፡፡

በቅጽር ውስጥም ሆነ አውላላ ሜዳ ላይ፣ በአንድ ስፍራ ላይ ዘውታሪ በመሆን ላይም ሆነ በጉዞ ላይ በመሆን፣ አንድ ከፊት ለፊ የሚያልፍን ሰው ፈራም አልፈራ ግርዶ ማድረግ ኢስላማዊ ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ሐዲሡ በቅጽር ውስጥ ሳሉም ሆነ አውላላ ሜዳ ላይ ሳሉ በሁለቱ መካከል

ልዩነትን አላሳደረም፡፡ምክንያቱም ጁሐይፈህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውንደ ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ላይ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በአንድ ሥፍራ ላይ ዝውታሪ ሳሉም ሆነ በጉዞ ላይ ሳሉ  ግርዶ ያደርጉ ነበር፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (501)፣ ሙስሊም በቁጥር (503) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 2 ወደግርዶው መጠጋቱ



ሰውየው ወደግርዶው ከተጠጋ፣ በግንባሩ መሬት ላይ በሚደፋበት ቦታና በግርዶው መካከል አንድ ፍየል የሚያሳልፍ መጠን ቦታ መኖሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ሰህል ኢብን ሰዕድ አስ-ሳዒዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «በአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- መስገጃና በግድግዳው መካከል አንዲት ፍየል የሚያሳልፍ ሥፍራ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (496)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (508) ላይ ዘግበውታል፡፡ በዚህ ሐዲሥ መስገጃቸው ላይ ማለት -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሱጁድ የሚያደርጉበት ሥፍራ ማለት ነው፡፡  በአሕመድና በአቢ ዳዉድ ዘገባ ደግሞ «በእሳቸውና በግርዶው መካከል ሶስት ክንድ ርዝመት ነበር፡፡» የሚል ተዘግቧል፡፡ አሕመድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6231)፣ አቢ ዳዉድ ደግሞ በቁጥር (2024) ላይ ዘግበውታል፡፡ አል-አልባኒም የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል (ሰሒሕ አቢ ዳዉድ ቅጽ ፡ 6 ገጽ ፡ 263)፡፡ የዚህ ሐዲሥ ምንጩ ቡኻሪ በቁጥር (506) ላይ የዘገቡት ሐዲሥ ነው፡፡ ይህም ፍየሏ ባትሄድና በመካከለቸው ያለው ርቀት ነው፡፡

## 3 ከሰጋጁ ፊት ለፊት የሚያልፍን ሰው መመለስ



አቢ ሰዒድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መለእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ **“አንዳችሁ ከሰገደ ከሰዎች የሚከልለውን ግርዶሽ ያድርግ፡፡ አንድ ሰውም በፊት ለፊቱ ለማለፍ ከፈለገ በአንድ ጎኑ ይከልክለው፡፡ እሻፈረኝ ካለ ይምታው፡፡ በርግጥ እርሱ ሸይጣን ነውና”** ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (505) ላይ ዘግበውታል፡፡

በሚሰግደው ሰው ፊት የምታልፈው ሴት ከሆነች ወይም ጥቁር ውሻ ወይም አህያ ከሆነ በትክክል ሊከለክላቸው ግድ ይላል፡፡ ምክንያቱም ከአቢ ዘር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተላለፈው ሐዲሥ ላይ ሰላት እንደሚያቋርጡ ሰፍሯል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (510) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 4 በእያንዳንዱ ሰላት መፋቂያ መጠቀም



ይህ መፋቂያ ዘውታሪ የሆነ ነቢያዊ ፈለግ መሆኑን የሚረጋገጥበት ሶስተኛ ቦታ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነቱና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ **"በሕዝቦቼ ወይም በሰዎች ላይ ማስቸገር ባይሆንብኝ ኖሮ በርግጥ ከእያንዳንዱ ሰላት ጋር በመፋቂያ ባዘዝኳቸው ነበር፡፡"** ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (887) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 2 ለሰላት በሚቆምበት ጊዜ የሚከተሉትን መፈጸም ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

### 1 በተክቢረተ-ል-ኢሕራም ላይ እጆችን ከፍ ማድረግ

سَمِعَ اللّٰهُ لمن حَمِده ربَّنا ولكَ الحمدُ



ኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላታቸውን ሲጀምሩ፣ ሩኩዕ ለማድረግ አላሁ አክበር ሲሉ እንዲሁም ከሩኩዕ ሲነሱ እጆቻቸውን እስከትከሻቸው ድረስ ከፍ ያደርጉ ነበር፡፡ ከሩኩዕ ሲነሱ፣ ***"ሰሚዐ-ልላሁ ሊመን ሐሚደህ ረብበና ወለከልሐምድ*** /አላህ የአመሰገኙን ምስጋና አዳመጠ፣ ጌታችን ሆይ! ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ /" ይሉ ነበር፡፡ ይህን ሱጁድ ላይ አይተገብሩም ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (735)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (390) ላይ ዘግበውታል፡፡

ኢብን ሁበይራህ -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «በተክቢረቱ-ል-ኢሕራም ወቅት እጆችን ማንሳት ነቢያዊ ፈለግ በመሆኑ ላይና ግዴታ ባለመሆኑ ላይ ዑለሞች ሀሣባቸውን አንድ አድርገዋል፡፡» አል-አፍሳሕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 123፡፡

ሐዲሥ የተዘገበባቸውና እጆች የሚነሱባቸው ሥፍራዎች አራት ናቸው፡፡ እነርሱም፡- በተክቢረተ-ል-ኢሕራም፣ በሩኩዕና ከረኩዕ በሚነሱበት ወቅት ናቸው፡፡ በእነዚህ ሥፍራዎች ላይ እጆችን ማንሳት በሳለፍነው የኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ትክክለኛ በሆነ የሐዲሥ ዘገባ ላይ ሰፍሯል፡፡ አራተኛው ሥፍራ፡- ከመጀመሪያው ተሸሁድ (አት-ተሒይያቱ ማለት) ሲነሱ ነው፡፡ ይህ በቡኻሪ በተዘገበው የኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ የጸና ነው፡፡

በሐዲሥ የተዘገቡት እጆች የሚነሱባቸው የሰላት ቦታዎች አራት ናቸው

የመክፈቻው ተክቢራህ ላይ

ረኩዕ ላይ

ከረኩው በመነሳት ላይ

እነዚህ ሶስቱ ከኢብን ዑመር -አላህ መልካምሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ከዚህ በፊት እንደተመለከተው በሁለቱ የሐዲሥ ዘገባዎች የተረጋገጡ ናቸው፡፡ አራተኛው ርዕስ፡-

ከመጀመሪያው ተሸሁድ (አት-ተሒያቱ) በሚነሱ ጊዜ

ይህ ከኢብን ዑመር -አላህ መልካምሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲሁ የተረጋገጠ በሆነው በሰሒሑ-ልቡኻሪ ዘገባ ውስጥ ሰፍሮ የሚገኝ ነው፡፡

## 2 እጆችን በሚያነሱበት ወቅት ጣቶችን ማራራቅ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ለሰላት ሲቆሙ እጃቸውን በመዘርጋት ከፍ ያደርጉ ነበር፡፡» አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (8875)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (753) እንዲሁም አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (240) ላይ ዘግበውታል፡፡ የሐዲሡን ትክክለኛነት አል-አልባኒይ አረጋግጠዋል፡፡ (ሰሒሑ አቢ ዳዉድ ቅጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 341)

## 3 እጆችን ነቢያዊ ፈለግ በሆነበት ሥፍራ ላይ ማድረግ

እጆችን ማንሳትን በተመለከተ ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የተዘገቡ ሐዲሦች በሁለት ዓይነት ሁኔታ ተዘግበዋል፡፡ ወደትከሻዎች አጠገብ ማንሳት ቡኻሪና ሙስሊም ከኢብነ ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ላይ ሰፍሯል፡፡ ቡኻረ ሐዲሡን በሐዲሥ ቁጥር (735)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (390) ላይ ዘግበውታል፡፡ ወደየጆሮዎች ጫፍም ማስጠጋት የሚለው ሙሰሊም ከ ማሊክ አቢን አል-ሑወይሪሥ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (391) ላይ ዘግበውታል፡፡ በዚህ መሰረትም ሰላት የሚሰግድ ሰው አንዳንድ ጊዜ የመጀመሪያውን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሌላኛው እየለያየ መፈጸም ይችላል፡፡





## 4 የሚሰግድ ሰው ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ ማድረጉ ነቢያ ፈለግ ነው፡፡

ኢብን ሁበይረህ እንዳሰፈሩት ይህ ሁኔታ የአብዛኛዎቹ ዑለሞች -አላህ ይዘንላቸው- ስምምነት ነው፡፡ አል-ኢፍሳሕ ቅጽ፡ 1 ገጽ ፡ 124፡፡

## 5 በቀኝ እጁ የግራ እጁን አጥብቆ መያዝ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**የመጀመሪያው ሁኔታ፡-** ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ ያስቀመጣል፡፡ ዋኢል ኢብን ሐጀር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላት ላይ ሲቆሙ በቀኝ እጃቸው የግራ እጃቸውን ሲይዙ ተመልክቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ አቡ ዳዉድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (755) እንዲሁም አን-ነሳኢይ በቁጥር (888) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይም ትክክለኛቱን አረጋግጠዋል፡፡

**ሁለተኛው ሁኔታ፡-** የቀኝ እጁን በግራ ክንዱ ላይ ያስቀምጣል፡፡ ሰህል ኢብን ሰዕድ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ሰዎች አንድ ሰው ሰላት ውስጥ ቀኝ እጁን በግራ ክንዱ ላይ እንዲያደርግ ይታዘዙ ነበር፡፡» ቡኻሪ ሐዲሡን ነሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (740) ላይ ዘገበውታል፡፡

በዚህ መሰረት የሚሰግደው ሰው ነቢያዊ ፈለጉን ለመከተል አንዳንድ ጊዜ ቀኝ እጁን በግራ እጁ ላይ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በግራ ክንዱ ላይ በማስቀመጥ እያቀያየረ መፈጸም ይችላል፡፡





## 6 የሰላት መክፈቻ ዱዓእ ማድረግ

የሰላት መክፈቻ ዱዓእ አገላለጽ የተለያየ ነው፡፡ ይህን ዱዓእ በተለያየ ሁኔታ ማለት የተወደደ ነው፡፡ በሐዲሥ ላይ ከተዘገቡ የሰላት መክፈቻ ዱዓእ መካከል፡-

1) سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ ، تَبَارَكَ اسْمُكَ وَتَعَالَى جَدُّكَ ، وَلاَ إِلَهَ غَيْرُكَ

**‹‹ሱብሓነከ-ልላለሁምመ ወቢሐምዲከ፣ ወተባረከ-ስሙከ፣ ወተዓላ ጀድዱከ ወላ ኢላሀ ገይሩከ፡፡**/ጠራት የተገባህ አላህ ሆይ! ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ ስምህም የተባረከ ነው፡፡ ክብርህም የላቀ ነው፡፡ በእርግጥ ካንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም፡፡ /›› አህመድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (11473)፣ አቡ ዳዉድ በቁትር (776)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (243) እንዲሁም አን-ነሳኢይ በቁጥር (900) ዘግበውታል፡፡ ሐዲሡ የሚጠናከርበት የተለያዩ መንገዶች ያሉ ሲሆን ኢብን ሐጀር የሐዲሡን በጥሩ ደረጃ መገኘት አረጋግጠዋል፡፡ (አል-አፍካር ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 412)፡፡

2 الْحَمْدُ لِلَّهِ حَمْداً كَثِيراً طَيِّباً مُبَارَكاً فِيهِ

**‹‹አል-ሐምዱ-ሊልላሂ ሐምደን ከሢይረን ጠይዩበን ሙባረከን ፊይሂ** /በርካታ፣ ያማረና በርከት ያለበት ምስጋና ለአላህ ነው፡፡/›› የዚህ ምስጋና ትሩፋት አስመልከተው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፣ **“ማናቸው ያነሷት ዘንድ አስራ ሁለት መላእክቶች ሲሽቀዳደሙባት በርግጥ ተመልክቻለሁ”** ሐዲሡን ሙስሊም ከአንስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (600) ዘግበውታል፡፡

3 اللَّهُمَّ بَاعِدْ بَيْنِي وَبَيْنَ خَطَايَايَ كَمَا بَاعَدْتَ بَيْنَ الْمَشْرِقِ وَالْمَغْرِبِ، اللَّهُمَّ نَقِّنِي مِنْ خَطَايَايَ كَمَا يُنَقَّى الثَّوْبُ الأَبْيَضُ مِنَ الدَّنَسِ، اللَّهُمَّ اغْسِلْنِي مِنْ خَطَايَايَ بِالثَّلْجِ وَالْمَاءِ وَالْبَرَدِ

**“አልላሁምመ ባዒድ በይኒ ወበይነ ኸጣያየ ከማ በዐድተ በይነ-ል-መሽሪቂ ወል-መግሪብ፡፡ አልላሁምመ ነቅቂኒ ሚን ኸጣያየ ከማ ዩነቀ አሥ-ሠውቡ-ል-አብየዱ ሚነ-ድደነስ፡፡ አልላሁምመ ኢግሲልኒ ሚን ኸጣያየ ቢሥሠልጂ ወል-ማኢል ወል-በረዲ፡፡** /አላህ ሆይ! በምስራቅና በምዕራብ እንዳራራቅከው በእኔና በሐጢአቶቼ መካከል አራርቅ፡፡ አላህ ሆይ! ነጭ ልብስ ከእድፍ እንደሚነጻ ሁሉ ከሐጢአቶቼ አንጻኝ፡፡ አላህ ሆይ! በበረዶ፣በውሃና በበቀቅ ከሐጢአቶቼ እጠበኝ፡፡/” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (744)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (598) ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

4 اللهُ أَكْبَرُ كَبِيراً ، وَالْحَمْدُ لِلَّهِ كَثِيراً ، وَسُبْحَانَ اللهِ بُكْرَةً وَأَصِيلاً

**“አለሁ አክበር ከቢራ፣ ወልሐምዱ ሊልላሂ ከሲይራ፣ ወሱበሓነ-ልላሂ ቡክረተን ወአሲይላ፡፡** /አላህ በእጅጉ መተለቅን ታላቅ ነው፡፡ በርካታ ምስጋና ለአላህ ይገባው፡፡ አላህ ዛሬም ምንጊዜም ከሚባለው ውድቅና የማይረባ ንግግር የጠራ ነው፡፡” የዚህን ዱዓእ ትሩፋት አስመልከተው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “በጣም ተደነቄላታለሁ፡፡ የሰማያት በሮች ተከፈቱላት፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (601) ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

## 7 ከሸይጣን ተንኮልና ጉትጎታ በአላህ መጠበቅ

ከሸይጣን ተንኮልና ጉትጎታ በአላህ መጠበቅ እንዲሁ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ የሚለው ሰው በተለያየ ጊዜ የተለያየውን አገላለጽ መጠቀምም እንዲሁ፡፡ ይህን አስመልክቶ ከተዘገቡት ሐዲሦች መካከል፡-

1 **“አዑዉዙ ቢልላሂ ሚነ-ሽሸይጣኒ-ርረጂይም፡፡** /ከተረገመው ሸይጣን በአላህ እጠበቃለሁ፡፡/”

ይህ አገላለጽ አብዛኛዎቹ ዑለሞች -አላህ ይዘንላቸው- የመረጡት አገላለጽ ነው፡፡ ይህንንም የመረጡበት አብይ ምክንያት፣ “ቁርአንንም ባንበብህ ጊዜ ርጉም ከኾነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ፡፡” (አን-ነሕል ፡ 98) በማለት የሰረፈውን የአላህ ቃል በመመርኮዝ ነው፡፡

2 **“አዑዉዙ ቢልላሂ-ስሰሚዒ-ል-ዐሊይሚ ሚነ-ሽሸይጣኒ-ርረጂይም፡፡** /ሰሚና ዐዋቂ በሆነው አላህ ከተረገመው ሸይጣን እጠበቃለሁ፡፡/”

ይህ፣ **“ከሰይጣንም ጉትጎታ ቢያገኝህ÷ (ከመልካም ጠባይም ቢመልስህ) በአላህ ተጠበቅ፤ እነሆ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና፡፡”** (ፉሲለት ፡ 36) ከሚለው የላቀው አላህ ቃል የተወሰደ ነው፡፡

## 8 በአላህ ሥም መጀመር

بِسْمِ اللَّهِ الرَّحْمنِ الرَّحِيمِ

ከሸይጣን በአላህ ከተጠበቁ በኋላ አንድ ሰው በአላህ ሥም የቁርኣን ንባቡን መጀመሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ እንዲህም ይላል፣ **‹‹ቢስሚ-ልላሂ-ርረሕማኒ-ርረሒይም፡፡** /በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡/»፡፡ ይህ ከነዒም አል-ሙጅመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ከተወራ ሐዲሥ የተወሰደ ነው፡፡ በዚህ ሐዲሥ ላይ ነዒም እንዲህ ብለዋል፣ «ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ኋላ ሰገድኩኝ፡፡ **“ቢስሚ-ልላሂ-ርረሕማኒ-ርረሒይም፡፡”**ን አነበቡ፡፡ ከዚያ የአል-ፋቲሐን ምዕራፍ አነበቡ፡፡» በዚሁ ሐዲሥ ላይም፣ «ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! የአላህ መልእክተኛን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላት አስመስልላችኋላሁ፡፡» ብለዋል፡፡ አን-ነሳኢይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (906) እንዲሁም ኢብን ኹዘይመህ የዘገቡት ሲሆን ትክክለኛነቱንም አረጋግጠዋል (ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 251)፡፡ አድ-ዳሩ-ል-ቁጥኒይ፣ «ይህ ትክክለኛ ሐዲሥ ነው፣ አስተላላፊዎቹም ሁሉም ተማኞች ናቸው፡፡» ብለዋል (አስ-ሱነን ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 46)፡፡

ግዴታ ከመሆን የሚያርቀው ደግሞ ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላቱን ላበላሸው ሰው ይህን እንዲል አላስተማሩትም፡፡ በአንጻሩ ወደመጽሐፉ የመክፈቻ ምዕራፍ ነበር ያመላከቱት፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (757) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር (397) ዘግበውታል፡፡

## 9 ከኢማም ጋር ኣሚን ማለት፡፡

ይህም ኢማሙን ድምጹን ይፋ አድርጎ የአል-ፋቲሐን ምዕራፍ ያነበበ( (የቀራ) ከሆነ ኢማሙ ኣሚን ካለ ተከታዩም ኣሚን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህም አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ኢማሙ ኣሚን ካለ ኣሚን በሉ፡፡ በርግጥ ኣሚን ማለቱ ከመላእክት ኣሚን ማለት ጋር የተገጣጠመለት ሰው ካሳለፈው ወንጀሎቹ ተምሮለታል፡፡” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (780) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር (410) ዘግበውታል፡፡

## 10 ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ በኋላ አንድ የቁርአን ምዕራፍ ማንበብ

በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዐዎች ላይ ማንበቡ ነቢያዊ ፈለግ ነው የሚለው የአብዛኛዎቹ ዑለሞች -አላህ ይዘንላቸው- ሃሳብ ነው፡፡ አቢ ቀታዳህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝንታና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በአዝ-ዙህር ሰላት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዐዎች ላይ የአል-ፋቲሐን ምዕራፍና ሌሎች ሁለት ምዕራፎችን ያነቡ ነበር፡፡ የመጀመሪያውን ያስረዝሙ የነበር ሲሆን በሁለተኛው ላይ ያሳጥሩ ነበር፡፡» ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (759) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር (451) ዘግበውታል፡፡

ድምጽ ይፋ ሆኖ በሚነበብባቸው ሰላቶች ተከታይ የሆነ ሰው ከአል-ፋተሐ በኋላ ያለውን ምዕራፍን አያነብም፡፡ ዝም ብሎ የኢማሙን ንባብ ያዳምጣል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (756) እንዲሁም ሙስሊም በቁጥር (394) ዘግበውታል፡፡

ኢብን ቁዳመህ -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «በመጀመሪያዎቹ ሁለት ረከዐዎች ላይ ከአል-ፋቲሐ ምዕራፍ በኋላ አንድ የቁርኣን ምዕራፍን ማንበብ ነቢያዊ ፈለግ በመሆኑ ላይ በዑለሞች መካከል የሃሳብ ልዩነት መኖሩን አናውቅም።» አል-ሙግኒ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 568።

## 〈3〉 በሩኩዕ ላይ የሚከተሉትን ነቢያዊ ፈለጎች መፈጸም ተገቢ ነው።

### 1 በሁለቱ መዳፎች ጉልበትን እንደሚይዝ አድርጎ ጉልበትን በመያዝ፣ ጣቶችንም በማራራቅ ሁለቱን መዳፎች ጉልበት ላይ ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው።



አቢ ሑመይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «የአላህ መልእክተኛን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላት በማወቅ ከናንተ የበለጥኩ ነበርኩ። ተክቢራህ ሲያደርጉ እጆቻቸውን ወደትከሻቸው ላይ ያስጠጉ እንደነበር፣ ሩኩዕ በሚያደርጉበት ወቅት እጆቻቸውን በጉልበቶቻቸው ላይ ያደላድሉ እንደነበር፣ ከዚያ ወገባቸውን ቀጥ ያደርጉ እንደነበር ተመልክቻቸዋለሁ።...» ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ላይ ዘገበውታል። በአቢ ሰዒይድ -አላህ መልካም ሥረዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተወራው ሐዲሥ፣ «ጉልበታቸው ላይ ጣቶቻቸውን አራርቀው ነበር።...» ብለዋል። ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (17081)፣ አቢ ዳዉድ በቁጥር (683)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (1038) በጥሩ የዘገባ ሰንሰለት ዘግበውታል። ለዚህ ሐዲሥም ኢብን ኹዘያመህ በቁጥር (594) ላይ ከዋኢል ኢብን ሐጀር የዘገቡት ሐዲሥ ደጋፊ ማስረጃው ነው።

### 2 ሩኩዕ የሚያደርግ ሰው ወገቡን ቀጥ አድርጎ መዘርጋቱ ነቢያዊ ፈልግ ነው።



አቢ ሑመይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ረኩዕ ሲያደርጉ እጆቻቸውን ከጉልበታቸው ጋር ያደላድሉ ነበር። ከዚያ ወገባቸውን ቀጥ አድርገው ይዘረጉ ነበር።...» ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ላይ ዘግበውታል። ረኩዕ የሚያደርግ ሰው ራሱ ራሰ አፈጣጠር ጋር እኩል ወጥ መሆን አለበት። ከፍ ማድረግም ሆነ ዝቅ ማድረግ የለበትም። ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ረኩዕ በእንዲህ ሁኔታ ገልጸዋል። ሐዲሡንም ሙስሊም ዘግበውታል።

«ረኩዕ ሲያደርጉ ራሳቸውን ከፍ አያደርጉም እንዲሁም በጣም ዝቅ አያደርጉም። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ያደርጉ ነበር።» ብለዋል። ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (498) ላይ ዘግበውታል።

### 3 ሩኩዕ የሚያደርግ ሰው ረኩዕ ላይ ክርኖቹን ከጎኖቹ ማራራቁ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



ከዚህ በላይ ባሳለፍነው ከአቢ መስዑድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተዘገበው ሐዲሥ ውስጥ፣ ‹‹ከዚያ ረኩዕ ያደርጋሉ እጆቻቸውን ያራርቃሉ፡፡ እጆቻቸውን በጉልበታቸው ላይ ያደርጋሉ፡፡ በጣቶቻቸውም መካከል ያራርቃሉ፡፡...›› ካሉ በኋላ፣ ‹‹የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በእንዲህ መልክ ይሰግዱ ነበር፡፡›› ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (17081)፣ አቢ ዳዉድ በቁጥር (863)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (1038) ላይ ዘግበውታል፡፡ ከዚህ በላይ በተራ ቁጥር 2 ላይ የሰፈረውን ይመልከቱ፡፡

ከጎኑ ያለውን ሰው እስካላስቸገረ ድረስ በሚል መስፈርት ረኩዕ ላይ እጆችን ከጎኖች ማራራቅ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ አንድ የሚሰግድ ሰው ነቢያዊ ፈለግ በሆነ ተግባር ሌላ የሚሰግድ ሰውን ማስቸገር የለበትም፡፡

ኢማም አን-ነወዊይ -አላህ ይዘንላቸው- ረኩዕ ላይ እጆችን ከጎኖች ማራራቅን በተመለከተ፣ ‹‹በወመደዱ ላይ ከአንድ ዓሊም በስተቀር በሌሎች ዑለሞች ዘንድ የሃሳብ ልዩነት አላውቅም፡፡ አት-ቲርሚዚይ የዚህን ተግባር በሩኩዕና በሱጁድ ላይ መወደድን በተመለከተ ከዑለሞች አስተላልፈዋል፡፡›› አል-መጅሙዕ ቅጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 410፡፡

### 4 ረኩዕ የሚደርገው ሰው በረኩዕ ላይ የሚባሉ ዚክሮችን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**سبحان ربي العظيم**

ረኩዕ ላይ **“ሱብሓነ ረብቢየ-ል-ዐዚይም፡፡** /እጅግ የላቀው ጌታዬ ከሚባሉት ከንቱና ውድቅ የሆኑ ንግግሮች ጠራ/” የሚለውን ዚክር በቅድሚያ ማለት አለበት፡፡ ከዚህ ሌላ ሩኩዕ ላይ የሚባሉ በርካታ አዝካሮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከልም፡-

1. **سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ، اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي**

   **“ሱብሓነከ-ልላሁምመ ወቢሐምዲከ አልላሁምመ ኢግፊር ሊ፡፡** /ከሚባሉት ከንቱና ውድቅ ንግግሮች የጠራህ የሆንከው አላህ ሆይ! ጌታችን ነህ፡፡ ምስጋናም ላንተ ነው፡፡ አላህ ሆይ! ሐጢአቶቼን ማርልኝ፡፡/” ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (794)፣ ሙስሊም በቁጥር (484) ከዓኢሻህ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2. **سُبُّوحٌ قُدُّوسٌ رَبُّ الْمَلاَئِكَةِ وَالرُّوحِ**

   **“ሱብቡሑን ቁድዱሱን ረብቡ-ል-መላኢከቲ ወርሩሕ፡፡** /ከሚባሉት ከንቱና ውድቅ ንግግሮች እጅጉን የጠራ ነው፡፡ እጅግ የተቀደሰም ነው፡፡ የመላእክትና የጅብሪል ጌታ ነው፡፡/” ከዓኢሻህ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን* ይውደድላቸው- ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (487) ዘግበውታል፡፡

3. **اللَّهُمَّ لَكَ رَكَعْتُ ، وَبِكَ آمَنْتُ ، وَلَكَ أَسْلَمْتُ ، خَشَعَ لَكَ سَمْعِي، وَبَصَرِي ، وَمُخِّي ، وَعَظْمِي ، وَعَصَبِي**

**“አልላሁምመ ለከ ረከዕቱ ወቢከ ኣመንቱ ወለከ አስለምቱ ኸሸዐ ለከ ሰምዒ ወበሰሪ ወሙኸኺ ወዐዝሚ ወዐሰቢ፡ ፡** /አላህ ሆይ! ላንተ አጎነበስኩ፣ ባንተም አመንኩ፣ ላንተም እጅ ሰጠሁ፣ ማድመጫያዬ፣ መመልከቻዬ፣ አንጎሌ፣ አጥንቴ፣ ነርቬ ላንተ ተመሰጠ፡ ፡/” ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (771) ዘግበውታል፡፡

4 **سبحانَ ذِي الجَبَرُوتِ وَالمَلَكوتِ وَالكِبْرِياءِ وَالعَظَمَة**

**“ሱብሓነ ዚልጀበሩዉቲ ወልመለኩቲ ወልኪብሪያኢ ወልዐዘመህ፡ ፡** /የክብር፣ የንግስና የኩራት ባለቤት የሆነው አላህ ከሚባሉት ከንቱና ውድቅ ንግግሮች በእጅጉ ጠራ፡፡/” ሐዲሡን አቢ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (873) እንዲሁም አን-ነሳኢይ በቁጥር (1050) ከዐውፍ ኢብን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል (ሰሒሕ አቢ ዳዉድ ቅጽ ፡ 4 ገጽ ፡ 27)፡፡

## 4 ከሩኩዕ መነሳት፤ በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ፡ ፡

### 1 ይህን የሰላት ሩኩን (መሠረት፣ አምድ) ማስረዘም፡ ፡

ሣቢት አል-ቢናኒይ ከአነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት አነስ እንዲህ ብለዋል፣ ‹‹የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሲያሰግዱን እንዳየሁት እናንተን ከማሰገድ ፈጽሞ አላጓድልም፡፡›› ሣቢት አል-ቢናኒይ፣ ‹‹እናንተ ስትፈጽሙት ያላየሁትን አንዳች ተግባር አነስ ይፈጽሙ ነበር፡፡ ራሳቸው ከሩኩዕ ሲያነሱ ካደረጉ በኋላ ያያቸው ሰው፣ “ረስተው ነውን?” እስኪል ድረስ ጸጥ ብለው ይቆሙ ነበር፡፡ ከሱጁድ ራሳቸው ሲያነሱ እንዲሁ ያያቸው ሰው፣ “ረስተው ነውን?” እስኪልብዙ ይቆዩ ነበር፡፡›› ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (821)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (472) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 2 ረብበና ወለከልሐምድ የሚለውን አገላለጽ በሚከተለው አኳኋን መለያየት፡ ፡

1 **اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ**

**“አልላሁምመ ረብበና ወለከልሐምድ፡ ፡** / አላህ ሆይ! ጌታችን አንተ ነህ፡፡ ምስጋናም ላንተ ነው፡ ፡/” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (795) ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡



2 **اللَّهُمَّ رَبَّنَا لَكَ الْحَمْدُ**

**“አልላሁምመ ረብበና ለከልሐመድ፡ ፡/** አላህ ሆይ! ጌታችን አንተ ነህ፡፡ ምሰጋና ላንተ ነው፡፡/” ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (796)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (404) ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

3 رَبَّنَا وَلَكَ الْحَمْدُ

**“ረብበና ወለከልሐምድ፡፡** /ጌታችን ሆይ! ምስጋናም ላንተ ነው፡፡/” ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (799)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (411) ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

4 رَبَّنَا لَكَ الْحَمْدُ

**“ረብበና ለከልሐመድ፡፡** /ጌታችን ሆይ! ምስጋና ላንተ ነው፡፡/” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (722) ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

የሚሰግደው ሰው አንዳድ ጊዜ አንዱን ሌላ ጊዜ ደግሞ ከሌላው ማለት ይችላል፡፡

## 3 ከሩኩዕ ከተነሱ በኋላ የሚባሉ ነቢያዊ ፈለጎችን ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ከረኩዕ ከተነሱ በኋላ ከሚባሉ ዚክሮች መካከል የሚከተሉትን ለአብነት፦

1 رَبَّنَا لَكَ الْحَمْدُ ، مِلْءُ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ ، وَمِلْءُ مَا شِئْتَ مِنْ شَيْءٍ بَعْدُ ، أَهْلُ الثَّنَاءِ وَالْمَجْدِ، أَحَقُّ مَا قَالَ الْعَبْدُ ، وَكُلُّنَا لَكَ عَبْدٌ ، اللَّهُمَّ لاَ مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ ، وَلاَ مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ ، وَلاَ يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ

**“ረብበና ለከልሐምድ፣ ሚልኡ-ስሰማዋቲ ወልአርዲ፣ ወሚልአ ማሺእተ ሚን ሸይኢን በዕድ፣ አህሉ-ሥሠናኢ ወልመጅድ፣ አሐቅቁ ማ ቃለልዐብድ፣ ወኩልሉና ለከልዐብድ፣ አልላሁምመ ላ ማኒዐ ሊማ አዕጠይት፣ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕት፣ ወላ የነፌዑ ዛልጀድዲ ሚንከልጀድ፡፡** /ጌታችን ሆይ! ምስጋና ላንተ ነው፡፡ የሰማይንና የምድርን ሙሉ፣ ካንዳች ነገር በኋላ የሻትከውን ሙሉ፣ አንተ የውዳሴና የክብር ባለቤት ነህ፡፡ ባሪያው ያለው እውነት ነው፡፡ ሁላችንም ላንተ ባሮች ነን፡፡ አላህ ሆይ! ለሰጠኸው ሰው ከልካይ የለም፡፡ ለከለከልከውም ሰው ሰጪ የለም፡፡ የችሮታ ባለቤት ካንተ ይበልጥ አይጠቅምም፡፡” ሐዲሡን ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (477) ከአቢ ሰዒይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2 الْحَمْدُ لِلَّهِ حَمْداً كَثِيراً طَيِّباً مُبَارَكاً فِيهِ

**“አል-ሐምዱሊልላሂ ሐምደን ከሢይረን ጠይዩበን ሙባረከን ፊይሂ፡፡** /በውስጡ መልካምና የተባረከ ያለበት በርከት ያለ ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡/” ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይህን ዚክር አስመልተው፣ “አስራ ሁለት መላእክቶች የትኛው ያንሳት በሚለው ላይ ሲሽቀዳደሙ በርግጥ አይቻለሁ፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (799)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (600) ዘግበውታል፡፡

3 اللَّهُمَّ طَهِّرْنِي بِالثَّلْجِ وَالْبَرَدِ وَالْمَاءِ الْبَارِدِ ، اللَّهُمَّ طَهِّرْنِي مِنَ الذُّنُوبِ وَالْخَطَايَا كَمَا يُنَقَّى الثَّوْبُ الأَبْيَضُ مِنَ الْوَسَخِ

**“አልላሁምመ ጠህሂርኒ ቢሥሠልጂ ወልበረዲ ወልማኢ-ልባሪድ፡፡ አልላሁምመ ጠህሂርኒ ሚነ-ዝዙኑዉቢ ወልኸጣያ ከማ ዩነቃ-ሥሠውቡ-ል-አብየዱ ሚነ-ወሰኺ፡፡** /አላህ ሆይ! በበረዶ፣ በበቀቅና በቀዝቃዛ ውሃ አንጻኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከወንጀሎችና ከሐጢአት ልክ ነጭ ልብስ ከቆሻሻ እንደሚነጻው አንጻኝ፡፡/”ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (476) ዘግበውታል፡፡

አንድ ሙስሊም እነዚህን አዝካሮች ከሩኩዕ ከተነሳ በኋላ የሚል ከሆነ ይህ የሰላት አምድ (አርካን) ማርዘም ይችላል፡፡

## 〈5〉 ሱጁድ፡- በውስጡ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉ፡፡

### 1 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው ክርኖቹን ከጎኖቹ እንዲሁም ሆዱን ከጭኖቹ ማራራቁ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



ዐብዱላህ ኢብን ቡሐይነህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሲሰግዱ የብብታቸው ንጣት እስከሚታይ ድረስ በእጆቻቸውን መካከል ያራርቁ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (390)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (495) ላይ ዘግበውታል፡፡ መይሙነህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሱጁድ ሲያደርጉ አንዲት የበግ ወይም የፍየል ግልገል ለማለፍ ብትፈልግ በእጆቻቸው መካከል ታልፋለች፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (496) ዘግበውታል፡፡ ይህ በሁለት እጆች መካከል በማራራቅ ላይ ማጋነን ያሳያል፡፡ ነቢያዊ ፈለጉ ከጎን ያለን ሰው በማያስቸግር መጠን ልክ ረኩዕ ላይ እንደሚራራቀው ዓይነት ማራራቅ ነው፡፡

ከነቢያዊ ፈለጎች መካከልም ሱጁድ የሚያደርገው ሰው በጭኖቹ መካከል ማራራቅ አለበት፡፡ አንድ ላይ ማታጋጋት የለበትም፡፡ እንዲሁም ሆዱን በጭኖቹ አንዳች አካል ላይ ማሳረፍ አይኖርበትም፡፡ አቢ ሑመይድ -አላም መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የአላህ መልእክተኛን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የሰላት አሰጋገድ ሲገልጹ፣ «ሱጁድ ሲያደርጉ ሆዳቸውን በጭናቸው አንድም ስፍራ ላይ ሳያሳርፉ ጭኖቻቸውን ያራርቁ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ አቢ ደዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (735) ላይ ዘግበውታል፡፡ አሽ-ሸውካኒና ሌሎችም እንዳሰፈሩት ይህ ተግባር ነቢያዊ ፈለግ በመሆኑ ላይ ዑለሞች ተስማምተዋል፡፡

አሽ-ሸውካኒይ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ይህ ሐዲሥ ሱጁድ ላይ በጭኖች መካከል ማራራቅና ሆድን ከጭኖች ላይ ማንሳት ሸሪዐዊ ድንጋጌ መሆኑን ያመላክታል፡፡ በዚህ ላይ የዑለሞች የሃሳብ ልዩነት የለም፡፡» ብለዋል፡፡ (ነይሉ-ል-አውጣር ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 257)፡፡

### 2 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው የእግሮቹን ጣቶች ወደቂብላህ አቅጣጫ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



አቢ ሑመይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «የአላህ መልእክተኛን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላትን በማጥናት ከእናንተ የበለጥኩ

ነኝ፡፡» ካሉ በኋላ፣ «ሰጁድ ሲያደርጉ እጃቸውን የተደላለደሉ አሊያም የሰበሰቡ ሳይሆኑ መሬት ላይ ያስቀምጡ ነበር፡፡ በእግሮቻቸውን ጣቶች ጫፍ ደግሞ ወደቂብላህ አቅጣጫ ይቆሙ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሱጁድ ላይ የእጅ ጣቶችን በተመለከተ ነቢየዊ ፈለግ የሆነው ሱጁድ የሚያደርገው ሰው እጆችን ወደቂብላህ አቅጣጫ ማስቀመጥ ነው፡፡ በኢማም ማሊክ ሙወጣእ የተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ ይህ ነቢያዊ ፈለግ የሆነ ተግባር ከኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ጸንቷል፡፡ በአቢ ሸይበህ ዘገባ ደግሞ ከሐፍስ ኢብን ዓሲም -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «አንድ ሰው ሰላት ውስጥ መዳፎቹን ዘርግቶ፣ ጣቶቹን ሰብስቦና ወደቂብላህ አቅጣጫ ማዞር ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው፡፡» የሚል ተዘግቧል፡፡ ሙሰንነፍ አቢ ሸይበህ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 236፡፡ ዋኢል ኢብን ሐጀር፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሱጁድ ሲያደርጉ ጣቶቻቸውን አንድ ላይ ይሰበስቡ ነበር፡፡» በማለት የተናገሩት ይህን ሐዲሥ ያጠናክራል፡፡ የሐዲሡን ደረጃ አል-ሀይሠሚይ በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡ (መጅሙዑ-ዝዘዋኢድ ቅጽ፡ 2 ገጽ ፡ 135)

### 3 ሱጁድ የሚያደርግ ሰው ነቢያዊ ፈለግ የሆነ አዝካሮችን ሱጁድ ላይ ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡ ፡

**سبحان ربي الأعلى**

ሱጁድ የሚያደርግ ሰው "ሱብሓነ ረብቢየ-ል-አዕላ /እጅግ የላቀው ጌታዬ ከሚነገሩት ውድቅና ከንቱ ንግግሮች ጠራ/" ከማለቱ ጋር ሌሎች ሱጁድ ላይ የሚደረጉና ነቢያ ፈለግ መሰረት ያላቸውን አዝካሮችን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ከእነዚህ ነቢያዊ መሰረት ያላቸው አዝካሮች መካከል፡-

1. **سُبْحَانَكَ اللَّهُمَّ رَبَّنَا وَبِحَمْدِكَ، اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي**

**"ሱብሓነከ-ልላሁምመ ረብበና ወቢሐምዲከ አልላሁምመ ኢግፊር ሊ፡ ፡**/ ከሚነገሩት ውድቅና ከንቱ ንግግሮች አላህ ሆይ በእጅጉ የጠራኸው ፡፡ ጌታችንም ነህ፡፡ ምስጋንም ላንተ ነው፡፡ አላህ ሆይ ወንጀሎቼን ማርልኝ፡፡/" ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (794)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (484) ላይ ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2. **سُبُّوحٌ قُدُّوسٌ رَبُّ الْمَلَائِكَةِ وَالرُّوحِ**

**"ሱብቡሑን ቁደድዱሱን ረብቡ-ል-መላኢከቲ ወርሩሕ፡ ፡** /ከሚነገሩት ውድቅና ከንቱ ንግግሮች በእጅጉ የጠራ ነው፡፡ በእጅጉም የተቀደሰ ነው፡፡ የመላእክትና የጅብሪል ጌታ ነው፡፡/" ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (487) ላይ ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

3. **اللَّهُمَّ لَكَ سَجَدْتُ ، وَبِكَ آمَنْتُ ، وَلَكَ أَسْلَمْتُ ، سَجَدَ وَجْهِي لِلَّذِي خَلَقَهُ وَصَوَّرَهُ، وَشَقَّ سَمْعَهُ وَبَصَرَهُ، تَبَارَكَ الله أَحْسَنُ الْخَالِقِينَ**

**"አልላሁምመ ለከ ሰጀድቱ፣ ወቢከ አምንቱ፣ ወለከአስለምቱ፣ ሰጀደ ወጅሂ ሊልለዚይ ኸለቀሁ ወሰውወረሁ ወሸቅቀ ሰምዐሁ ወበሰረሁ ተባረከ-ልላሁ አሕሰኑ-ልኻለኪቂይን፡ ፡** /አላህ ሆይ! ላንተ በግንባሬ ተደፋሁ፤ ባንተም አምንኩ፤ ላንተም

እጅ ሰጠሁ፤ ፊቴ ለዚያ ለፈጠረው ላስተካከለው፣ መስሚያውንና ማያውን ለሰነጠቀው ጌታ ሱጁድ አደረገ። ከሰአሊዎች ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።/" ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (771) ከዐሊይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል።

4 اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ذَنْبِي كُلَّهُ دِقَّهُ وَجِلَّهُ ، وَأَوَّلَهُ وَآخِرَهُ، وَعَلَانِيَتَهُ وَسِرَّهُ

**"አልላሁም ኢግፊር ሊ ዘንቢ ኩልለሁ ዲቅቀሁ ወጂልለሁ ወአውወለሁ ወኣኺረሁ ወዐላኒይየተሁ ወሲርረሁ።** /አላህ ሆይ! በጣም ኢምንቱንም፣ ትልቁንም፣ መጀመሪያውንም፣ መጨረሻውንም፣ ይፋውንም፣ ድብቁንም ወንጀሌን ባጠቃላይ ማርልኝ።" ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (483) ላይ ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል።

5 اللَّهُمَّ أَعُوذُ بِرِضَاكَ مِنْ سَخَطِكَ ، وَبِمُعَافَاتِكَ مِنْ عُقُوبَتِكَ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْكَ ، لَا أُحْصِي ثَنَاءً عَلَيْكَ ، أَنْتَ كَمَا أَثْنَيْتَ عَلَى نَفْسِكَ

سبحان ربي العظيم

سبحان ربي الأعلى

**"አልላሁምመ አዑዙ በሪዳከ ሚን ሰኸጢክ፣ ወቢሙዓፋቲከ ሚን ዑቁዉበቲክ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚንክ፣ ላ ኡሕሲ ሠናአን ዐለይክ አንተ ከማአሥነይተ ዐላ ነፍሲክ።** /አላህ ሆ! በመልካም ፍላጎትህ ከቁጣህ እጠበቃለሁ። በይቅር ባይነተህ ከቅጣትህ እንጠበቃለሁ። ባንተም ካንተ እጠበቃለሁ። አንተ ባራስህ ላይ እንዳወርድከው ውዳሴ ማወደስን ላወድስ ፈጽሞ አልዘልቅም።/" ይህ ሐዲሥ ከዓኢሻ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ተዘግቧል። ከነዚህ አዝካሮች መካከል የቻለውን ያህል ሱጁድ ላይ ማለቱና ማለያየቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው። እንደሚታወቀው ረኩዕ ላይ ግዴታው አንድ ጊዜ ብቻ፣ **"ሱብሓነ ረብቢየ-ል-ዐዚይም"** ማለት ሲሆን ከዚያ በላይ መጨመር ነቢያዊ ፈለግ ነው። በሱጁድ ላይ እንዲሁ፣ **"ሱብሓነ ረብቢየ-ል-አዕላ"** አንድ ጊዜ ማለት ግዴታ ሲሆን ሁለተኛውና ሶስተኛው ነቢያዊ ፈለግ ነው።

## 4 ሱጁድ ላይ ደዓእን ማብዛት ነቢያ ፈለግ ነው።



ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸሰው ላይ ይሁን-፣ "ሰጁድ ደግሞ በእሱ ላይ በዱዓእ ታገሉ። ዱዓችሁ ምላሽ ያገኝ ዘንድ።እርሱ ዱዓእ ተቀባይነትን የሚገኝበት ነውና።" ብለዋል። ሐዲሡን ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (479) ላይ ዘግበውታል።

## 6 በሁለት ሱጁዶች መካከል ባለው መቀመጥ ላይ ያሉ ነቢያዊ ፈለጎች፡፡

### 1 አንድ የሚሰግድ ሰው በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ለማረፍ ሲቀመጥ ግራ እግሩን በማንጠፍ በእሱ ላይ መቀመጡና የቀኝ እግሩን ደግሞ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



አቢ ሑመይድ አስ-ሳዒዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ፣ «በሁለቱ ረከዐዎች ሲቀመጡ በግራ እግራቸው ላይ ይቀመጡና ቀኝ እግራቸውን ቀጥ አድርገው ያቆሙ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 2 ይህን የሰላት አምድ (መሰረት) ማርዘም፡፡

ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የሣቢት አል-ቢናኒይ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ላይ ይህ ሁኔታ ሥፍሯል፡፡

### 3 ለሁለተኛ ወይም ለሶስተኛው ወይም ለአራተኛው ረከዐህ መነሳት የፈለገ ከመነሳቱ በፊት ቀለል ያለ መቀመጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ይህ ቀለል ያለ መቀመጥ **“የርፍት መቀመጥ”** በሚል ስያሜ ይታወቃል፡፡ ለዚህ የርፍት መቀመጥ ምንም ዓይነት አዝካር የለውም፡፡

ይህ ነቢያዊ ፈለግ በሶሰት ሐዲሦች ጸንቷል፡፡ ከእነርሱ መካከልም፡-

ማሊክ አል-ሑወይሪሥ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን- በዊትር ሰላታቸው ውስጥ ሳሉ በደንብ ተደላድለው ሳይቀመጡ እንደማይቆሙ በርግጥ ተመልከተዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (823) ላይ ዘግበውታል፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **“ስሰግድ እንዳያችሁት አድርጋችሁ ስገዱ፡፡”** በማለት የተናገሩትን ሐዲሥ ማሊክ አል-ሑወይሪሥ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ያስተላለፉት ናቸው፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (631) ላይ ዘግበውታል፡፡

በ«ረፍት መቀመጥ» ነቢያዊ ፈለግ መሆን ላይ ዑለሞች በሃሳብ ተለያይተዋል፡፡ ትክክለኛ ግን ነቢያዊ ፈለግ ነው የሚለው ነው፡፡ ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የማሊክ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ያስተላለፉት ሐዲሥ መሰረት ነው፡፡ ነቢያዊ ፈለግ መሆኑን ይበልጥ ከተቀበሉት መካከል፡- አን-ነወዊይ፣ ኢብን ባዝ፣ አል-አልባኒይ -አላህ ይዘንላቸው-፣ ለጅነቱ-ድዳኢመህ ሊልሁሒ-ል-ዒልሚይየህ ወልኢፍታእ ይገኛሉ፡፡ ፈታዋ ወመቃላት ሙተነዊዐህ ቅጽ ፡ 11 ገጽ ፡ 99፣ ፈታዋ አል-ለጅኑ-ድዳኢመህ ቅጽ ፡ 6 ገጽ ፡ 445 – 446፡፡

አን-ነወዊ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ይህ በትክክለኛ ሐዲሦች የተረጋገጠ ነው፡፡» አል-መጅሙዕ ቅጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 441፡፡

## 〈7〉 ተሸሁድ ውስጥ ያሉ ነቢያዊ ፈለጎች፡-

### 1 የሚሰግደው ሰው ተሸሁድ ላይ ግራ እግሩን ማንጠፉ፤ ቀኝ እግሩን ደግሞ ቀጥ አድርጎ ማቆሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



አንድ የሚሰግድ ሰው ሁለት ወይም ሶስት ወይም አራት ረከዐዎችን ይስገድ ሁለተኛውን ረከዐህ ከሰገድ በኋላ ለተሸሁድ ሲቀመጥ አቀማመጡ በእንዲህ ዓይነት ነው፡፡ ይህም አቢ ሑመይድ አስ-ሳዒይዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ፣ «በሁለቱ ረከዐዎች ላይ ሲቀመጡ በግራ እግራቸው ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ቀኝ እግራቸውንም ቀጥ አድርገው ያቆሙ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ዘግበውታል፡፡ ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «በየሁለቱ ረከዐዎች አት-ተሒይያቱን ይሉ ነበር፡፡ ግራ እግራቸውን አንጠፈው ቀኝ እግራቸውን ቀጥ አድርገው ያቆሙ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (498) ዘግበውታል፡፡

በባለ ሶስትና አራት ረከዐ ሰላቶች ላይ ያለውን የመጨረሻ ተሸሁድ አስመልክቶ የሰፈረውን አገላለጽ ወደፊት እንመለከተዋለን፡፡

### 2 የሚሰግድ ሰው በተሸሁድ ላይ የእጆቹን የአቀማመጥ ሁኔታ መቀያየሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

በተሸሁድ ላይ መዳፎችን ማስቀመጥ ሁለት ዓይነት መገለጫዎች አሉት፡፡ እነርሱም፡-

**አንደኛ፡-** መዳፎችን በጭኖች ላይ ማስቀመጥ፡፡

**ሁለተኛ፡-** መዳፎችን በጉልበቶች ላይ ማስቀመጥ፡፡ ይህም በግራ መዳፉ የግራ እግሩን ጨብጦ ይይዛል፡፡ ቀኝ መዳፉ ደግሞ -ወደፊት እንደምንመለከተው- የአላህን አንድነት ያመለክትበታል፡፡ ግራ መዳፍ ምንጊዜም የተዘረጋ ነው፡፡





ኢብን ዑመር -አላም መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ይሁን- ሰላት ላይ ሲቀመጡ ቀኝ መዳፋቸውን በቀኝ ማዳፋቸው ላይ ሲያስቀምጡ

ጣቶቻቸውን በሙሉ ይሰበስቡ ከአውራ ጣታቸው ቀጥሎ ባለው -አመልካች-ጣታቸው አመላከቱ:: የግራ መዳፋቸውን በግራ ጭናቸው ላይ አስቀመጡ::» ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (580) ላይ ዘግበውታል:: በሌላ ዘገባ ደግሞ፣ «ግራ መዳፋቸው የግራ ጉልበታቸውን አጥብቆ ይይዝ ነበር::» ብለዋል:: ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (579) ላይ ዘግበውታል::

## 3 ተሸሁድ ላይ የጣቶችን አቀማመጥ ሁኔታ ማለዋወጥ ነቢያዊ ፈለግ ነው::

ተሸሁድ ላይ የጣቶች አቀማመት ይዘት ሁለት ዓይነት ነው:-

**የመጀመሪያው:-** የቀኝ እጃቹን ጣቶች በሙሉ ይሰበስባቸውና በአመልካች ጣት ብቻ ያመለክታል:: ግራ መዳፉ ግን እንደተዘረጋ ይቀመጣል::

ከዚህ ባለይ ባሳለፍነው የኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ፣ «...ሁሉንም ጣቶቻቸውን ሰበሰቡ:: ከአውራ ጣታቸው ቀጥሎ ባለው ጣታቸው አመለከቱ::...» ብለዋል:: ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (580) ላይ ዘግበውታል::

**ሁለተኛው:-** በተሸሁድ ላይ የቀኝ እጁን አውራ ጣትና አመልካች ጣቱን ጫፎች በማገናኘት ክብ ያደርግና ሌሎቹን ሶስት ጣቶቹን አጥፎ ይጨብጣቸዋል:: በአመልካች ጣቱም ወደፊት ያመለክታል:: የግራ እጁቹ ጣቶች ሳይታጠፉ በግራ ታፋ ላይ እንደተዘረጉ ይቀመጣሉ::





የዚህ ማስረጃው ኢብን ዑመር -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፤ "ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን- ለተሸሁድ ሲቀመጡ የግራ እጃቸውን በግራ ታፋቸው ላይ የቀኝ እጃቸውን በቀኝ ታፋቸው ላይ ላይ በማስቀመጥ አውራ ጣቸውንና አመልካች ጣታቸውን በማያያዝ ሌሎቹን ሶስት ጣቶቻቸውን ደግሞ በማጠፍ በአመልካች ጣታቸው ያመልከረቱ ነበር::" (850)

## 4 የሚስግደው ሰው የተሸሁድ ዓይነቶችን መለዋወጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው::

የሚከተለውን የተሸሁድ አገላለጽ አንዳንድ ጊዜ ሲል አንዳነመድ ጊዜ ደግሞ ሌላኛውን ይላል:: በሐዲሥ መሰረት ካለቸው **የተሸሁድ ዓይነቶች መካከል:-**

1. التَّحِيَّاتُ لِلَّهِ ، وَالصَّلَوَاتُ ، وَالطَّيِّبَاتُ ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ وَرَحْمَةُ اللَّهِ وَبَرَكَاتُهُ ، السَّلَامُ عَلَيْنَا وَعَلَى عِبَادِ اللَّهِ الصَّالِحِينَ ، أَشْهَدُ أَنْ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ ، وَأَشْهَدُ أَنَّ مُحَمَّدًا عَبْدُهُ وَرَسُولُهُ

**"አት-ተሒይያቱ ሊልላሂ ወስሰለዋቱ ወጥጠይዩባቱ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃ-ንነቢዩ ወረሕመቱልላሂ ወበረካቱሁ አስሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላለሂ**

**አስሳሊሒይነ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐምመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፡፡** /ሰላምታዎችም፣ ክብሮችም፣ መልካም ነገሮችም ላአላህ ይሁኑ፡፡ አንቱ ነቢይ ሆይ! በእርስዎ ላይ የአላህ ሰላምታ፣ እዝነትና በረከት ይሁን፡፡ በኛ ላይና በመልካሞቹ የአላህ ባሮች ላይ ሰላም ይሁን፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ ሙሐመድም ባሪያውና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ፡፡/" ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1202)፣ ሙስሊም በቁጥር (402) ከኢብን መስዑድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2. التَّحِيَّاتُ الْمُبَارَكَاتُ ، الصَّلَوَاتُ الطَّيِّبَاتُ لِلَّهِ ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ

**"አት-ተሒይያቱ አል-ሙባረካቱ አስ-ሰላዋቱ ሊልላህ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃ-ንነቢዩ..."** ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (403) ከኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን ቀሪው የሐዲሱ ክልፍ ካሳለፍነው የሚቀጥል ስለሆነ ይህንኑ ይላል፡፡

3. التَّحِيَّاتُ الطَّيِّبَاتُ الصَّلَوَاتُ لله ، السَّلَامُ عَلَيْكَ أَيُّهَا النَّبِيُّ

**"አት-ተሒይያቱ አጥ-ጠይባቱ አስ-ሰለዋቱ ሊልላሂ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃ-ንነቢዩ..."** ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (404) ከአቢ ሙሳ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን ቀሪው የሐዲሱ ክልፍ ካሳለፍነው የሚቀጥል ስለሆነ ይህንኑ ይላል፡፡

## 5 ሶስት ወይም አራት ረከዐህ በሚሰገድባቸው ሰላቶች ውስጥ በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ የሚሰግደው ሰው በመቀመጫው መቀመጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ይህ ማለት ሰላቶቹ ረከዐቸው ሶስት ወይም አራት የሆኑ ከሆኑ የሚሰግደው ሰው በመጨረሻ ተሸሁድ ላይ በግራ የመቀመጫ አካሉ መሬት ላይ ተደላድሎ ይቀመጣል፡፡ ይህ ዓይነቱ በግራ የመቀመጫ አካል ላይ መቀመጥ በበርካታ ዓይነት የመጣ ሲሆን እነዚህኑ መለዋወጡ የተወደደ ተግባር ነው፡፡

**በሐዲሥ ከተዘገቡ በመቀመጫ አካል የመቀመጥ ዓይቶች መካከል፡-**

1. **የግራ እግሩን አንጥፎ በቀኙ በኩል ያወጣዋል፡፡ ቀኝ እግሩንም ቀጥ አድርጎ ያቆማል፡፡ የመቀመጫ አካሉንም መሬት ላይ ያስቀምጣል፡፡**



ይህን የአቀማመጥ ሁኔታ ቡኻሪ -አላህ ይዘንላቸው- ከአቢ ሑምይድ አስ-ሳዒዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (828) ዘግበውታል፡፡



2> **ሁለቱን እግሮቹን አንጥፎ በቀኝ ጎኑ ያወጣቸዋል፡፡ የመቀመጫ አካሉንም መሬት ላይ ያስቀምጣል፡፡**

ይህን የአቀማመጥ ሁኔታ አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (731)፣ ኢብን ሒብባን በቁጥር (1867)፣ አል-በይሀቂይ በቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 128 ከአቢ ሑመይድ አስ-ሳዒዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን ትክክለኛነቱን አል-አልባኒይ አረጋግጠዋል፡፡ -ሁሉንም አላህ ይዘንላቸው-፡፡

ግልጽ እንዲሆን በመቀመጫ አካል መሬት ላይ የሚቀመጡት በመጀመሪያው ተሸሁድ ላይ ሳይሆን ረከዐቸው ሶሰት ወይም አራት በሆኑት ሰላቶች የመጨረሻው ተሸሁድ ላይ ነው፡፡

## 6 የሚሰግደው ሰው በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ ሰለዋት በሚያደርግበት ወቅት የሰለዋት ዓይነቱን መለዋወጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የሚደረገው ሰለዋት በበርካታ ሁኔታዎች የተዘገበ ሲሆን የሚሰግደው ሁሉንም እየለዋወጠ ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

1> **اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّدٍ ، وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ ، وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ ، اللَّهُمَّ بَارِكْ عَلَى مُحَمَّدٍ ، وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ ، كَمَا بَارَكْتَ عَلَى إِبْرَاهِيمَ ، وَعَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ**

**“አልላሁምመ ሰልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐምመዲን ከማ ሰልለይተ ዐላ ኢብራሂይመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ አንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡ አልላሁምመ ባሪክ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐምመዲን ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂይመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ አንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡** /አላህ ሆይ! በሙሐመድና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ ክብርን አውርድ፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ክብር እንዳወረድከው፡፡ በርግጥ አንተ እጅግ የተመሰገንክ በእጅግም የተከበርክ ነህ፡፡ አላህ ሆይ! ሙሐመድንና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ በረከትን አውርድ፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ በረከትን እንዳወረድከው፡፡ በርግጥ አንተ እጅግ የተመሰገንክ በእጅግም የተከበርክ ነህ፡፡/” ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3370) ከከዕብ ኢብን ዑጅረህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2> **اللَّهُمَّ صَلِّ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّد كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ ، وَبَارِكْ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى آلِ مُحَمَّدٍ كَمَا بَارَكْتَ عَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ ، فِي الْعَالَمِينَ ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ**

**“አልላሁምመ ሰልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ ኣሊ ሙሐምመዲን ከማ ሰልለይተ ዐላ ኢብራሂይመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ፣ ወባሪክ ዐላ ሙሐምመዲን ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂይመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ ፊልዓለሚይነ ኢንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡”** ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (405) ከአቢ መስዑድ አል-አንሷሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

3 اللَّهُمَّ صَلِّ عَلى مُحَمَّدٍ وَعَلَى أَزْوَاجِهِ وَذُرِّيَّتِهِ ، كَمَا صَلَّيْتَ عَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ ، وَبَارِكْ عَلَى مُحَمَّدٍ وَعَلَى أَزْوَاجِهِ وَذُرِّيَّتِهِ، كَمَا بَارَكْتَ عَلَى آلِ إِبْرَاهِيمَ ، إِنَّكَ حَمِيدٌ مَجِيدٌ

**“አልላሁምመ ሰልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ሰልለይተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ ወባሪክ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ባረክተ ዐላ ኢብራሂመ ወዐላ ኣሊ ኢብራሂይመ ኢነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡** /አላህ ሆይ! በሙሐመድና በሚስቶቻቸው፣ በዘሮቻቸው ላይ ክብርን አውርድ፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ በረከትን እንዳወረድከው፡፡ በሙሐመድና በሚስቶቻቸው፣ በዘሮቻቸው ላይ በረከት አውርድ፡፡ በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ በረከትን እንዳወረድከው፡፡” ሐዲሡን ሙስሊም ከአቢ ሑመይድ አስ-ሳዒዲይ -አላህ መልካም ሥራዎቻውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (407) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 7 የሚሰግደው ሰው ሰላቱን በሰላምታ ከማጠናቀቁ በፊት ከአራት ነገሮች በአላህ ጥበቃን መጠየቁ ነቢያዊ ፈለገ ነው፡፡

ይህ ሃሳብ የአብዛኛዎቹ ዑለሞች -አላህ ይዘንላቸው- የሃሳብ ስምምነት ነው፡፡ አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ የመጨረሻውን ተሸሁድ ካጠናቀቀ ከአራት ነገሮች በአላህ ይጠበቅ፡፡ከጀሀነም ቅጣት፣ ከቀብር ቅጣት፣ ከሕያውያንና ከሙታትን ፈተና፣ ከመሲሑ-ድደጃል ተንኮል፡፡”** ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (588)፣ ቡኻሪ በቁጥር (832) ላይ ዘግበውታል፡፡

በሐዲሥ የተዘገቡ በርካታ ዱዓዎች አሉ፡፡ ለሚሰገድ ሰው ዱዓዉን በየጊዜው ሰላቱን በሰላምታ ከማጠናቀቁ በፊት መቀያየሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ በሐዲሥ ከተዘገቡት ዱዓዎች መካከል፡-

1 اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ من المأْثَمِ والمغْرَمِ

**“አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነ-ልመእሠሚ ወልመግረሚ፡፡** /አላህ ሆይ! ወንጀል ከመፈጸምና ከክስረት ባንተ እጠበቃለሁ፡፡/” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (832)፣ ሙስሊም በቁጥር (589) ላይ ዘግበውታል፡፡

2 اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الجَنَّةَ وَأَعَوْذُ بِكَ مِنَ النَّارِ

**“አልላሁምመ አስአሉከ-ልጀንነተ ወአዑዙ ቢከ ሚነ-ንናር፡፡** /አላህ ሆይ! ጀንትን እጠይቅሃለሁ፤ ባንተም ከእሳት እጠበቃለሁ፡፡/” ሐዲሡን አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (792) ሲዘግቡት አል-አልባኒይም የዘገባ ሰነዳቸውን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ (ሰሒሑ አቢ ዳዉድ ቅጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 377)፡፡

3 اللَّهُمَّ إِنِّي ظَلَمْتُ نَفْسِي ظُلْمًا كَثِيرًا وَلَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ فَاغْفِرْ لِي مَغْفِرَةً مِنْ عِنْدِكَ وَارْحَمْنِي ، إِنَّكَ أَنْتَ الْغَفُورُ الرَّحِيمُ

**“አልላሁምመ ኢንኒ ዘለምቱ ነፍሲ ዙልመን ከሢይራ ወላ የግፊሩ-ዝዙኑዉበ ኢልላ አንተ ፈ-ግፊር ሊ መግፊረተን ሚን ዒንዲከ ወርሐምኒ ኢንነከ አንተ-ልገፉሩ-ርረሒይም፡፡** /አላህ ሆይ! ነፍሴን ብዙ በደሎችን በድያለሁ፤ ወንጀሎችን ደግሞ ካንተ በስተቀር የሚምር የለም፡፡ ካንተ በሆነ ምህረት ወንጀሎቼን ማርልኝ እዘንልኝም፡፡ በርግጥ አንተ እጅግ መሐሪና አዛኝ ነህ፡፡/” ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6326)፣ ሙስሊም በቁጥር (2705) ላይ ዘግበውታል፡፡

4 اللَّهُمَّ أَعِنِّي عَلَى ذِكْرِكَ ، وَشُكْرِكَ ، وَحُسْنِ عِبَادَتِكَ

**“አላልሁምመ አዒንኒ ዐላ ዚክሪከ ወሹክሪከ ወሑስኒ ዒባደቲክ፡፡** /አላህ ሆይ! አንተን በማስተወስ፣ አንተን በማመስገን፣ ማመለክህን በማሳመር ላይ እርዳኝ፡፡/” ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ቁጥር (22119)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (1522)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (1304) ሲዘግቡት አል-አልባኒይ ትክክለነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ሰሒሑ-ል-ጃሚዕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 1320)፡፡

5 اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْبُخْلِ ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنَ الْجُبْنِ ، وَأَعُوذُ بِكَ أَنْ أُرَدَّ إِلَى أَرْذَلِ الْعُمُرِ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ فِتْنَةِ الدُّنْيَا ، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ عَذَابِ الْقَبْرِ

**“አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነ-ልቡኽሊ ወአዑዙ ቢከ ሚነ-ልጁብኒ፣ ወአዑዙ ቢከ አን ኡረድደ ኢላ አርዘሊ-ልዑሙሪ ወአዑዙ ቢከ ሚን ፊትነቲ-ድዱንያ ወአዑዙ ቢከ ሚን ዓዛቢ-ልቀብር፡፡** /አላህ ሆይ! ከንፉግነት ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከፈሪነትም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ወደእርጅና እድሜ ከመመለስም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ ከምድራዊው ሕይወት ፈተና ባንተም እጠበቃለሁ፡፡ ከቀብር ቅጣትም ባንተ እጠበቃለሁ፡፡/” ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6370) ላይ ዘግበውታል፡፡

6 اللَّهُمَّ حَاسِبْنِي حِسَابًا يَسِيرًا

**“አልላሁምመ ሓሲብኒ ሒሳበን የሲይራ፡፡** /አላህ ሆይ! ገር የሆነ መተሳሰብን ተሳሰበኝ፡፡/” አሕመድ ሐዲሡን በቁጥር (24215) ላይ ሲዘግቡት አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ተሕቂይቁ ሚሽካቱ-ልመሳቢይሕ ቅጽ ፡ 3 ገጽ ፡ 1544)

ከዚያ ሰላምታውን እያቀረበ በመዞር ሰላቱን በሰላምታ ያጠናቅቃል፡፡ መዞሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ሲዞሩም በጣም መዞር እንዲሁ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሲዞሩ ከኋላቸው ያለ ሰው የጉንጫቸውን ንጣት እስከሚያይ ድረስ ይዞሩ ነበር፡፡ ከሰዕድ ኢብን አቢ ወቃስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በቀኛቸውና በግራቸው ሰላምታ ሲያቀርቡ የጉንጫቸው ንጣትን እስከማይ ድረስ እመለከታቸው ነበር፡፡» ብለዋል፡፤ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (582) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 8 በሐዲሥ የተዘገቡ አዝካሮችን ግዴታ የሆኑ ሰላቶችን በሰላምታ ካጠናቀቁ በኋላ ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

አን-ነወዊይ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ዑለሞች ከሰላት በኋላ ዚክር ማድረግ በመወደዱ ላይ ሃሳባቸውን አንድ አድርገዋል፡፡» አል-አዝካር ገጽ ፡ 66፡፡

በዚህ ዚክር ድምጸን ከፍ ማድረግ ይወደዳል፡፡ ኢብን ዐባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸወን ይውደድላቸው-፣ «ግዴታ ከሆኑ ሰላቶች በኋላ ሰዎች ሲበታተኑ በዚክር ድምጽን ከፍ ማድረግ በነቢዩ -በእሳቸው ላይ የአላህ እዝነትና ሰላምታ ይሁን- ዘመን ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (841)፣ ሙስሊም በቁጥር (583) ላይ ዘግበውታል፡፡

### አዝካሮቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. اللَّهُمَّ أَنْتَ السَّلاَمُ وَمِنْكَ السَّلاَمُ ، تَبَارَكْتَ ذَا الْجَلاَلِ وَالإِكْرَامِ

   ሶስት ጊዜ -ከላቀው- አላህ ምህረትን ይጠይቃል (አስተግፊሩ-ልላህ ይላል)፡፡ ከዚያም፣ **“አልላሁምመ አንተ-ስሰላም ወሚንከ-ስሰላም ተባረክተ ዚል ጀላሊ ወልኢክራም፡፡** /አላህ ሆይ! አንተ ሰላም ነህ፡፡ ሰላምም ካንተ ነው፡፡ የክብርና የሚግስ ባለቤት የሆንከው ጌታ የተባረክ ነህ፡፡/” ይላል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (591) ላ ከሠውባን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2. لاَ إِلهَ إِلاَّ اللّٰهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ، لاَ حَوْلَ وَلاَ قُوَّةَ إِلاَّ بِاللّٰهِ، لاَ إِلهَ إِلاَّ اللّٰهُ، وَلاَ نَعْبُدُ إِلاَّ إِيَّاهُ، لَهُ النِّعْمَةُ وَلَهُ الْفَضْلُ ، وَلَهُ الثَّنَاءُ الْحَسَنُ ، لاَ إِلهَ إِلاَّ اللّٰهُ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ ، وَلَوْ كَرِهَ الْكَافِرُونَ

   **“ላ ኢላሀ ኢልለልላሁ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁ-ልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር፤ ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ፤ ላ ኢላህ አልለላሁ ላ ነዕቡዱ ኢልላ ኢይያሁ፤ ለሁ-ንኒዕመቱ ወለሁ-ልፈድሉ፤ ወለሁ-ሥሠናኡ-ልሐሰን፤ ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ሙኽሊሲይነ ለሁ-ድዲይነ ወለው ከሪሀ-ልካፊሪዉን፡፡** / ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ ብጤ የለውም፡፡ ንግስናም ለርሱ ነው፡፡ ምስጋናም ለርሱ ነው፡፡ እርሱም በሁለም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ በርታትም ሆነ ነገሮችን መለወጥ በአላህ ካልሆነ በስተቀር የለም፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ከእርሱ በስተቀር ሌላን አናመልክም፡፡ ጸጋም ለእርሱ ነው፡፡ ችሮታም ለእርሱ ነው፡፡ መልካም ውዳሴም ለእርሱ ነው፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ከሐዲያን የሚጠሉ ቢሆንም ለእርሱ ቅን ታዛዦች ነን፡፡/” ሐዲሡን ሙስሊም ከኢብን ዘበይር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (596) ላይ ዘግበውታል፡፡

3. لاَ إِلهَ إِلاَّ اللّٰهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ، اللَّهُمَّ لاَ مَانِعَ لِمَا أَعْطَيْتَ، وَلاَ مُعْطِيَ لِمَا مَنَعْتَ ، وَلاَ يَنْفَعُ ذَا الْجَدِّ مِنْكَ الْجَدُّ

   **“ላ ኢላሀ ኢልለልላሁ ወሕደሁ ላ ሸሪይከ ለሁ ለሁ-ልሙልኩ ወለሁ-ልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር፤ አልላሁምመ ላ ማኒዐ ሊማ አዕጠይተ ወላ ሙዕጢየ ሊማ መነዕት ወላ የንፈዑ ዛል ጀድዲ ሚንከ-ልጀድ፡፡** /ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ ንግስናም ለእርሱ ነው፡፡ምስጋናም ለእርሱ ነው፡፡ እርሱ

በሁሉም ነገር ቻይ ነው- አላህ ሆይ! ለሰጠኸው ከልካይ የለም፡፡ ለከለከልከውም ሰጪ የለም፡ ፡ ካንተ ችሮታ ይበልጥ የሌላ ችሮታ ፈጽሞ አይጠቅምም፡፡/" ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (593) ዘግበውታል፡፡

4〉 **ከዚያ በሐዲሥ የተዘገቡ ውዳሴዎችን ይላል፡፡ የተለያየ አገላለጾች አሏቸው፡፡ እነርሱም፡-**

سبحان الله، الحمد لله، الله أكبر

**የመጀመሪያው፡-** **"ሱብሓነ-ልላህ"** (33) ጊዜ፡፡ **"አልሐምዱሊ-ልላህ"** (33) ጊዜ፡፡ **"አልላሁ አክበር"** (33) ጊዜ፡፡ የመቶ መሙያ፣ **"ላ ኢላሀ አልለላህ ወሕደሁ** ... " አንድ ጊዜ፡፡

لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ "አላህን ከእያንዳንዱ ሰላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ከሚነገሩ ውድቅና ከንቱ ንግግሮች ያጠራ፣ አላህን ሰላሳ ሶስት ጊዜ ያመሰገነ፣ አላህን ሰላሳ ሶስት ጊዜ ያላቀ እነዚህ ዘጠና ዘጠን ናቸው፡፡ መቶኛ መሙያውን፡- ከአላህ በበስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ብጤም የለውም፡፡ ንግስናም ለእርሱ ነው፡፡ ምስጋናም ለእርሱ ነው፡፡ እርሱም በሁሉም ነገሮች ላይ ቻይ ነው፡፡ ያለ ሐጢአቱ የባሕር አረፋ ያህል ቢሆኑም በእርግጥ ተምረውለታል፡፡" ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (597) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ሁለተኛው፡-** **" ሱብሓነ-ልላህ (33) ጊዜ፣ አልሐምዱሊ-ልላህ (33) ጊዜ፣ አላሁ አክበር (34) ጊዜ፡፡"** ይህም ከዕብ ኢብን ዑጅራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ማጠቃለያ የሆኑትና ከእያንዳንዱ ግዴታ የሆነ ሰላት በኋላ የሚላቸውን ወይም የሚተገብራቸውን ከንቱ የማያስቀሩ የሆኑ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላህን ከሚነገሩ ውድቅና ክንቱ ንግግሮች ማጣራት፣ ሰላሳ ሶሰት ጊዜ አላህን ማመስገን፣ ሰላሳ አራት ጊዜ አላህን ማላቅ ናቸው፡፡"** ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (596) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ሶስተኛ፡-** **"ሱብሓነ-ልላህ (25) ጊዜ፣ አልሐምዱሊ-ልላህ (25) ጊዜ፣ አላሁ አክበር (25) ጊዜ፣ ላ ኢላሀ ኢ-ልለልላህ (25) ጊዜ፡፡"**

ይህን አገላለጽ አት-ቲርሚዚይ ከዐብዱላህ ኢብን ዘይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3413) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ተሕቂይቁ ሚሽካቱ-ልመሳቢይሕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 307)

**አራተኛ**፡- **"ሱብሓነ-ልላህ (10) ጊዜ፣ አልሐምዱሊ-ልላህ (10) ጊዜ፣ አላሁ አክበር (10) ጊዜ፡፡"**

ይህን አገላለጽ አት-ቲርሚዚይ ከዐብደላህ ኢብን ዐምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3410) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ (ተሕቂይቁ ሚሽካቱ-ልመሳቢይሕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ፡ 743)

ከዚህ በላይ በሐዲሥ የተዘገቡ ዒባዳዎች እንዴት እንደሚፈጸሙ የሚያመለክት መሰረታዊ መመሪያ እንዳሳለፍነው ይህንንም ዚክር በማለያየት አንድ ጊዜ ሌለውን ደግሞ ሌላ ጊዜ ማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ተስቢሕን በጣት ማድረግ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህንንም በተመለከተ አሕመድና በአት-ቲርሚዚይ በዘገቡት ሐዲሥ ላይ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ "ተስቢሕ አድርጉ በጣቶች ላይ አድርጉትም፡፡ በእርግጥ እነርሱ ተጠያቂዎች፣ ተናጋሪዎችም ናቸው፡፡" ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (27086)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (3486) የዘገቡት ሲሆን (ተሕቂይቁ ሚሽካቱ-ልመሳቢይሕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ፡ 753)

### 5 አየቱ-ልኩርሲይን መቅራት

አቢ ኡማመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ከእያንዳንዱ ግዴታ የሆነ ሰላት በኋላ አየተ-ልኩርሲይዩን ያነበበ ከሞት በስተቀር ጀነት ከመግባት የሚከለክለው ነገር የለም፡፡"** ሐዲሡን አን-ነሳኢይ በሱነኑ-ልኩብራ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (9928) ላይ የዘገቡት ሲሆን አል-ሙንዚሪይ አት-ርጊይብ ወት-ተርሂይብ በተሰኘው መጽሐፋቸው በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2373)፣ ኢብን ዐብዱ-ልሃዲ አል-ሙሐሪር በተሰኘው መጽሐፋቸው ቅጽ 1 ገጽ ፡ 198፣ ኢብን አል-ቀይዩም ዛዱ-ልሚዓድ በተሰኘው መጽሐፋቸው ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 303 ላይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡

### 6 አል-ሙዐዊዘተይንን "ቁል አዑዙ ቢረብቢ-ልፈለቅ" እና "ቁል አዑዙ ቢረብቢ-ንናስ"ን መቅራት፡፡

ዑቅበት ኢብን ዓሚር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከእያንዳንዱ ሰላት በኋላ አል-ሙዐዉዘተይንን እንድቀራ አዘዙኝ፡፡» አቡ ዳዉድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1525) ላይ የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ፣ «የዘገባ ሰነዱ ትክክል ነው ብያለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ከዚህ ሌላ የሐዲሡን ትክክለኛነት ኢብን ኹዘይመህና ኢብን ሒባን አረጋግጠዋል፡፡ ሰሒሑ አቢ ዳዉድ ቅጽ ፡ 5 ገጽ ፡ 254፡፡

እነዚህ አጠቃላይ የሆኑና አንድ የሚሰግድ ሰው ቢተገብራቸው የሚወደድ የሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች ናቸው፡፡ እስካሁንም ድረስ የፈጅር ሰላት ወቅት ውስጥ ነው ያለነው፡፡ እዚህ ላይ ያቀረብነው በሁሉም የሰላት ምዕራፎች ላይ ለመጥቀስ ይቀለን ዘንድ ነው፡፡ -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፡፡

## 9 ከአል-ፈጅር ሰላት በኋላ ጸሐይ እስክትወጣ ድረስ በመስገጃው ላይ መቀመጥ

ጃቢር ኢብን ሰሙረህ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የአል-ፈጅር ሰላትን ከሰገዱ መስገጃቸው ላይ ጸሐይ ከፍ ብላ እስከምትወጣ ድረስ ይቀመጡ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (670) ላይ ዘግበውታል፡፡

## የጠዋት አዝካሮች



የጠዋት አዝካሮች ወቅት ጎህ ከቀደደበበት ጀምሮ ይጀምራል፡፡ ይኸውም ሙአዚኑ አዛን ለአል-ፈጅር ሰላት አዛን ካደረገበት ጊዜ አንስቶ የጠዋት አዝካሮች ወቅት ይጀምራል፡፡ አዝካር ለአንድ የአላህ ባሪያ በምድራዊ ሕይወቱ መጠበቂያ ከለለላው፣ በወዲያኛው ዘላለማዊ ዓለም ደግሞ ትልቅ ሐብቱ በመሆኑ ላይ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

### የጠዋትና የማታ አዝካሮች የሚከተሉት ናቸው

1 مَنْ قَالَ لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ وَحْدَهُ لَا شَرِيكَ لَهُ ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٍ

**“ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ወሕደሁ ላ ሸሪይከ ለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር፤ ሲያነጋ አስር ጊዜ ያለ በእሷ ምክንያት አንድ መቶ ምንዳዎች ተጽፎለታል፡፡ ከእርሱ ላይም አንድ መቶ ሐጢአቶች ተሰርየውለታል፡፡ አንድ ጫንቃን ነጻ ከማውጣት ጋር ትስካከልለታለች፡፡ እሷ ምክንያትም በዚያን ወቅት እስከሚያመሽ ድረስ ይጠበቃል፡፡ ይህንኑ ሲያመሽ ያለ የዚሁ ዓይነት ይሆንለታል”** ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (8719) ላይ ዘግበውታል፡፡ ኢብን ባዝም -አላህ ይዘንላቸው- ዘገባው በመልካም ደረጃ የሚገኝ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡

2 **أَمْسَيْنَا وَأَمْسَى الْمُلْكُ لِلَّهِ ، وَالْحَمْدُ لِلَّهِ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ مِنْ خَيْرِ هَذِهِ اللَّيْلَةِ وَخَيْرِ مَا فِيهَا، وَأَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّهَا وَشَرِّ مَا فِيهَا ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْكَسَلِ وَالْهَرَمِ ، وَسُوءِ الْكِبَرِ، وَفِتْنَةِ الدُّنْيَا ، وَعَذَابِ الْقَبْرِ**

**وَإِذَا أَصْبَحَ قَالَ ذَلِكَ أَيْضًا : أَصْبَحْنَا وَأَصْبَحَ الْمُلْكُ لِلَّهِ... أَسْأَلُكَ خَيْرِ مَا فِي هَذَا الْيَوم وَخَيْر مَا بعدِه، وَأَعُوذُ بِك مِنْ شَرِّ مَا فِي هَذا اليَوم وَشَر مَا بَعْدِه**

**“አምሰይና ወአምሰ-ልሙልከ ሊልላህ፣ ወልሐምዱሊልላህ ላ ኢላሀ ኢልለላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለህ፣ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ ሚን ኸይሪ ሀዚሂ-ልለይለቲ ወኸይረ ማፊይሃ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪሃ ወሸርረ ማፊይሃ፣ አልላሁምመ አንኒ አዑዙ ቢከ ሚል ከሰሊ፣ ወልሀረሚ፣ ወሱኢል ኪበሪ፣ ወፊትነቲ-ድዱንያ፣ ወዐዛቢ-ልቀብር፡፡” ሲያነጋም እንዲሁ ይላል፣ “አስበሕና ወአስበሐ-ልሙልኩ ሊልላህ … አስአሉከ ኸይረ ማፊሀዘ-ልየውሚ ወኸይረ ማ በዕደህ፣ ወአዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማፊ ሀዘ-ልየውሚ ወሸርረ ማበዕደህ…/** አመሸን ንግስናም ለአላህ ሆኖ አመሸ፡፡ ምስጋናም አላህ ነው፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ ብጤም የለውም፡፡ አላህ ሆይ! ከዚህች ሌሊት መልካም ነገርንና በውስጧም ካለው መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ፡፡ በመጠፎ ነገሮቿና በውስጧም ከሚገኝ መጥፎዋ በአንተ እጠበቃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ከስንፍና፣ ከሽምግልና፣ ከመጥፎ እርጅና፣ ከምድር ፈተና እና ከቀብር ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ፡፡/ ሲያነጋ ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ቃላት በመለወጥ ይህንኑ ይላል፡፡ /አነጋን ንግስናም ለአላህ ሆኖ አነጋ፡፡ …. የዚህን ቀን መልካምነትና ከርሱ በኋላ የሚገኘን መልካም ነገር እጠይቅሃለሁ፡፡ ከርሱ መጥፎነትና ከእርሱ በኋላ ካለው መጥፎ ነገር ባንተ እጠበቃለሁ፡፡…” ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2723) ዘግበውታል፡፡

3 **اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ خَلَقْتَنِي,وَأَنَا عَبْدُكَ,وَأَنَا عَلَى عَهْدِكَ وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ ، أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ، وَأَبُوءُ لَكَ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ**

**ሰይዩዱ-ልኢስቲግፋር (የምህረት መጠየቂያ ቃላት የበላይ)፡- “አልላሁምመ አንተ ረብቢ ላ ኢላሀ ኢልላ አንተ ኸለቅተኒ ወአነ ዐብዱከ፣ ወአነ ዐላ ዐህዲክ ወወዕዲክ ማስተጠዕቱ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማሰነዕቱ አቡዉኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለይየ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈግፊር ሊ ፈኢንነሁ ላ የግፊሩ-ዝዙኑዉበ ኢልላ አንተ፡፡** አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ፡፡ ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ የፈጠርከኝ አንተ ነህ፡፡ እኔ ባሪያህ ነኝ፡፡ በምችለው አቅም በቃል-ኪዳንህና በቀጠሮህ ላይ ነኝ፡፡ በእኔ ላይ በለገስከው ጸጋዎችህ ወዳንተ እመለሳለሁ፡፡ በወንጀሎቼም ወዳንተ እመለሳለሁ፡፡ ወንጀሎቼን ማርልኝ፡፡ በርግጥ ካንተ በስተቀር ወንጀሎችን የሚምር ማንም የለም፡፡/” የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “እርግጠኛ ሆኖ በቀኑ ክፍለ-ጊዜ ላይ ያለና በዚያው ቀኑ ሳይመሽ የሞተ እንደሆነ እርሱ ከጀነት ሰዎች ነው፡፡ እርግጠኛ ሆኖ ሌሊት ላይ ያለና በዚያው ሌሊት ላይ ሳያነጋ የሞተ እንደሆነ እርሱ ከጀነት ሰዎች ነው፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6306) ላይ ዘግበውታል፡፡

4 اللَّهُمَّ بِكَ أَصْبَحْنَا، وَبِكَ أَمْسَيْنَا، وَبِكَ نَحْيَا، وَبِكَ نَمُوتُ، وَإِلَيْكَ النُّشُورُ
اللَّهُمَّ بِكَ أَمْسَيْنَا وَبِكَ أَصْبَحْنَا وَبِكَ نَحْيَا وَبِكَ نَمُوتُ وَإِلَيْكَ الْمَصِيرِ

**"አንዳችሁ ሲያጋ፣ ‹አልላሁምመ ቢከ አስበሕና፣ ወቢከ አመንና፣ ወቢከ አስበሕና ወቢከ አምሰይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙዉት ወኢለይከ-ልመሲይር፡፡** /አላህ ሆይ! ባንተ አነጋን፣ ባንተም አመሸን፡፡ ባንተም ሕያው እንሆናለን፡፡ ባንተም እንሞታለን፡፡ መመለሻም ወዳንተ ነው፡፡/" ይበል፡፡ ሲያመሽ ‹አልላሁምመ ቢከ አምሰይና ወቢለከ አስበሕና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙዉት ወኢለይከ-ንኑሹር፡፡ /አላህ ሆይ! ባንተ አመሸን፡፡ ባንተም አነጋን፡፡ ባንተ ሕያው እንሆናለን፡፡ ባንተም እንሞታለን፡፡ ሞቶ መቀስቀስም ወዳንተ ነው፡፡/› ይበል፡፡" ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5068)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (3391)፣ አን-ነሳኢይ በአስ-ሱነን አል-ኩብራ መጽሐፋቸው ላይ በቁጥር (9836)፣ ኢብን ማጀህ በቁጥር (3868) ላይ ዘግበውታል፡፡

5 اللَّهُمَّ فَاطِرَ السَّمَوَاتِ وَالْأَرْضِ ، عَالِمَ الْغَيْبِ وَالشَّهَادَةِ ، لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ رَبَّ كُلِّ شَيْءٍ وَمَلِيكَهُ ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ نَفْسِي وَمِنْ شَرِّ الشَّيْطَانِ وَشِرْكِهِ ، وَأَنْ أَقْتَرِفَ عَلَى نَفْسِي سُوءًا ، أَوْ أَجُرَّهُ إِلَى مُسْلِمٍ

**"አልላሁምመ ፈጢረ-ስሰማዋቲ ወልአርድ፣ ዓሊሚ-ልገይቢ ሸሸሃደህ ላ ኢላሀ ኢልላ አንተ ረብበ ኩል ሸይኢን የመሊይከሁ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲ ወሚን ሸርሪ-ሸሸይጣኒ ወሺርኪሂ ወአን አቅተሪፈ ዐላ ነፍሲ ሱዉአን አው አጁርረሁ ኢላ ሙስሊም፡፡** /አላህ ሆይ! የሰማያትና የምድር ፈጣሪ፣ ሩቅና ድብቅ እውቀቶችን የምታውቅ የሆነከው ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንተ የሁሉም ጌታና ገዢ ነህ፡፡ ከነፍሴ ተንኮል፣ ከሸይጣንም ተንኮልና ጉትጎታ ባንተ እጠበቃለሁ፡፡ በነፍሴ ላይ መጥፎ ነገርን ከምሰራ ወይም ወደሙስሊም እንዳልወስድ ባንተ እጠበቃለሁ፡፡/" ይህን አስመልክተው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ "ስታነጋ፣ ስታመሽ፣ መኝታህን ስትይዝ ይህችን በላት" ብለዋል፡፡ አሕመድ ሐዲሡን በሐዲሥ (6597)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (5076)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (3529)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (7699) ላይ ዘግበውታል፡፡ኢብን ባዝም -አላህ ይዘንላቸው- የዘገባ ሰነዱን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡

6 بِسْمِ اللَّهِ الَّذِي لَا يَضُرُّ مَعَ اسْمِهِ شَيْءٌ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَهُوَ السَّمِيعُ الْعَلِيمُ

**"ማንኛወም የአላህ ባሪያ በየቀኑ ጠዋት፣ በየምሽቱ ሌሊት፡- ‹ቢስሚልላሂ-ልላዚ ላ የዱርሩ መዐ-ስሚሂ ሸይኡን ፊልአርዲ ወላ ፊስሰማኢ ወሁወ-ስሰሚይዑ-ልዐሊይም፡፡** /በዚያ ከስሙ ጋር በምድር ወይም በሰማይ ላይ ያለ አንዳች ነገር የማይጎዳው በሆነው አላህ ስም፡፡ እርሱም ሰሚውና ዐዋቂው ነው፡፡› **ሶስት ጊዜ ካለ አንዳች ነገር አይጎዳውም፡፡"** ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (446)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (10179)፣ ኢብን ማጀህ በቁጥር (3869) ላይ ዘግበውታል፡፡

ኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «አት-ቲርሚዚይ ሐዲሡ መልካም ደረጃ ላይ የሚገኝ ትክክለኛ የሆነ ሐዲሥ ነው ብለዋል ሐዲሡም እሳቸው -አላህ ይዘንላቸው- እንዳሉት ነው። ፡» ብለዋል፡፡

7 رَضِيتُ بِاللَّهِ رَبًّا , وَبِالْإِسْلَامِ دِينًا , وَبِمُحَمَّدٍ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ نَبِيًّا

**“ማንኛውም የአላህ ባሪያ ሲያነጋና ሲያመሽ ሶስት ጊዜ፣ ‹ረዲይቱ ቢልላሂ ረብበን፣ ወቢልኢስላሚ ዲይነን፣ ወቢሙሐምመዲን ሰልላሁ ዐለይሂ ወሰልለመ ነቢይያ፡፡** /የአላህን ጌትነት፣ የኢስላምን ሃይማኖትነት፣ የሙሐመድን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ነቢይነት ወደድሁ፡፡/› **ካለ በትንሳኤ እለት አላህ እሱን ሊያስደስተው በአላህ ላይ ሐቅ አለ፡፡”** ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (18967)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (3389)፣ ኢብን ማጀህ በቁጥር (3870) ላይ ዘግበውታል፡፡ ኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው- የሐዲሡን የዘገባ ሰነድ ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡

8 اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَافِيَةَ فِي الدُّنْيَا وَالْآخِرَةِ ، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْأَلُكَ الْعَفْوَ وَالْعَافِيَةَ فِي دِينِي وَدُنْيَايَ ، وَأَهْلِي وَمَالِي ، اللَّهُمَّ اسْتُرْ عَوْرَاتِي، وَآمِنْ رَوْعَاتِي، اللَّهُمَّ احْفَظْنِي مِنْ بَيْنِ يَدَيَّ وَمِنْ خَلْفِي ، وَعَنْ يَمِينِي وَعَنْ شِمَالِي ، وَمِنْ فَوْقِي ، وَأَعُوذُ بِعَظَمَتِكَ أَنْ أُغْتَالَ مِنْ تَحْتِي

**“አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ-ልዓፊየተ ፊድዱንያ ወልኣኺረህ፣ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ አል-ዐፍወ ወልዓፊየተ ፊዲይኒ ወዱንያየ ወአህሊ ወማሊ፣ አልላሁምመ-ስቱር ዐውራቲ ወአሚን ረውዓቲ፣ አልላሁምመ ኢሕፊዝኒ ሚን በይኒ የደይየ ወሚን ኸልፊ ወዐን የሚይኒ ወዐን ሺማሊ ወሚን ፈውቂ ወአዑዙ ቢዐዘመቲከ አን አግታለ ሚን ተሕቲ፡፡** /አላህ ሆይ! በሃይማኖቴና በምድራዊ ሕይወቴ ላይ ደህንነትን እጠይቅሃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! በሃይማኖቴ፣ በምድራዊ ሕይወቴ፣ በቤተሰቤና በገንዘቤ ይቅርታንና ደህንነተን እጠይቅሃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! ነውሬን ደብቅልኝ፡፡ ክብሬን ጠብቅልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከፊት ለፊቴ፣ ከበስተኋላዬ፣ በቀኜ፣ በግራዬ፣ ከላዬ ጠበቀኝ፡፡ ከሥሬም እንዳልርድ በትልቅነትህ እጠበቃለሁ፡፡/” ሐዲሡን አሕመድ ሙስነድ በተሰኘው መጽሐፋቸው በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (4785)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (5074)፣ አን-ነሳኢይ ሱነኑ-ልኩብራ በተሰኘው መጽሐፋቸው በቁጥር (10401)፣ ኢብን ማጀህ በቁጥር (3871) ሲዘግቡ አል-ሓኪም ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡

9 أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللَّهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ

**“አዑዙ ቢከሊማቲ-ልላሂ-ትታምማቲ ሚን ሸርሪ ማኸለቅ፡፡** /ምሉእ በሆኑት የአላህ ቃላት ከተፈጠረው ተንኮል እጠበቃለሁ፡፡/” ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (7898)፣ አት-ቱርሚዚይ በቁጥር (3437) ከቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን የሐዲሡን የዘገባ ሰነድ ትክክለኛነት ኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው- አረጋግጠዋል፡፡

10 أَصْبَحْنَا عَلَى فِطْرَةِ الْإِسْلَامِ ، وَكَلِمَةِ الْإِخْلَاصِ، وَدِينِ نَبِيِّنَا مُحَمَّدٍ ـ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ـ وَمِلَّةِ أَبِينَا إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا، وَمَا كَانَ مِنَ الْمُشْرِكِينَ

«የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሲያነጉ፣ **"አስበሕና ዐላ ፊጥረቲ-ልኢስላም፣ ወከሊመቲ-ልኢኽላስ፣ ወዲኒ ነቢይዪና ሙሐምመዲን -ሰልለላሁ ዐለይሂ ወሰልለም- ወሚልለቲ አቢይና ኢብራሂይመ ሐኒይፈን ወማ ካነ ሚነ-ልሙሽሪኪይን፡፡** /በኢስላም ተፈጥሮ ላይ፣ በቅንነት ቃል፣ በነብያችን ሙሐመድ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዲን ላይና በቀጥተኛው የአባታችን መንገድ ላይ አነጋን፡፡ በእርግጥ እሳቸው አጋሪ አልነበሩም፣" ይሉ ነበር፡፡» ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (21144፣ 15365) ላይ ዘግበውታል፡፡ ሲያመሹም፣ "አምሰይና ዐላ ፊጥረቲል-ኢስላም.../በኢስላም ተፈጥሮ ላይ አመሸን.../" ይሉ ነበር፡፡ የሐዲሡን የዘገባ ሰነድ ትክክለኛነት ኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው- አረጋግጠዋል፡፡

ከዚህ በላይ ባለፈው የኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው- የሐዲሥ ማረጋገጫ ሰነድ ላይ ርዕሱ፣ ***‹‹ቱሕፈቱ-ልአኽያር ቢበያኒ ጁምቱ-ንፊዐህ ሚማ ወረረ ፊልከታቢ ወስሱነህ ሚን-ልአድዒየቲ ወልአዝካር››*** የተሰኘ ሲሆን በውስጡም የጠዋትና የማታ አካሮች ምዕራፍ ይገኛል፡፡

11 يَا حَيُّ يَا قَيُّومُ بِرَحْمَتِكَ أَسْتَغِيثُ أَصْلِحْ لِي شَأْنِي كُلَّهُ ، وَلَا تَكِلْنِي إِلَى نَفْسِي طَرْفَةَ عَيْنٍ

**"ያ ሐይዩ ያ ቀይዩሙ ቢረሕመቲከ አሥተጊይሡ አስሊሕ ሸእኒ ኩልለሁ ወላ ተኪልኒ ኢላ ነፍሲ ጠርፈተ ዐይኒ፡፡"** ሐዲሡን አን-ነሳኢይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (10405)፣ አል-በዝዛር በመጽሐፋቸው ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 282 የዘገቡት ሲሆን የሐዲሡን በመልካም ደረጃ መገኘት ኢብን አል-ሐጀርና አል-አልባኒይ አረጋግጠዋል፡፡ ነታኢጁ-ልአፍካር ገጽ ፡ 177፣ ሲልሲለቱ-ልአሓዲሡ አስ-ሰሒሐህ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 449፡፡

12 حَسْبِيَ الله لاَ إِلهَ إِلاَّ هُوَ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَهُوَ رَبُّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ

**"ሰባት ጊዜ ሕስቢየ-ልላሁ ላ ኢላሀ አልላ ሁወ ዐለይሂ ተወክከልቱ ወሁወ ረብቡ-ልዐርሺ-ልዐዚይም ያለ አላህ ከጭንቁ ይብቃቃዋል፡፡"** ሐዲሡን አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5081) ከአቢ ደርዳእ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን ሐዲሡን ያስተላለፉት እምነት የሚጣልባቸው ናቸው፡፡ አል-አልባኒይ ሐዲሡ የመርፉዕ ደረጃ የሚሰጠው ነው ብለዋል፡፡ አስ-ሲልሰለህ ቅጽ ፡ 11 ገጽ ፡ 449፡፡



## ሶስተኛ፡- የአድ-ዱሓ ሰላት ወቅት



በአድ-ዱሓ ወቅት አንድ የአላህ ባሪያ የአድ-ዱሓ ሰላት መስገዱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

### ለዚህ ማስረጃው፡-

1. አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ወደጄ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሶስት ነገሮች ላይ አደራ ብለውኛል፡፡ -እነርሱም፡- ከእያንዳንዱ ወር ሶስት ቀናትን በመጾም፣ በአድ-ዱሓ ሁለት ረከዐዎችና ከመተኛቴ በፊት ዊትር በመስገድ ላይ ናቸው፡፡» ብለዋል፡፡ እንደዚሁም ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አባ ደርዳእን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዚሁወ ላይ አደራ ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (722) ላይ ዘግበውታል፡፡ አባ ዘርንም -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- አድራ ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አን-ነሳኢይ በአስ-ሱነኑ-ልኩብራ መጽሐፋቸው በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2712) ላይ ዘግበውታል፡፡ አል-አልበኒይም የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ አስ-ሰሒሐህ 2166፡፡

2 አቢ ዘር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ከእናንተ መካከል የአንዳችሁ የአካል መገጣጠሚያዎች ሁሉ ሰደቃህ ጸንቶባቸው ያነጋሉ፡፡ እያንዳንዱ ተስቢሕ (ሱብሐነልላህ) ሰደቃህ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተሕሚድ (አልሐምዱሊላህ) ሰደቃህ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተህሊል (ላኢላህ ኢልለሏህ) ሰደቃህ ነው፡፡ እያንዳንዱ ተክቢር (አላሁ አክበር) ሰደቃህ ነው፡፡ በመልካም ማዘዝ ሰደቃህ ነው፡፡ ከመጥፎ መከልከልም ሰደቃህ ነው፡፡ በአድ ዱሓ የሚሰግዳቸው ሁለት ረከዐዎች እነዚህን ሁሉ (በምንዳ) ያብቃቁታል (ይስተካከሉታል)፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (720) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሙሰሊም በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባቸው ከዓኢሻህ -አላህ መላከም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- አንድ ሰው ከሶሰት መቶ ስልሳ መገጣጠሚያዎች በርግጥ የተፈጠረ መሆኑንና በትንሳኤ እለት በእነዚህ መገጣጠሚያዎች ሰደቃ ይዞ የመጣ በዚያን ወቅት ራሱን ከጀሃነም እሳት ነጻ አውጥቶ እንሚሄድ ያብራሩበትን ሐዲሥ ዘግበዋል፡፡

## ወቅቱ፡ -

የአድ-ዱሓ ሰላት ወቅት ጸሐይ ወገግ ብላ ከወጣችብት ወይም ሰላት መስገድ ክልክል ከሆነበት ጊዜ በኋላ ካለው ጊዜ አንስቶ ይጅምራል፡፡

የዙህር ሰላት ወቅት ከመግባቱ ከአስር ደቂቃ በፊት ይጠናቀቃል፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** ከዐምር ኢብን ዐንበሰህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“የሱብሒ ሰላትን ስገድ ከዚያ ጸሐይ ከወጣችበት በጣም ከፍ እስከምትልበት ጊዜ ድረስ ከሰላት ተቆጠብ፡፡ ከዚያ ስገድ፡፡ ይህች ሰላት ጥላ ከራሳ ይዘት ከፍ እስከሚል ድረስ መላእክት የሚታደሙባት የሆነች ሰላት ነች፡፡ ከዚያ ከሰላት ተቆጠብ፡፡ በዚህ ጊዜ ጀሃነም ትፋፋማለች፡፡…”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (832) ላይ ዘግበውታል፡፡

## በላጩ ወቅት፡ -

**በመጨረሻው ወቅት ላይ ነው፡፡** ይህም ጊዜው በሚሞቅበት ወቅት ነው፡፡

ለዚህ ማስረጃው፡-ዘይድ ኢብን አርቀም -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደስተላለፉት ነቢ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“የጸጸት ተመላሾች ሰላት ጊዜው በሚሞቅበት ወቅት ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (748) ላይ ዘግበውታል፡፡

ኢብን ባዝ -አላህ ይዘንላቸው-፡- «...ይህ በወቅቱ መጨረሻ ላይ መስገዳቸው በላጭ ከሚሆኑ ሰላቶች መካከል አንዱ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ ፈታዋ አል-ኢስላሚይየህ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 515፡፡

## የረከዐዎቹ ብዛት፡-

ትንሹ የአድ-ዱሓ ሰላት ረከዐህ ሁለት ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃው ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት የአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ላይ፣ «ወዳጄ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሶስት ነገሮች ላይ አደራ ብለውኛል» ካሉ በኋላ፣ «በአድ-ዱሓ ሁለት ረከዐዎች» የሚል ጠቅሰዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1981)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (721) ላይ ዘግበውታል፡፡

በስምንት ረከዐዎች ላይ የገደበውን ለመቃረን አብዛኛው ረከዐወህ ምንም ወሰን የለውም፡፡ ስለዚህ የሚሰግደው ሰው ከፈለገ ከስምንት በላይ መጨመር ይችላል፡፡ ይህም ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አራት ረከዐህ ይሰግዱ ነበር፡፡ አላህ እስከሻው ድረስም ይጨምሩ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (719) ላይ ዘግበውታል፡፡



ከአደ-ዱሓ ሰላት ትሩፋት የተነሳ ይህን ሰላት መስገድ ነቢዩ (የአላህ ሰላምታና እዝነት በእሳቸው ላይ ይሁን) ለሰሓቦቻቸው አደራ ያሉት ሰላት ነው፡፡

## አራተኛ፡- የዙህር ሰላት ወቅት



በውስጡ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡-

### አንደኛው ጉዳይ፡- ከዙህር በፊትና በኋላ የሚሰገዱ ሱንናዎች

ከዚህ በላይ በፍላጎት በሚፈጸሙ ነቢያዊ ፈለጎች ርዕስ ላይ ከዙህር በፊት አራት ረከዐህ፣ ከዙህር ሰላት በኋላ ሁለት ረከዐህ ሰላቶች መስገድ እንዳለ ተመልክተናል፡፡ ለዚህም የዓኢሻህ፣ የኡምሙ ሐቢባህ፣ የኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- ሐዲሥ በማስረጃነት ተቀምጧል፡፡

### ሁለተኛው ጉዳይ፡- የዙህር ሰላት ላይ የመጀመሪያውን ረከዐህ መቆም ከሁለተኛው ረከዐህ መቆም ማስረዘም ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው፡፡

አቢ ሰዒይድ አል-ኹድሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ለዙህር ሰላት ኢቃም ይደረጋል፡፡ የሚሄድ የፈለገ ወደበቂዕ ይሄዳል፡፡ ጉዳዩን ከፋጸመ በኋላ ዉዱእ ያደርጋል፡፡ ከዚያ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የሚያረዝሙት የመጀመሪያው ረከዐህ ላይ ሳሉ ዘንድ ይመጣል፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (545) ላይ ዘግበውታል፡፡

ስለዚህ አንድ የዙህር ሰላትን የሚያሰግድ ሰው የመጀመሪያውን ረከዐህ ማርዘሙ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ሰውዬው ለብቻው ቢሰግድም እንደሁ ነው፡፡ ማንኛዋም ሴት ብትሆን ለዙህር ሰላት ስትቆም ይህን ማድረግ አለባት፡፡ ይህ እየተረሳ የመጣ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ አላህ ነቢያዊ ፈለግን በተሟላ ሁኔታ የምንተገበርና የምንጠብቅ እንዲያደርገን እንለምነዋለን፡፡


**ሶስተኛው ነጥብ፡- በጣም ሞቃትማ በሚሆንበት ጊዜ ሙቀቱ ጋብ እስከሚል ድረስ ማዘግየት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡**

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሙቀቱ ከበረታ ሰላትን አቀዝቅዙ፡፡ የሙቀት በርቱነት ከጀሃነም እስትንፋስ ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (533፣534)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (615) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሸይኽ ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ጸሐይ በበጋ ወቅት ስድሰት ሰአት ላይ ከአናት ታዘንፋለች፣ የዐሰር ወቅት በግምት አስር ሰአት ተኩል ላይ ነው ብለን ብንገምት፣ የማቀዝቀዣው ሰአት ወደአስር ሰአት ገደማ ነው ማለት ነው፡፡» አል-ሙምቲዕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 104፡፡

ማቀዝቀዙ በሕብረት ለሚስግዱም ሆነ ለብቻው ለሚሰግድ ሰው አጠቃላይ ነው፡፡ ሸይኻችን ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው- ይህን መርጠዋል፡፡ በዚህ ሥር ሴቶችም ይጠቃለላሉ፡፡ ሴቶችም ሙቀቱ ብርቱ በሚሆንበት ወቅት ማቀዝቃዝ ነቢያዊ ፈለግ መከተል ተደርጎ ይቆጠርላቸዋል፡፡ ይህም አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ያስተላለፉት ሐዲሥ ሁሉንም የሚያጠቃልል ስለሆነ ነው፡፡





- ነቢዩ (የአላህ ሰላምታና እዝነት በእሳቸው ላይ ይሁን)፤ «ሰላት ብርሃን ነው፡፡» ብለዋል፡፡ ይህ ማለት ለናንተ በምድራዊው ዓለምና በወዲያኛው ዘላለማዊ ዓለም ብርሃን ነው ማለት ነው፡፡

## አምስተኛ፡- የዐስር ሰላት ወቅት



ከዚህ በላይ ከግዴታ ሰላቶች በፊት ስለሚሰገዱ የሱንና ሰላቶች ስናወሳና ስናብራራ ከዐስር በፊት ምንም አላልንም፡፡

ሸይኹ-ል-ኢስላም ኢብን ተይሚያህ -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ከዐስር በፊትን በተመለከተ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከዐስር በፊት ይሰግዱ ነበር ብሎ የተናገረ አንድም የለም፡፡ አለ ከተባለም በሐዲሡ ላይ ድክምት እንዲውም ስህተት የሆነ ካልሆነ በስተቀር ምንም የለም፡፡» ብለዋል፡፡ አል-ፈታዋ ቅጽ ፡ 23 ገጽ፡ 125፡፡

ትክክለኛው -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፡- ከዐስር በፊት የተገደበ የሱንና ሰላትን መስገድ ነቢያዊ ፈለግ አይደለም፡፡ ስለዚህ ይህ ጉዳይ ያልተገደበ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት ሰላት መስገድ ክልክል ከሆነበት ወቅት ውጭ ልክ በማንኛውም ወቅት እንደሚሰገደው የፈለገ ሰው ሁለት ረከዐህ ወይም ከዚያ በላይ በራሱ ፍላጎት ሊሰግድ ይችላል፡፡ ነገር ግን የተገደበ የሆነ ሰላት ከዐስር ሰላት በፊት የለም፡፡

## የንጋትና የምሽት አዝካሮች

የጠዋትና የምሽት አዝካሮች ወቅት ከመቼ ይጀምራል?

## የንጋት አዝካር ወቅት፡-

ትክክለኛው ጉሕ ከቀደደበት ወይም የፈጅር ሰላት ከገባበት ጊዜ አንስቶ ይጀምራል፡፡ ሙአዚኑ ለፈጅር ሰላት አዛን ካደረገበት ጊዜ አንስቶ የጠዋት ዚክር ይጀምራል፡፡ ይህ የአጠቃላይ ዑለሞች -ለሁሉም አላህ ይዘንላቸው- የጋራ ሃሳብ ነው፡፡

## የምሽት አዝካር ወቅት፡-

**ይበልጥ ሚዛን የሚደፋው -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፣** ከዐስር በኋላ ጸሐይ እስከምትጠልቅበት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ይጀምራል የሚለው ነው፡፡ ጸሐይ ከጠለቀች በኋላም ማለት ይቻላል (ይበቃል)፡፡

## ስድስተኛ፡- የመግሪብ ሰላት ወቅት



በውስጡ በርካታ ነጥቦች አሉ፡-

**የመጀመሪያው ነጥብ፡-** በመግሪብ የመጀመሪያ ወቅት ላይ ሕጻናትን መሰብሰብ

**ሁለተኛው ነጥብ፡-** በመግሪብ የመጀመሪያው ወቅት ላይ በሮችን መዝጋትና -በእጅጉ የላቀውን- አላህን ማውሳት፡፡

እነዚህ ሁለት ተግባራት መፈጸም ከሸይጣኖችንና ከአጋንንት መጠበቂያ ነው፡፡ በመግሪብ የመጀመሪያው ወቅት ሕጻናትን መሰብሰብ በዚያ ወቅት ከሚሰራጩ ሸይጣኖች ሕጻናቱን መጠበቂያ ነው፡፡ በዚሁ ወቅት ላይ በሮችን መዝጋትን -እጅግ የላቀውን- አላህን ማውሳት እንዲሁ መጠበቂያ ነው፡፡ ስንት ሕጻናት ናቸው በዚህ ወቅት ሳይከለከሉ በሸይጣኖች የተለከፉት፡፡ ይህ ዓይነቱ ኢስላም ለሕጻናቱና ለቤታችን ያደረገው ትልቅ እንክብካቤና ጥበቃ እንዴት ያስደስትና ያስገርም!



**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ጃቢር ኢብን ዐብዲላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“የምሽቱ ክፍል ሲሆን -ስታመሹ- ሕጻናቶቻችሁን ሰብስቡ፡፡ በርግጥ ሸይጣኖች በዚህ ጊዜ ይሰራጫሉ፡፡ ከምሽቱ የተወሰነ ጊዜ ሲያልፍ ተዉዋቸው፡፡ በሮችን ዝጉ፡፡ አላህንም አውሱ፡፡ በርግጥ ሸይጣን የተዘጋን ቤት አይከፍትም፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3304)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2012) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሕጻናትን መሰብሰብና በሮችን መዝጋት የሚወደድ ተግባር ከመሆኑ አንጻር ነው ተግባራዊ የሚሆነው፡፡ *ፈታዋ ለጅነቱ አድ-ዳኢመህ ቅጽ ፡ 26 ገጽ ፡ 317፡፡*

## ሶስተኛው ነጥብ፡- <u>ከመግሪብ ሰላት በፊት ሁለት ረከዐዎችን መስገድ</u>

ዐብዱላህ ኢብን መገፍፈል -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ከመግሪብ በፊት ስገዱ” አሉና ሰዎች ነቢያዊ ፈለግ አድርገው እንዳይዙት ጠልተው በሶስተኛው ላይ፣ “ለፈለገ ሰው፡፡” አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲ ዘገባ ቁር (1183) ላይ ዘግበውታል፡፡

**እንዲሁ በእያንዳንዱ አዛንና ኢቃመህ መካከል ሁለት ረከዐዎችን መስገድ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡**

እነዚህ ሁለት ረከዐዎች እንደፈጅር፣ ዙህር ዓይነት ከሆኑ ብርቱ የሆኑ የሱንና ሰላቶችን መስገድ እነዚህን ሰላቶች ያብቃቃል፡፡ ወይም ሰውዬም መስጂድ ተቀምጦ ከሆነና ሙአዚኑ ለዐስር ወይም ለዒሻእ ሰላት አዛን ያደረገ እንደሆነ ተነስቶ ሁለት ረከዐዎችን መስገዱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዐብዱላህ ኢብን አል-መገፍፈል አል-ሙዘኒይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-ሶስት ጊዜ፣ **“በእያንዳንዱ ሁለት አዛኖች መካከል ሰላት አለ፡፡”** አሉና በሶስተኛው ላይ፣ “ለፈለገ ሰው” አሉ፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (624)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (838) ላይ ዘግበውታል፡፡

ከመግሪብ በፊትና በእያንዳንዱ ሁለት አዛኖች መካከል የሚሰገዱት ሁለት ረከዐዎች ብር እንደሆኑት የሱንና ሰላቶች አይደሉም። ምናልባትም አንዳንድ ጊዜ ሊተዉ ይችላሉ። ለዚህም ነው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሐዲሣቸው ላይ ሰዎች ነቢያዊ ፈለግ አድርገው እንዳይዙት በመጥላት **"ለፈለገ ሰው"** ያሉት።

## አራተኛው ነጥብ፡- <u>ከዒሻእ ሰላት በፊት መተኛት ይጠላል</u>


አቢ በርዘተ-ልአስለሚይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዒሻእን ማዘግየት ይወዱ ነበር።» ብለዋል። እንዲህም ብለዋል፣ «ከእሷ -(ከዒሻእ)- በፊት መተኛትንና ከእሷ በኋላም ንግግርን ይጠሉ ነበር።» ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (599)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (647) ላይ ዘግበውታል።

ከመግሪብ ወቅት ማለትም ከዒሻእ በፊት መተኛት የተጠላበት አብይ ምክንያት (ምስጢር) መተኛቱ የዒሻእ ሰላትን ያሳልፋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።



◆ በቀንና በሌሊት ንስሐ ማድረግ ለአንድ የአላህ ባሪያ የሁሉ ነገር ቁልፍ ነው። በንስሐ ውስጥ ይህ የአላህ ባሪያ ወደአላህ የሚያደርገው ጉዞ የተስተካከለ እንዲሆን የሚረዳ ምክንያት የሆነ ነገር አለ። ነቢዩ (የአላህ ሰላምታና እዝነት በእሳቸው ላይ ይሁን)፣ «የላቀ ልእልና ክብር የተገባው አላህ በቀን ውስጥ ሃጢአት የፈጸመ ሰው ንስሐ አድርጎ ወደርሱ ይመለስ ዘንድ እጆቹን ሌሊት ላይ ይዘረጋል። ሌሊት ላይ ሃጢአት የፈጸመ ሰው ንስሐ አድርጎ ወደርሱ ይመለስ ዘንድ እጆቹን ቀን ላይ ይዘረጋል።» ብለዋል።

## ሰባተኛ፡- የዒሻእ ሰላት ወቅት



**በውስጡ በርካታ ነጥቦች አሉ፡-**

**አንደኛው ነጥብ፡-** <u>ከዒሻእ ሰላት በኋላ ንግግርና ተሰብስቦ መቀመጥ ይጠላል</u>

ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የአቡ በርዘት-ልአስለሚይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ውስጥ፣«ከእሷ -(ከዒሻእ)- በፊት መተኛትንና ከእሷ በኋላም ንግግርን ይጠሉ ነበር፡፡» የሚል ሰፍሯል፡፡

**-አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው- የተጠላበት ምክንያት፡-** ሰውዬው እንቅልፍ መተኛቱ ይዘገያል፡፡ ስለዚህም የሱብሒ ሰላት የመጀመሪያ ወቅት ወይም ሌሊት ላይ ተነስቶ የመስገድ ልምዱ እንዳያልፈው ስለሚፈራ ነው፡፡

**ሁለተኛው ነጥብ፡- ተከትለው በሚሰግዱ ሰዎች ላይ ምንም ችግር የማያስከትል እስከሆነ ድረስ በዒሻእ ሰላት ላይ በላጩ ሰላቱ መዘግየቱ ነው፡፡**

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዓኢሸህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ከእለታት አንድ ቀን ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አብዛኛው የሌሊት ክፍል እስከሚያልፍና መስጂድ ውስጥ ያሉት ሁሉ እስኪተኙ ድረስ ብቅ ሳይሉ ቀሩ፡፡ ከዚያ ሊሰግዱ ወጡና፣ "በሕዝቦቼ ላይ ማስቸገር ባይሆንበኝ ኖሮ በርግጥ ወቅቱ ይህ ነው፡፡" አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (638) ላይ ዘግበውታል፡፡

በዚህ ላይ ነቢያዊ ፈለጉ የሴት ሙብትን በተመለከተ በጀማዐህ ሰላት የልተሳሰረች በመሆኗ ችግር እስከሌለባት ድረስ የዒሻእ ሰላትን ማዘግየቷ ነው፡፡ እንደዚሁ አንድ ወንድ ለምሳሌ በጉዞ ላይ ወይም በሌላ ምክንያት በጀማዐህ ከመስገድ ጋር ያልተሳሰረ ከሆነ የዒሻእ ሰላትን ማዘግየቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**በየሌሊቱ የአል-ኢኽላስን ምዕራፍ ማንበብ (መቅራት) ከሱንናዎች መካከል አንዱ ሱንና ነው፡፡**

ከአቢ አድ-ደርዳእ (አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው) እንደተላለፈው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)፤ **‹‹ከመካከላችሁ አንዳችሁ በአንድ ሌሊት የቁርአንን ሲሶ ከመቅራት ይሳነፋልን?››** አሉ፡፡ ሰሓቦችም፤ «እንዴት ነው የቁርአንን ሲሶ ሊቀራ የሚችለው?» አሉ፡፡ እሳቸውም፤ **‹‹ቁል ሁወ-ልላሁ አሐድ የቁርአንን ሲሶ ትስተካከላለች፡፡››** አሉ፡፡ ሙስሊም (811)፣ ይህንኑ ሐዲሥ ቡኻሪ ከአቢ ሰዒድ አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይቀበላቸው በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5015) ዘግበውታል፡፡



## የመኝታ ነቢያዊ ፈለጎች

### መኝታ በርካታ ነቢያዊ ፈለጎች አሉት፡-

### 1 በመኝታ ወቅት በሮችን መዝጋት፡-



ጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ስትተኙ መብራቶችን አጥፉ፣ በሮችን ዝጉ፣ ማጠጫዎችን አስደግፉ፣ ምግብንና መጠጥን ሸፍኑ፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5624)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2012) ላይ ዘግበውታል፡፡

በሮች እንዲዘጉ የታዘዘበት ምስጢሩ፡- ከዚህ በላይ በጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ላይ እንደሰፈረው ሸይጣኖች እንዳይገቡ ነው፡፡ በዚህ ሐዲሥ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ብለዋል፡፡

**“በሮችን ዝጉ፣ የአላህ ሥም አውሱ፣ በርግጥ ሸይጣን የተዘጋ በርን አይከፍትም፡፡”** ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5623)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2012) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 2 ከመተኛት በፊት እሳትን ማጥፋት



ከዚህ በላይ በሰፈረው የጃቢር -የአላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ስትተኙ መብራቶችን አጥፉ፡፡” ብለዋል፡፡

ኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን፣ “በምትተኙበት ወቅት እሳትን በቤታችሁ ውስጥ አትተዉ፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2015) ላይ ዘግበውታል፡፡

ስለዚህ እዚህ ላይ እንዲያበራ ክር ያለበት ኩራዝ ወይም ማሾ ለአብነት ተጠቀሰ እንጂ ከዚህ ጋር በማዛመድ ማንኛውም ለቃጠሎ ምክንያት የሚሆንን ነገር በዚህ ሥር በማካተት መጥፋት ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንደነገሩን እሳት በርግጥ ለኛ ጠላት ነው፡፡

በዚህ መሰረትም፡- አንድ ሰው እሳቱ ምንም እንደማይለው ደህንነት የሚሰማው ከሆነና በዙሪያው እሱን የሚያባብስ ነገር የሌለ መሆኑን ካረጋገጠ በዚህ ጊዜ መተዉ ምንም ችግር የለውም፡፡ ድንጋጌውም በመኖሩና ባለመኖሩ ላይ ነው፡፡


## 3 ከመተኛት በፊት ዉዱእ ማድረግ



اللهم انى اسلمت وجهى اليك

በራእ ኢብን ዓዚብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“መኝታህ ላይ ለመጋደም ስትፈልግ ለሰላት እንደምታደርገው ዉዱእ አድርግ፡፡ ከዚያ በቀኝ ጎንህ ተጋደም፡፡ ከዚያ አልላሁምመ አስለምቱ ወጅሂ ኢለይከ... የሚለው በል፡፡”** አሉ፡፡ ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (247)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2710) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 4 የሚተኛበትን ፍራሽ ከመተኛቱ በፊት ማራገፍ



بِاسْمِكَ رَبِّ وَضَعْتُ جَنْبِي

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “አንዳንችሁ ወደመኝታው ካመራ በውስጠኛው ሽርጡ ፍራሹን ያራግፍ፡፡ በእሱ ላይ ምን እንደተተወ አያውቅም፡፡ ከዚያም ቢስሚከልላሁምመ ወደዕቱ ጀንቢ ይበል... ይበል፡፡” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6320)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2714) ላይ ዘግበውታል፡፡

ከዚህ በላይ ከሠፈረው በውስጠኛ ሽርጡ ፍራሽን ማራገፍ ነቢያዊ ፈለግ እንደሆነ ግልጽ ይሆንልናል፡፡ በዚህም መሰረት ማራገፉ ሶስት ጊዜ ሲሆን የአላህን ስም ማውሳትም ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

በላጩ በውሰጠኛው ልብስ ማራገፉ ነው፡፡ ከዑለሞች መካከል በማንኛውም ነገር ማራገፍ ይቻላል ያሉ ሲኖሩ ዋናው ቁም ነገሩ የፍራሹ መራገፍ ነው፡፡ ይህን ካሉት ዑለሞች መካከል ኢብን ጀብረይን -አላህ ይዘንላቸው- ሲሆኑ እሳቸውም፣ «በውስጥ ሽርጥ ማራገፍ መስፈርት አይደለም፡፡ ፍራሹን ሁሉ የሚያራግፈው ቢሆንም ወይም በጥምጣም ወይም ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ቢያራግፈው የታሰበው ተፈጻሚ ሆኗል፡፡» ብለዋል፡፡ የእሳቸውን ፈታዋ በቁጥር (2693) ይመልከቱ፡፡

## 5 በቀኝ ጎን መተኛት

## 6 ቀኝ መዳፉን በቀኝ ጉንጩ ሥር ማስቀመጥ

اللَّهُمَّ اني أَسْلَمْتُ وَجْهِي إِلَيْكَ

ለነዚህ ለሁለቱ ማስረጃ የሚሆነው ሐዲሥ አል-በራእ ኢብን ዓዚብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-



፣ **“መኝታህ ላይ ለመጋደም ስትፈልግ ለሰላት እንደምታደርገው ዉዱእ አድርግ፡፡ ከዚያ በቀኝ ጎንህ ተጋደም፡፡ ከዚያ አልላሁምመ አስለምቱ ወጅሂ ኢለይከ...የሚለው በል፡፡”** አሉ፡፡ ብለዋል፡ ፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (247)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2710) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሑዘይፈህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ምሽት ላይ ለመተኛት ወደመኝታ ሥፍራቸው ላይ ሲተኙ መዳፋቸውን ከጉንጫቸው ሥር ያደርጉ ነበር፡፡ » ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6314) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 7 የመኝታ አዝካሮችን ማለት



ለመኝታ ከቁርኣንና ነቢያዊ ፈለግ የተወሰዱ አዝካሮች አሉ፡፡

### 1 ከቁርኣን ከተወሰዱ፡-

#### 1 አየቱ-ልኩርሲይን መቅራት

በመኝታ ወቅት አየቱ-ልኩርሲይን መቅራት ነቢያዊ ፈለግ ከመሆኑ በተጨማሪ ለሚለው ሰው እስኪያነጋ ድረስ ከሸይጣን መጠበቂያውም ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** የአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ከዘካ ንብረት ላይ ከሚሰርቀው ጋር የነበራቸው ታሪክ ነው፡፡ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ምርኮኛህ ትናንትና ምን ሰራ?”** አሉኝ፡፡ እኔም፡- የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አላህ በርሱ ሊጠቅመኝ የሚችልበትን ቃላት ሊያስተምረኝ ወሰነ፡፡ እንዲሄድ አደረግኩት አልኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ **“ምንድን ነች እሷ?”** አሉኝ፡፡ እኔም፡- «ወደመኝታህ ከመጣህ አየቱ-ልኩርሲይን

{اللَّهُ لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ} አንቀጹን እስከምትጨርስ ድረስ ቅራ፡፡ ካንተ ላይ በርግጥ ከአላህ የሆነ ጠባቂ ፈጽሞ አይለይም፡፡ እስከምታነጋ ድረስም ሸይጣን አይቀርብህም፡፡ እነርሱ በመልካም ነገር ላይ ተነሳሽ የሆኑ ናቸው፡፡» አለኝ አልኳቸው፡፡ ነቢዩም -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“እሱ በጣም ውሸታም ሆኖ ሳለ እውነቱን ነግሮሃል፡፡ አባ ሁረይራህ ሆይ! ለሶስት ቀናት ማንን ታናግር እንደነበር ታውቃለህን?”** አሉኝ፡፡ እኔም፡- ፈጽሞ አላውቅም አልኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ “ያ ሸይጣን ነው፡፡” አሉኝ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2311) በሐዲሡ ላይ ሃሳብ ሰጥተው ሲዘግቡት አን-ነሳኢይ በአስ-ሱነኑ-ልኩብራ መጽሐፋቸው በቁጥር (10795) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 2 ከአል-በቀራህ ምዕራፍ የመጨረሻዎቹን ሁለት አንቀጾች መቅራት

አቢ መስዑድ አል-አንሳሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"በአንድ ምሽት እነዚህ ሁለት አንቀጾች ከአል-በቀራህ ምዕራፍ የቀራ ከሁሉ ነገር ይብቃቁታል፡፡"** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (4008)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (807) ላይ ዘግበውታል፡፡ ሁለቱ የአል-በቀራህ ምዕራፍ የመጨረሻ አንቀጾች በተለይ በመኝታ ላይ ከሚባሉት አዝካሮች መካከል የሚቀመጡ ሳይሆን በምሽት ላይ የሚቀሩ የቁርአን አንቀጾች ናቸው፡፡ እነዚህን ሁለት አንቀጾች ምሽት ላይ ያልቀራቸውና መኝታው ላይ ያስታወሳቸው ሰው በዚያ ወቅት ይቅራቸው፡፡

**(ይብቃቁታል)** በሚለው ቃል ትርጓሜ ላይ ዑለሞች በሃሳብ ተለያይተዋል፡፡ ይኸውም፡-

ከሌሊት ሰላት ይብቃቁታል ማለት ነው የተባለ ሲሆን ከሸይጣን ይከለክሉታል ማለት ነው ተብሏልም፡፡

እንደዚሁ ከስህተት ይከላከሉታል ተብሏል፡፡ ሁሉም እንደሚሆን አን-ነወዊይ -አላህ ይዘንላቸው- አስፍረዋል፡፡ ሸርሑ አን-ነወዊይ ሊ-ሙሰሊም የአል-ፋቲሐና የአል-በቀራህ ምዕራፍ መደምደሚያዎች... በሚለው ምዕራፍ ሥር ሐዲሥ ቁጥር (808)ን ይመልከቱ፡፡

### 3 የአል-ኢኽላስንና የአል-ሙዐውዊዘተይን በመዳፎች ላይ መቅራት፣ በመዳፎቹ ላይም እትፍ እትፍ ማለት ከዚያ ሶስት ጊዜ በእነሱ (በመዳፎቹ) ሰውነትን ማበስ፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በየምሽቱ ወደመኝታቸው ሲሄዱ ሁለቱን መዳፎቻቸውን ይሰበስቡና እትፍ እትፍ ይለባቸዋል፡፡ በውስጣቸውም፣

{قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ} وَ {قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ الْفَلَقِ} وَ {قُلْ أَعُوذُ بِرَبِّ النَّاسِ}

**"ቁል ሁወ-ልላሁ አሐድ"**ን፣ **"ቁል አዑዉዙ ቢርብቢ-ልፈለቅ"**ንና **"ቁል አዑዉዙ ቢረብቢ-ንናስ"**ን ይቀሩባቸዋል፡፡ ከዚያም የቻሉትን ያህል ሰውነታቸውን ያብሱባቸዋል፡፡ ከራሳቸው፣ ከፊታቸውና ከፊት ለፊት ካለው ሰውነታቸውም ማበስን ይጀምሩባቸዋል፡፡ ይህን ሶስት ጊዜ ይፈጽሙ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5017) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ከዚህ ካሳለፍነው ሐዲሥ የምንቀስመው፡-** ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ይህን ነቢያዊ ፈለግ ተግባራዊ ያደርጉ እንደነበር ነው፡፡ ይህንንም **‹‹በየምሽቱ››** ብለው ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተናገሩት ሐዲሥ ላይ እናገኛለን፡፡ ይህን ነቢያዊ ፈለግ ይተገብሩ ነበር ማለት መዳፎቻቸውን ሰብስበው ከዚያ የአል-ኢኽላስንና የአል-ሙአውዊዘተይንን ምዕራፎች ካነበቡ በኋላ እትፍ እትፍ ይሉባቸዋል ከዚያ ከራሳቸውና ከፊታቸው በመጀመር የቻሉትን የሰውነታቸውን አካል ያብሱባቸዋል፡፡ ይህንንም ሶስት ጊዜ ይፈጽሙ ነበር፡፡

### 4 የአል-ካፊሩዉንን ምዕራፍ ማንበብ

ዑርወህ ኢብን ነውፈል ከአባታቸው -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ለነውፈል፣ **"{قُلْ يَا أَيُّها الْكَافِرُونَ}ን ቅሩ፡፡ በማጠናቀቂያዋ ላይም ተኛ፡፡ በእርግጥ እሷ ከሺርክ ነጻነት ነች፡፡"** ብለዋቸዋል፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አሕመድ (21934)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (5055)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (3403) ላይ የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይም -አላህ ይዘንላቸው- የሐዲሡን በመልካም ደረጃ ላይ መገኘት አረጋግጠዋል፡፡

## 2 ከነቢያዊ ፈለጎች የተሰወዱ ዱዓዎች በርካታ ናቸው፡፡ ከእነርሱ መካከልም፡-



1 **بِاسْمِكَ اللَّهُمَّ أَمُوتُ وَأَحْيَا**

**"ቢስሚከልላሁ አሙቱ ወአሕያ፡፡** /አላህ ሆይ! በስምህ እሞታለሁ፣ ሕያው እሆናለሁም፡፡/" ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6324) ላይ ከሑዘይፋህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2 **اللَّهُمَّ خَلَقْتَ نَفْسِي وَأَنْتَ تَوَفَّاهَا, لَكَ مَمَاتُهَا وَمَحْيَاهَا، إِنْ أَحْيَيْتَهَا فَاحْفَظْهَا، وَإِنْ أَمَتَّهَا فَاغْفِرْ لَهَا، اللَّهُمَّ إِنِّي أَسأَلُكَ الْعَافِيَةَ**

**"አልላሁምመ አንተ ኸለቅተ ነፍሲ ወአንተ ተወፉሃ ለከ መማቱሃ መወሕያሃ ኢን አሕየይተሃ ፈሕፈዝሃ ወኢን አመትተሃ ፈግፊር** ለሃ አልላሁምመ ኢንኒ አስአሉከ-ልዓፊየህ፡፡/አላህ ሆይ! ነፍሴን ፈጠርካት፣ አንተው ነህ የምትገድላት፣ መሞቻዋም፣ ሕያውነቷም ላንተ ነው፡፡ ሕያው ካደረግካት ጠብቃት፡፡ ከገደልካት ምሕረት አድርግላት፡፡ አላህ ሆይ! በርግጥ ጤንነትን እጠይቅሃለሁ፡፡/" ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2712) ላይ ዘግበውታል፡፡

3 **اللَّهُمَّ رَبَّ السَّمَاوَاتِ وَرَبَّ الأَرْضِ وَرَبَّ الْعَرْشِ الْعَظِيمِ ، رَبَّنَا وَرَبَّ كُلِّ شَيْءٍ, فَالِقَ الْحَبِّ وَالنَّوَى , وَمُنْزِلَ التَّوْرَاةِ وَالإِنْجِيلِ وَالْفُرْقَانِ ، أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ كُلِّ شَيْءٍ أَنْتَ آخِذٌ بِنَاصِيَتِهِ اللَّهُمَّ أَنْتَ الأَوَّلُ فَلَيْسَ قَبْلَكَ شَيْءٌ , وَأَنْتَ الآخِرُ فَلَيْسَ بَعْدَكَ شَيْءٌ , وَأَنْتَ الظَّاهِرُ فَلَيْسَ فَوْقَكَ شَيْءٌ ، وَأَنْتَ الْبَاطِنُ فَلَيْسَ دُونَكَ شَيْءٌ ، اقْضِ عَنَّاالدَّيْنَ وَأَغْنِنَا مِنَ الْفَقْرِ**

**"አልላሁምመ ረብበ-ስሰማዋቲ ወረብበ-ልአርዲ ወረብበ-ልዐርሺ-ልዐዚይም ረብበና ወረብበ ኩልሊ ሸይእ ፋሊቁ-ልሐብቢ ወ-ንነዋ ሙንዚለ-ትተውራቲ ወልኢንጂሊ ወልፉርቃን አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ኩልሊ አንተ ኣኺዙን ቢናሲየቲሂ አልላሁምመ አንተ-ልአውወሉ ፈለይሰ ቀብለከ ሸይኡን ወአንተ-ልኣኺሩ ፈለይሰ በዕደከ ሸይኡን ወአንተ-ዝዛሂሩ ፈለይሰ ፈውቀከ ሸይእ ወአንተ-ልባጢኑ ፈለይሰ ዱዉነከ ሸይእ ኢቅዲ ዐንና-ድደይነ አግኒና ሚን-ልፈቅር፡፡** /የሰማያት፣ የምድር፣ የላቀው ዐርሽ ጌታ፣ ጌታችንና የሁሉም ነገር ጌታ የሆንከው፣ አንተ ፍሬንና በቆልተን ፈልቃቂ፣ ተውራትን፣ ኢንጂልንና ቁርኣንን የምታወርድ የሆንከው

አላህ ሆይ! አንተ አናቱን ያዥ የምትይዝ በሆንከው ባንተ ከሁሉም ነገር ተንኮል እጠበቃለሁ፡፡ አላህ ሆይ! አንተ የመጀመሪያው ነህ ካንተ በፊት ምንም ነገር የለም፡፡ አንተ ግልጹ ነህ ከበላይህ ምንም ነገር የለም፡፡ አንተ ስውሩ ነህ ካንተ ውጭ ምንም ነገር የለም፡፡ እዳችንን ክፈልልን፡፡ ከድህነትም አብቃቃን፡፡/" ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2713) ላይ ዘግበውታል፡፡

4 **بِاسْمِكَ رَبِّ وَضَعْتُ جَنْبِي وَبِكَ أَرْفَعُهُ إِنْ أَمْسَكْتَ نَفْسِي فَارْحَمْهَا وَإِنْ أَرْسَلْتَهَا فَاحْفَظْهَا بِمَا تَحْفَظُ بِهِ عِبَادَكَ الصَّالِحِينَ**

**"ቢስሚከ ረብቢ ወደዕቱ ጀንቢ ወቢከ አርፈዑህ ኢን አምሰክተ ነፍሲ ፈርሐምሃ ወኢን አርሰልተሃ ፈሕፈዝሃ ቢማ ተሕፈዙ ቢሂ ዒባደከ-ስሳሊሒይን፡፡**/ ጌታዬ ሆይ! በስምህ ጎኔን አሳረፍኩ፡፡ ባንተም አነሳዋለሁ፡፡ ነፍሴን ከያዝክ እዘንላት፡፡ ከለቀቅካት መልካም ባሮችህን በምትጠብቅበት ጠብቃት፡፡/" ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6302)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2714) ላይ ዘግበውታል፡፡

4 **الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي أَطْعَمَنَا وَسَقَانَا، وَكَفَانَا وَآوَانَا، فَكَمْ مِمَّنْ لاَ كَافِيَ لَهُ وَلاَ مُؤْوِيَ**

**"አልሐምዱሊልላሂ-ልለዚ አጥዐመና ወሰቃና ወከፋና ወአዋና ፈከም ሚምመን ካፊየ ለሁ ወላ መእዊ፡፡**/ለመገበን፣ ላጠጣን፣ ለጠበቀን፣ መጠጊያ ለሰጠን ለዚያ ለአላህ ምስጋና ይሁን፡፡ የሚጠብቀውም ሆነ መጠጊያ የሌለው ስንቱ ይኖር ይሆን፡፡/" ሙሉ ሐዲሡን አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደመኝታቸው ሲሄዱ፣ "አልሐምዱሊልላሂ..." ይሉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2715) ላይ ዘግበውታል፡፡

6 **اللَّهُمَّ قِنِي عَذَابَكَ يَوْمَ تَبْعَثُ عِبَادَكَ**

**"አልላሁምመ ቂኒ ዐዛበከ የውመ ተብዐሡ ዒባደክ፡፡**/አላህ ሆይ! ባሮችህን በምትቀሰቅስበት ቀን ካለው ቅጣትህ ጠብቀኝ፡፡/" ሐዲሡን አሕመድ በሐዲሥ ቁጥር (18660) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይም ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ፡ 869፡፡

7 **ሰላሳ ሶስት ጊዜያት ተስቢሕና ተሕሚድ (አላህም ከከንቱና ውድቅ ከሆኑ ንግግሮች ማጥራትና አላህን ማመስገን) እንዲሁም ሰላሳ አራት ጊዜ ተክቢር (አላህን ማላቅ)፡፡**

አንድ ሰው ለመተኛ ሲፈልግ ሰላሳ ሶስት ጊዜያት ተስቢሕና ተሕሚድ (አላህም ከከንቱና ውድቅ ከሆኑ ንግግሮች ማጥራቱና አላህን ማመስገኑ) እንዲሁም ሰላሳ አራት ጊዜ ተክቢር (አላህን ማላቁ) ነቢያዊ ፈለግ ሲሆን ትሩፋቱም የላቀ ነው፡፡ ይኸውም ለሰውነት ብርታት ይሰጣል፡፡

**ለዚህም ማስረጃው፡** - ዐሊይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ፋጢመህ በመጅ ምክንያት እጇ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት አቤት አለች፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደምርኮኞች መጥተዋል፡፡ ወደእሳቸው ዘንድ አላገኘቻቸውም፡፡ ዓኢሻን አገኘች፡፡ ሁኔታውን ነገረቻት፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሲመጡ ፈጢመህ ወደእሷ ዘንድ እንደመጣች ነገረቻቸው፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ

ይሁን- መጡ፡፡ መኝታችንን ይዘናል፡፡ ለመሳት ዳዳን፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **“በቦታችሁ ላይ ሁኑ፡፡”** አሉን፡፡ የእግራቸውን ቅዝቃዜ ደረቴ ላይ እስኪሰማኝ ድረስ በመካከላችን ተቀመጡ፡፡ ከዚያም፣ **“ከጠየቃችሁት የተሻለ ነገር ላስተምራችሁን? መኝታችሁን ስትይዙ አላህን ሰላሳ አራት ጊዜ ታልቃላችሁ፣ ከከንቱና ውድቅ ከሆኑ ንግግሮች ሰላሳ ሶስት ጊዜ ታጠሩታልችሁ፡፡ ሰላሳ ሶሰት ጊዜ ታመሰግኑታላችሁ፡፡ ይኻችሁ ከአግልጋይ ለናንተ የተሻለ ነው፡፡”** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር (3705)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2727) ላይ ዘግበውታል፡፡

በሌላ ዘገባ ዐሊይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከሰማሁት በኋላ ፈጽሞ አልተውኩትም፡፡» ብለዋል፡፡ «በሰፊን ሌሊትም ቢሆን?» ተባሉ፡፡ እሳቸውም፣«በሰፊን ሌሊትም ቢሆን» አሉ፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር (5362)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2727) ላይ ዘግበውታል፡፡

8 اللَّهُمَّ إِنِّي أَسْلَمْتُ وَجْهِي إِلَيْكَ ، وَفَوَّضْتُ أَمْرِي إِلَيْكَ ، وَأَلْجَأْتُ ظَهْرِي إِلَيْكَ ، رَغْبَةً وَرَهْبَةً إِلَيْكَ. لاَ مَلْجَأَ وَلاَ مَنْجَا مِنْكَ إِلاَّ إِلَيْكَ، آمَنْتُ بِكِتَابِكَ الَّذِي أَنْزَلْتَ، وَبِنَبِيِّكَ الَّذِي أَرْسَلْتَ

**“አልላሁምመ ኢንኒ አስለምቱ ወጅሂ ኢለይክ ወፈውድቱ አምሪ ኢለይክ፣ ወአልጀእቱ ዘህሪ ኢለይክ ረግበተን ወረህበተን ኢለይክ ላመልጀአ ወላ መንጀ መንከ ኢልላ ኢለይክ ኣመንቱ ቢኪታቢክ-ልለዚ ኣመንቱ ቢኪታቢከ-ልለዚ አንዘልት ወቢነቢይዩከ-ልለዚ አርሰልት፡፡** /አላህ ሆይ! ፊቴን ወዳንተ አሳልፌ ሰጠሁ፡፡ ጉዳዬን ወዳንተ አቤት አልኩ፡፡ ጀርባዬን ወዳንተ አስጠጋሁ፡፡ በፍላጎትና በፍራቻ ወዳንተ መጣሁ፡፡ ወዳንተው ካልሆነ በስተቀር በርግጥ መጠጊያና ካንተ መሸሺያ የለም፡፡ በዚያ ባወረድከው መጽሐፍህና በላከው ነቢይህም አመንኩ፡፡/” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ



◆ አላህን ማውሳት መጠበቂያ ምሽግ፣ ልብን ሕያው ማድረጊያ ምክንያት ናቸውና አላህን ከሚያወሱ ሰዎች መካከል አንዱ ሁን፡፡ የአላህ መልእክተኛ (የአላህ ሰላምና እዝነት በእሳቸው ላይ ይሁን)፤ «ጌታውን የሚያወሳና ጌታውን የማያወሳ ሰው ምሳሌያቸው ልክ ሕይወት እንዳለውና እንደሞተ ሰው ነው፡፡» ብለዋል፡፡


ዘገባ ቁጥር (247)፣ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2710) ላይ ዘግበውታል፡፡ በሐዲሡ መጨረሻ ላይ፣ "-በምድር ላይ የመጨረሻ ንግግርህ አድርጋቸው፡፡ በዚያች ሌሊት ከሞትክ አንተ በኢስላም ላይ ሆነ ሞተሃል፡፡" ያሉ ሲሆን በሌላ የሙስሊም ዘገባ፣ "ካነጋህም በመልካም ነገር ላይ አንግተሃል፡፡" ብለዋል የሚል ዘገባ ተዘግቧል፡፡

በዚህ ሐዲሥ ላይ ሌላ ነቢያዊ ፈለግ እናገኛለን፡፡ ይኸውም፡- አንድ ሰው ይህን ዚክር ከመተኛቱ በፊት የሚናገረው የመጨረሻ ንግግሩ ሊያደርገው ይገባል፡፡ ምናልባት በዚያ ሌሊት ላይ ቢሞት ትልቅ ምንዳ ይታሰብለታል፡፡ በኢስላም ተፈጥሮ ላይ ሆነው ከሞቱት ጋር ይሆናል፡፡ በሌላ አነጋገር ቀጥተኛ በሆነው በኢብራሂም -የአላህ ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈለግ ላይ ሞቷል፡፡ ካነጋ ደግሞ በመልካም ሲሳዩና ስራው ላይ ሆኖ ይሞታል፡፡ ይህ አነጋገር ከዚህ በላይ ካለፉት ሁሉ የተሻለና ሁሉንም ነገሮች ያጠቃለለ ነው፡፡ -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፡፡

**اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ خَلَقْتَنِي وَأَنَا عَبْدُكَ وَأَنَا عَلَى عَهْدِكَ وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ وَأَبُوءُ لَكَ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ**

**በዚህ ላይ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባው ነገር ቢሆን፡-** ይህ አላህ የክብርና የልእልና ባለቤት የሆነው ጌታ የተመጻደቀበት የሆነ በእጅጉ የላቀ ዚክር ነው፡፡ የትልቅ ትሩፋት ሰበብም ነው፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ከሸድዳድ ኢብን አውስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ***"የኢስቲግፋር የበላይ ማለት፡- አልላሁምመ አንተ ርብቢ ላ ኢላሀ ኢልላ አንተ ኸለቅተኒ ወአና ዐብዱከ ወአና ዐላ ዐህዲክ ወወዕዲክ መ-ስተጠዕቱ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ማ ሰንዕቱ አቡዉኡ ለከ ቢኒዕመቲከ-ለለቲ ዐለይየ ወአቡኡ ለከ ቢዘንቢ ፈግፊር ሊ ፈ ኢንነሁ ላየግፊሩ-ዝዙኑበ ኢልላ አንተ፣*** /አላህ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ ካንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ አንተ ፈጥረኸኛል፡፡ እኔ ባሪይህ ነኝ፡፡ እኔ በቻልኩት መጠን በቃል-ኪዳንህና በቀጠሮች ላይ ነኝ፡፡ ከፈጸምኩት ተንኮል ባንተ እጠበቃለሁ፡፡በኔ ላይ ባጎናጸፍከው ጸጋዎችህ ወዳንተ እመለሳለሁ፡፡ በወንጀሌም ወዳንተ እመለሳለሁ ወንጀሌን ማርልኝ፡፡ በእርግጥ ካንተ በስተቀር ወንጀሎችን የሚምር የለም፡፡/ **ማለትህ ነው፡፡ እውነት ነው ብሎ ያለ ከማምሸቱ በፊት በዚያ ቀኑ ከሞተ እሱ ከጀነት ሰዎች መካከል ነው፡፡ ሌሊት ላይ እውነት ነው ብሎ ያለ ሳያነጋ በፊት ከሞተ እሱ ከጀነት ሰዎች መካከል ነው፡፡"** ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6306) ላይ ዘግበውታል፡፡

## የ ተኛ ሰው በሚያየው ነገር ላይ ያሉ ነቢያዊ ፈለጎች



በአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉትና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ላይ እንደሰፈረው አንድ የተኛ ሰው የሚያየው ነገር ከሶስት ሁኔታዎች ውጭ አይሆንም፡፡ እነርሱም፡-

1. መልካም የሆነ ሕልም፡፡ እሱም ከአላህ የሆነ ብስራት ሲሆን ስነ-ስርአቶች አሉት፡፡ እነርሱን ወደፊት እንመለከታቸዋለን፡፡

2 የሚያሳዝን ሕልም፦- ይህ ከሸይጣን ሲሆን ማገኛውም የአላህ ባሪያ ስነ-ስርአቱን በትክክል ከፈጸመ ምንም ነገር አይጎዳውም:: እነርሱን ወደፊት እንመለከታቸዋለን::

3 ከመተኛቱ በፊት ሲያስበው የነበረውን በሕልሙ ያያል:: ይህ ደግሞ ምንም ነገር አይደለም::

## በዚህ ምዕራፍ ሥር ከመጡ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል በበርካታ ሐዲሦች ላይ የመጣው:-

አቢ ሰለመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «በርግጥ የምታሳምመኝን ሕልም የማይ ነበርኩ:: አባ ቀታዳህን አገኘሁና፦- የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"መልካም ሕልም ከአላህ ነው:: አንዳችሁ የሚወደውን ሕልም ካየ ለሚወደው ሰው ካልሆነ በስተቀር አይናገር:: የሚጠላው ሕልም ካየ በግራ ጎኑ ሶስት ጊዜ እትፍ እትፍ ይበል:: ከሸይጣን ተንኮልና ካየው ሕልም ተንኮል በአላህ ይጠበቅ:: ለአንድም ሰው አይናገር:: ምንም አይጎዳውምና ነው::"** እስካሉ ድረስ የምታሳምመኝ የሆነችን ሕልም እመለከት ነበር::» አልኩኝ» ብለዋል::

አቢ ሰለመህ እንዲህም ብለዋል፣ «ይህን ሐዲሥ እስከምሰማ ድረስ በእኔ ላይ ከተራራ የከበደ ሕልም አመለከት ነበር:: ከዚያ ምንም ትኩረት አላደርግበትም::» ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5747)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2261) ላይ ዘግበውታል:: በሌላ ዘገባ ደግሞ፣ **"መልካም ሕልም ከአላህ ነው:: ሕልሞች ከሸይጣን ናቸው:: አንዳችሁ የሚፈራው ሕልም ካየ በግራው በኩል እትፍ እትፍ ይበል:: ከእሷ ተንኮል በአላህ ይጠበቅ:: በእርግጥ እሷ ምንም አትጎዳውም::"** የሚል ተዘግቧል:: ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3292)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2261) ላይ ዘግበውታል::

ጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ከሸይጣን ሶስት ጊዜ በአላህ ይጠበቅ:: ከነበረበት ጎን ወደሌላኛው ይዙር::"** ብለዋል::ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2262) ላይ ዘግበውታል::

አቢ ሰዒይድ አል-ኹድሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉትና ቡኻሪ ሐዲሡን እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"አንዳችሁ መልካም ሕልም ካየ እሷ ከአላህ ነች:: በእሷ ሰበብ አላህን ያመስግን::"** ብለዋል:: ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (7045) ላይ ዘግበውታል::

**ካለፉት ሐዲሦች ጥሩ ሕልም ያየ የሚከተለውን መተግበሩ ነቢያዊ ፈለግ እንደሆነ እንገነዘባለን፡ ፡ እነርሱም፡-**

1 **አንደኛ፡-** በእሷ ሰበብ አላህን ያመስግን፡፡

**ሁለተኛ፡-** ለሰዎች ስለእሷ ይናገር፡፡

2 **የሚጠላውን ሕልም ያየ ሰው የሚከተለውን መተግበሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡-**

**አንደኛ፡-** በግራው በኩል እትፍ እትፍ ይላል፡፡

**ሁለተኛ፡-** ሶስት ጊዜ ከሸይጣንና ካየው ነገር ተንኮል በአላህ መጠበቅ አለበት፡፡ ይህ ማለት ሶስት ጊዜ «አዑዚ ቢልላሂ ሚነ-ሽሽይጣኒ-ርረጂይም ወሚን ሸርሪሃ» ይላል፡፡

**ሶስተኛ፡-** ለማንም ሰው መናገር የለበትም፡፡ ይህ ከፈጸመም ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንደተናገሩት ምንም ጉዳት አታደርስበትም፡፡

**አራተኛ፡-** ከተኛበት ጎኑ ወደሌላኛው ይዛወራል፡፡ በጀርባው ተንጋሎ ከነበረ በጎኑ ይተኛል፡፡

**አምስተኛ፡-** ተነስቶ ሁለት ረከዐዎችን ይሰግዳል፡፡

**ከዚህ በላይ ካሳለፍናቸው ሐዲሦች የምንቀስማቸው ቁም ነገሮች፡-** የሙስሊም ሕልም ከነብይነት አንዱ አካል ነው፡፡ ከሰዎች በሕልሙ ላይ እውነተኛ የሆነ ሰው ነቅቶም ቢሆን እውነተኛ የሆነ ሰው ነው፡፡ ይህ የእውነተኛነት ተጽእኖ ነው፡፡ በሙስሊም ላይ ያለው በረከት እንቅልፍ ላይ ሳለም ቀጣይ ነው፡፡

**ሌሊት ላይ ከእንቅልፉ የነቃ ሰው ይህን ዚክር ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡-**

اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ خَلَقْتَنِي وَأَنَا عَبْدُكَ وَأَنَا عَلَى عَهْدِكَ وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ وَأَبُوءُ لَكَ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ

ከዑባደህ ኢብን አስ-ሳሚት -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሌሊት ላይ ድንገት የነቃና ላ ኢለሀ አልለልላሀ ወሕደሁ ላ ሸሪከ-ልላሀ ለሁ-ልሙልኩ ወለሁ-ልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር አልሐምዱሊልላህ የሱብሓነ-ልላህ ወላ ኢላሀ ኢልለልላሁ ውልላሁ አክበር ወላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ፡ ፡** /ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ አጋር የለውም፡፡ ንግሥና ለሱ ነው፡፡ ምስጋናም ለእሱ ነው፡፡ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡ ከከንቱና ውድቅ ንግግሮች አላህ በእጅጉ ጠራ፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምም፡፡ አላህ ታላቅ ነውም፡፡ ብልሐትም ሆነ ሃይል በአላህ ካልሆነ በስተቀር በሌላ የለም፡፡/ ያለና ከዚያም አልላሁምመ ኢግፊር ሊ፡፡ /አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማርልኝ፡፡/ ወይም ዱዓእ ካደረገ ዱዓው ምላሽ ያገኛል፡፡ ዉዱእ አድርጎ ከሰገደ ሰላቱ ተቀባይነትን ያገኛል፡፡” ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1154) ላይ ዘግበውታል፡፡

ኢብን አሢር -አላህ ይዘንላቸው-፣ **‹‹“ሌሊት ላይ ድንገት የነቃ” ማለት ከእንቅልፉ የባነነ ማለት ነው፡፡››** ብለዋል፡፡ ኢብን አሢር፡- አን-ኒሃያ ፊ ገሪቢ-ልአሠር ገጽ ፡ 108፡፡

**اللَّهُمَّ أَنْتَ رَبِّي لَا إِلَهَ إِلَّا أَنْتَ خَلَقْتَنِي وَأَنَا عَبْدُكَ وَأَنَا عَلَى عَهْدِكَ وَوَعْدِكَ مَا اسْتَطَعْتُ أَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ مَا صَنَعْتُ أَبُوءُ لَكَ بِنِعْمَتِكَ عَلَيَّ وَأَبُوءُ لَكَ بِذَنْبِي فَاغْفِرْ لِي فَإِنَّهُ لَا يَغْفِرُ الذُّنُوبَ إِلَّا أَنْتَ**

በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ሁለት የላቁ የሆኑ ብስራቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡- ከእንቅልፉ ድንገት ነቅቶ፣ **“ላ ኢለሀ አልለልላህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ-ልላህ ለሁ-ልሙልኩ ወለሁ-ልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር አልሐምዱሊልላህ የሱብሓነ-ልላህ ወላ ኢላህ ኢልለልላህ ውልላሁ አክበር ወላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢልላ ቢልላህ፡፡** /ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡ ብቻውን ነው፡፡ አጋር የለውም፡፡ ንግሥና ለሱ ነው፡፡ ምስጋናም ለእሱ ነው፡፡ እርሱ በሁለም ነገር ላይ ቻይ ነው፡፡ ምስጋና ለአላህ ይሁን፡፡ ከከንቱና ውድቅ ንግግሮች አላህ በእጅጉ ጠራ፡፡ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለምም፡፡ አላህ ታላቅ ነውም፡፡ ብልሐትም ሆነ ሃይል በአላህ ካልሆነ በስተቀር በሌላ የለም፡፡/” የሚለውን ዚክር ያለ ሰው ሁለት ብስራቶች አሉት፡፡

**አንደኛው፡ -** “አልላሁምመ ኢግፊር ሊ /አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማርልኝ፡፡/ ወይም ዱዓእ ካደረገ ዱዓው ምላሽ ያገኛል፡፡”

**ሁለተኛ፡ -** ተነስቶ ዉዱእ አድርጎ ከሰገደ ሰላቱ ተቀባይነት አለው፡፡ እነዚህን ችሮታዎች ላጣቀመን አላህ ምስጋና ይገባው፡፡ ለተግባሩ አጋጣሚውን እንጠይቀዋለን፡፡

ይህ ነቢያዊ ፈለግ በጊዜ የተገደቡ ነቢያዊ ፈለጎችን መቋጫ ነው፡፡ ከእሱ በኋላ ያሉት ነቢያዊ ፈለጎች ለምሳሌ፡- መጽሐፉን የጀመርንበት ከእንቅልፍ መንቃት አንዱ ሲሆን በሥሩም የመጀመሪያው መፋቂያና **“አል-ሐምዱሊልላሂ-ልለዚ አህያና በዕደ ማ አማተና ወኢለይሂ-ንኑሻር፡፡**/ ከገደለን በኋላ ሕያው ላደረገን ለዚያ ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡/” የሚለው ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡







# በጊዜ ያልተገደቡ ነቢያዊ ፈለጎች

ይህ እለታዊ የሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች ሁለተኛው ክፍል ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ነቢያዊ ፈለግ ርዕሱ በጣም ሰፊና በርካታ ነው፡፡ ከእሱም ውስጥ በሁኔታዎች፣ በግለሰቦች፣ በቦታዎችና በጊዜያት የሚለያዩ ነቢያዊ ፈለጎች ይገኛሉ፡፡

በቀንና በምሽት ላይ የሚደጋገሙትን ነቢያዊ ፈለጎችን ለማቅረብ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ አላህን ስኬትና ዳር መድረስን እጠይቀዋለሁ፡፡

**የዚህ ክፍል የመጀመሪያው ነቢያዊ ፈለግ፡-**

## አንደኛ፡- የአመጋገብ ሱንናዎች



### 1 በምግቡ መጀመሪያ ላይ የአላህን ስም ማውሳት

ዑመር ኢብን አቢ ሰለመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «በአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ቤት ውስጥ ልጅ ነበርኩኝ። እጄ መመገቢያ ትሪውን ይነካካ ነበር። እንዲህ አሉኝ፣ **“አንተ ልጅ ሆይ! የአላህን ስም አውሳ። በቀኝህም ተመገብ። ከፊት ለፊትህም ተመገብ።”** ከዚያች ጊዜ አንስቶ አመጋገቤ እንደዚያ ከመሆን አልተወገድም።» ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5376)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2022) ላይ ዘግበውታል።

ለአንድ ሙስሊም የተሻለው የአላህን ስም ማውሳትን አለመተዉ ነው። የአላህን ስም ማውሳቱን ከረሳና ካስታወሰ፣ ‹**ቢስሚልላህ አውወለሁ ወአኺረሁ።** *በመጀመሪያውም በመጨረሻው ላይ በአላህ ስም።›* ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው።

**بسم الله أوله وآخره**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- **“አንዳችሁ ሲመገብ የአላህን ስም ያውሳ። የአላህን ስም በመጀመሪያው ላይ ማውሳትን ከረሳ ቢስሚልላህ አውወለሁ ወአኺረሁ።** በመጀመሪያውም በመጨረሻው ላይ በአላህ ስም።/ ይበል።” ማለታቸውን የዘገቡበት ሐዲሥ ነው። ሐዲሡን አቢ ዳዉድ በቁጥር (3767)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (1858) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል። *ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 282።*

ሐዲሡ አንድ ሲመገብ ከሸይጣን ጋር እንዳይመሳሰል በቀኝ እጁ መመገብ እንዳለበት አረጋግጧል፡፡ አንድ ሙስሊም ሲመገብ የአላህ ስምን ካላወሳ በምግቡ ላይ ሸይጣን ይጋራዋል፡፡ በግራ እጁ ከተመገበ ወይም ከጠጣ በዚህ ድርጊቱ ሸይጣንን ተመሳስሏል፡፡ ምክንያቱም ሸይጣን የሚመገበውም የሚጠጣውም በግራው ስለሆነ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ሸይጣን ወደአንድ ቤት ውስጥ የመግባት፣ በውስጡም የማደርና ከቤቱ ቤተሰቦች ጋር ምግብን የመጋራት ከፍተኛ ጉጉት አለው፡፡ ጃቢር ኢብን ዐብዱላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንድ ሰው ወደቤቱ ሲገባ በምግባቱና በምግቡ ላይ የአላህን ስም ካወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያና እራት የላችሁም ይላል፡፡ ሰውዬው ሲገባ በመግባቱ ላይ የአላህን ስም ካላወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያ አገኛችሁ፡፡ ” በምግቡ ላይ የአላህን ስም ካላወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያና እራት አገኛችሁ፡፡ ይላል፡፡”** ሲሉ መስማታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (2018) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 2 ከፊት ለፊት መመገብ



ከዚህ በላይ በዑመር ኢብን አቢ ሰለማህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በተላለፈው ሐዲሥ ላይ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ከፊት ለፊትህ ብላ፡፡”** ማለታቸው ተዘግቧል፡፡

## 3 የወደቀችውን ቁራሽ ማንሳትና በላዩዋ ላይ ያለውን ጎጂ ነገር ማስወገድና መመገብ

ጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“በርግጥ ሸይጣን አንዳችሁን በሁሉም ሁኔታው ላይ ይመጣበታል፡፡ ምግቡ ላይም ሳይቀር ይመጣል፡፡ ከአንዳችሁ አንዳች ቁራሽ ብትወድቅ በላዩዋ ላይ ያለውን ጎጂ ነገር ያስወግድና ከዚያ ይብላት፡፡ ለሸይጣን ፈጽሞ አይተዋት፡፡ ከጨረሰ ጣቶቹን ይላስ፡፡ የምግቡ በረካት በየትኛው የምግቡ ክፍል ላይ እንዳለ አያውቅምና፡፡”** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2033) ላይ ዘግበውታል፡፡

ይህን ሐዲሥ የሚያስተውል በርግጥ ሸይጣን አንድን ሰው በሁሉም ነገሮቹ ላይ ለመጋራት፣ በረከትን ከእሱ ላይ ለማስወገድ፣ በርካታ ሁኔታዎቹን ሊያበላሽበት ጉጉት እንዳለው ይረዳል፡፡ ሸይጣን ከአንድ ሰው ጋር ለመቆራኘት ፍላጎት እንዳለው ከሚያረጋግጡልን መካከል፣ **“በርግጥ ሸይጣን አንዳችሁን በሁሉም ሁኔታው ላይ ይመጣበታል፡፡”** የሚለው የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሐዲሥ ነው፡፡ ከነዚህ ሁኔታዎች መካከል የተወሰኑትን ግልጽ የሚያደርጉ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ከዚህ በፊት ያሳለፍነው በምግብና በማደሪያ ላይ የሰፈሩት ሐዲሦች አብነት ይጠቀሳሉ፡

## 4 ጣቶችን መላስ



መላስ ማለት በምላስ ጫፍ ጣቶቹን እያንዳንዳቸው መላስ ማለት ነው፡፡ ነቢያዊ ፈለጉ የሰውየውን ጣቶች እንደሚስቱ ዓይነት ሰው እንዲልስለት ማድረጉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጣቶቹን ሳይላስ በፊት በመሐረብ ወይም በሶፍት አለማበሱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡** - ከዚህ በፊት ያሳለፍነው የጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ነው፡፡

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ከተመገበ እጁን ሳይልስ ወይም ሳያስልስ በሰፌት አያብስ፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5456)፣ ሙስሊም በቁጥር (2033) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 5 የመመገቢያ ትሪውን ማጽዳት



የመመገቢያ ትሪውን ማጽዳት ማለት በሚበላበት አካባቢ ያለውን ሥፍራ ንጹሕ አድርጎ ማጽዳት ማለት ነው፡፡ **ለምሳሌ፡** - ሰውዬው ሩዝ የሚበላ ከነበር ነቢያዊ ፈለጉ ከፊት ለፊቱ አንዳች ነገር አለመተዉ፣ የተቀረውን ማበሱና መብላቱ ነው፡፡ ምናልባትም የምግቡ በረከት ያለው በዚህ በቀረውና በማይተወው ላይ ይሆናል፡፡

**ለዚህም ማስረጃው፡** - አነስ -አላህነ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ትሪውን እንድናጸዳ አዘዙን፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (2034) ላይ ዘግበውታል፡፡ በሌላ የሙስሊም ዘገባ አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ትሪውን ያጽዳ፡፡”** ብለዋል፡፡ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (2035) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሸይኻችን ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ትርጉሙ ምግብ የቀረበትን ሥፍራ እየተከታተልክ በጣቶችህ በማስወገድ ጣትህን መላስ ነው፡፡ የሚሳዝነው የዲን ትምህርት ተማሪዎችንም ቢሆኑ ይህ እንደዚሁ ነው፡፡» *ሸርሑ ሪያዱ-ስሳሊሒን ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 892፡፡*

## 6 በሶሰት ጣቶች መብላት



በሶሰት ጣቶች መብላት ነቢያዊ ፈለግ ነው። ይሁን እንጂ በሶስት ጣቶች መብላት የሚለው እንደቴምር ዓይነት የመሰለን ነገር ነው መብላት ተደርጎ ይወሰዳል።

**ለዚህ ማስረጃው፦** ከዕብ ኢብን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሶሰት ጣቶች ይበሉ ነበር። እጃቸውን ሳያብሱ በፊት ይልሱ ነበር።» ብለዋል። ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2032) ላይ ዘግበውታል።

## 7 ከእቃው ውጭ ሶስት ጊዜ መተንፈስ

በእቃ ውስጥ ላይ ያለን ውሃ በሶሰት ጊዜ መጠጣትና በእያንዳንዱ መጠጣት በኋላ መተንፈስ ነቢያዊ ፈለግ ነው።



**ለዚህ ማስረጃው፦** አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በመጠጥ ላይ ሶስት ጊዜ ይተነፍሱና፣ **"በርግጥ እሱ አርኪ፣ ፈዋሽና እጅግ ጣፋጭ የሆነ ነው።"** ይሉ ነበር።» ብለዋል። አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲሁ፣ «በመጠጥ ላይ ሶስት ጊዜ እተነፍሳለሁ።» ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሀዲሥ ዘገባ ቁጥር (5631)፣ ሙስሊም በቁጥር (2028) ላይ ዘግበውታል።

መተንፈስ ማለት ሲጠጡ ከእቃው ውጭ ይተነፍሱ ነበር ማለት ነው። በውሃው ላይ መተንፈስ የተጠላ ተግባር ነው። አቢ ቀታደህ -አላህ መልካም ሥረዎቻቸውን ይውደድላቸው- ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ላይ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"አንዳችሁ ከጠጣ በእቃው ውስጥ አይተንፍስ።"** ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5630)፣ ሙስሊም በቁጥር (267) ላይ ዘግበውታል።

## 8 ከምግብ በኋላ -በእጅጉ የላቀውን- አላህን ማመስገን

### ለዚህ ነቢያዊ ፈለግ ማስረጃው፡-

አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"በርግጥ አላህ አንድ ባሪያው አንዲት ነገር በልቶ በእሷ ላይ ማመስገኑን ከእሱ ይወዳል፡፡ ወይም አንዳች ነገር ጠጥቶ በእሷ ላይ ማመስገኑን ከእሱ ይወዳል፡፡"** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (2743) ላይ ዘግበውታል፡፡




**አላህን ለማመስገን የተለያዩ የምስጋና ዓይነቶች አሉ፡፡ ከእነሱ መካከል፡-**

1. الْحَمْدُ لِلَّهِ كَثِيرًا طَيِّبًا مُبَارَكًا فِيهِ غَيْرَ مَكْفِيٍّ ، وَلَا مُوَدَّعٍ ، وَلَا مُسْتَغْنًى عَنْهُ رَبَّنَا

   "አልሐምዱሊልላሂ ከሢይረን ጠይዪበን ሙባረከን ፊይሂ ገይረ መክፊይዪን ወላ ሙወደዒን ወላ ሙስተግነን ዐንሁ ረብበና፡፡" ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር (5458) ላይ ከአቢ ኡማመህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

2. الْحَمْدُ لِلَّهِ الَّذِي كَفَانَا وَأَرْوَانَا غَيْرَ مَكْفِيٍّ، وَلَا مَكْفُورٍ

   "አልሐምዱሊልለሂ-ልለዚ ከፋና ወአርዋና ገይረ መከፊይዪን ወላ መክፉዉር፡፡" ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5459) ላይ  ዘግበውታል፡፡

## 9 በምግብ ላይ መሰብሰብ

በምግብ ላይ መሰብሰብና አለመለያየት ከነቢያዊ ፈለጎች አንዱ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** ጃቢር ኢብን ዐብዲላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"የአንድ ሰው ምግብ ለሁለት ሰዎች ይበቃል፡፡ የሁለት ሰዎች ምግብ ለአራት ሰዎች ይበቃል፡፡ የአራት ሰዎች ምግብ ለስምንት ሰዎች ይበቃል፡፡"** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙሰሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2059) ላይ ዘግበውታል፡፡



## 10 አንድ ሰው ምግቡ ደስ ካለው ማወደስ

አንድ ሰው የሚመገበው ምግብ ደስ ካለው በእርግጥ በውስጡ ባለው እንደሚያወድሰው ጥርጥር የለውም፡፡ ይህ ተግባር ደግሞ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡** - ጃቢር ኢብን ዐብዲላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነበዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ቤተሰባቸውን ዳቦ ማባያ ነገር ጠየቁ፡፡ እነሱም፡- ‹ከኮምጣጤ በስተቀር ምንም ነገር የለንም› አሏቸው፡፡ እንዲመጣ አደረጉ፡፡ ዳቦውን ይበሉበት ጀመሩና፣ **"ግሩም ማባያ ኮምጣጤ ነው፡፡ ግሩም ማባያ ኮምጣጤ ነው፡፡"** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2025) ላይ ዘግበውታል፡፡ እነሱ ዘመን የነበረው ኮምጣጤ አሁን በኛ ዘመን እንዳለው ኮምጣጤ አይደለም፡፡ አይቆመጥጥም፡፡ ለማባያነት ያገለግላል፡፡

ሸይኻችን ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው-፣ «ይህ እንዲሁ ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስተምህሮዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ በርግጥ እሳቸው አንዳች ምግብ ደስ ካላቸው ያወድሱት ነበር፡፡ ለምሳሌ ዳቦን ስታመሰግን ፡- እነ እከሌ የጋገሩት ዳቦ ምነኛ ግሩም ዳቦ ነው! ወይም የመሳሰለውን ትላለህ፡፡ ይህ እንዲሁ ከአላህ መልእክተኛ-የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈለጎች መካከል ነው፡፡» ብለዋል፡፡ *ሸርሑ ሪያዱ-ስሳሊሒን ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 1057፡፡*

ነባራዊ ሁኔታችንን ላየ በርካታ የነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈለጎችን እንደምንቃረን ይታዘባል፡፡ ሰዎች ነቢያዊ ፈለገን መተው ብቻ አይደለም ጭራሽ ተቃርነውታልም፡፡ ከነዚህ መካከል ምግብ ማነወር አንዱ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ያንቋሽሻሉ፡፡ ይህ የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስተምህሮዎችን መቃረን ነው፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደዘገቡት፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈጽሞ አንድም ጊዜ ምግብን አነውረው አያውቁም፡፡ ከወደዱት ይመገቡታል፡፡ ያለዚያ ይተዉታል፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3563)፣ ሙስሊም በቁጥር (2064) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 11 ለምግቡ ባለቤት ዱዓእ ማድረግ

اللَّهُمَّ بَارِكْ لَهُمْ فِي مَا رَزَقْتَهُمْ ، وَاغْفِرْ لَهُمْ ، وَارْحَمْهُمْ

**ለዚህ ማስረጃው፡** - ዐብዱላህ ኢብን ቡስር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ « የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አባቴ ዘንድ አረፉ፡፡ ምግብና ሸርባ አቀረብንላቸው፡፡ ከእሱም በሉ፡፡ ከዚያ ይበሉት የነበረው ቴምር መጣላቸው፡፡ ፍሬዎቹን በጣቶቻቸው መካከል ይወረውሩና የአመልካችና የመካከል ጣቶቻቸውን ይሰበስቡ ነበር፡፡ ከዚያ የሚጠጣ ነገር መጣላቸውና ጠጡ፡፡ ከዚያ በቀኛቸው ላለው ሰጡት፡፡ ከዚያም አባቴ የፈረሳቸውን ልጓም ይዞ፣ ‹አላህን ይለምኑልን፡፡› አለ፡፡ እሳቸውም፣ **"አልላሁምመ ባሪክ ለሁም ፊማ ረዘቅተሁም፡፡ ወግፊር ለሁም፡፡ ወርሐምሁም**፡፡/አላህ ሆይ! በለገስካቸው ሲሳይ ላይ ባርክላቸው፡፡ ወንጀሎቻቸውን ማርላቸውም፡፡ እዘንላቸውም፡፡/" አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2042) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 12 የሚጠጣ ሰው ከግራው ይልቅ በቀኙ በኩል ያለውን ሰው ማጠጣቱ የተወደደ ተግባር ስለመሆኑ

ይህ ማለት አንድ ሰው አንዳች ነገር ከጠጣ በኋላ የሚጠጣውን ነገር በቀኝ በኩል ላለው ሰው ማስተላለፉ ነቢያዊ ፈለግ ነው ማለት ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** አነስ ኢብን ማሊክ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው*-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደቤታችን መጡ፡፡ የሚጠጣ ነገር እንዲመጣላቸው ጠየቁ፡፡ ፍየላችንን አለብንላቸው፡፡ ከዚያ ከዚህ ምንጬ ውሃ ሰጠኋቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ አቡ በክር በግራቸው፣ ዑመር በፊት ለፊታቸው እንዲሁም አንድ ገጠሬ ሰው በቀኛቸው በኩል ነበሩ፡፡ የአላህ መልእክተኛ የሚጠጡትን ጠጥተው ከጨረሱ በኋላ ዑመር እያመላከቷቸው፣ ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህ አቡ በክር ናቸው፡፡› አሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛ ለገጠሬው ሰጡት፡፡ አቡ በክርንና ዑመርን ተዉ፡፡ ከዚያም የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“የቀኝ ጓዶች፣ የቀን ጓዶች፣ የቀኝ ጓዶች፡፡”** አሉ፡፡ አነስ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው*-፣«እሷ ሱንና ነች፡፡ እሷ ሱንና ነች፡፡ እሷ ሱንና ነች፡፡» አሉ፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (2571)፣ ሙስሊም በቁጥር (2029) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 13 ሰዎችን የሚያጠጣ ሰው መጨረሻ ላይ የሚጠጣ ስለመሆኑ

ሰዎችን የሚያጠጣ ሰው መጨረሻ ላይ መጠጣቱ ነቢያዊ ፈከግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** ረዘም ባለው የአቢ ቀታዳህ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው*- ሐዲሥ ውስጥ፣ «...የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እና ከእኔ ውጭ ማንም ሳይቀር የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-እየቀዱ እኔ አጠጣ ነበር፡፡ ከዚያ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ቀዱና፣ “ጠጣ” አሉኝ፡፡ እኔም፣ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እርስዎ እስኪጠጡ ድረስ አልጠጣም፡፡ አልኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ “እኔ ሰዎችን አጠጪና በመጨረሻቸው ጠጪ ነኝ፡፡” አሉ፡፡ እኔም ጠጣሁ፡፡ የአላህ መልእክተኛም ጠጡ፡፡...» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (681) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ፋይዳ፡-** አንድ ሰው ወተት የጠጣ ከሆነ ወተት በመጠጣቱ በውሃ መጉመጥመጡ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህም አፉ ውስጥ ያለው የወተቱ ቅባት እንዲለቅ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃው፡- ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም *ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው*-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወተት ጠጡ፡፡ ውሃ እንዲመጣላቸው አዘዙ፡፡ ከዚያም ተጉመጠመጡና፣ “በርግጥ እሱ ቅባት ነው፡፡” ቡኻሪ በቁጥር (211)፣ ሙስሊም በቁጥር (358) ላይ ዘግበውታል፡፡



## 14 በሚመሽበት ወቅት እቃዎችን መክደንና የአላህ ስምን ማውሳት

ሲመሽ ክፍት የሆኑ እቃዎችን መክደን፣ ማጠጫዎችን ማጋደም ግጣም ካለቸውም መዝጋትና በዚህ ጊዜም የአላህን ስም ማውሳት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማሰረጃው፡-** ጃቢር ኢብን ዐብዲላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣« የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"እቃን ክደኑ፡፡ ማጠጫዎችንም ግጠሙ፡፡ በአመት ውስጥ በሽታ የሚወርድበት ሌሊት አለ፡፡ ክዳን በሌለበት እቃ ወይም ግጣም በሌለበት ማጠጫ በኩል ከዚያ በሽታ ላይ አንዳች በሽታ ሳያወርደበት አያልፍም፡፡"** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (2014) ላይ የዘገቡት ሲሆን ቡኻሪ ከጃቢር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ላይ እንዲሁ፣ **"አኮሌያችሁንም ግጠሙ፡፡ የአላህን ስምንም አውሱ፡፡ እቃዎቻችሁንም ሸፍኑ፡፡ የአላህንም ስም አውሱ፡፡ አንዳች ነገር በእሷ ላይ ብታጋድሙም፡፡"** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (5623) ላይ ዘግበውታል፡፡



## ሁለተኛ፡- በሰላምታ፣ በመገናኘትና አብሮ በመቀመጥ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች



### 1 ሰላምታ ማቅረብ ከነቢያዊ ፈለጎች ነው፡፡

ማስረጃዎቹ በጣም በርካታ ናቸው፡፡ ከእነር መካከል፡- አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “አንድ ሙስሊም በሙስሊም ላይ ያለው መብት ስድስት ነው፡፡” አሉ፡፡ ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እነርሱ ምን ምን ናቸው? ተባሉ፡፡ እሳቸውም፣ “ስታገኘው ሰላም በለው፡፡ ከጠራህ ምላ ስጠው፡፡ ምክር ከጠየቀህ ምክር ለግሰው፡፡ አነጥሶ አላህን ካመሰገነ አላህ ይማርህ በለው፡፡ ከታመመ ጎብኘው፡፡ ከሞተ ተከተለው፡፡” አሉ፡፡ ሙስሊም በቁጥር (2162) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ሰላምታን መመለስ (ምላሽ መስጠት) ግዴታ ነው፡፡ ለዚህም ማስረጃው፡-**

አላህ እንዲህ ብሏል፣ **“በሰላምታም በተከበራችሁም ጊዜ ከርሷ ይበልጥ ባማረ (ሰላምታ) አክብሩ ወይም (እርሷኑ) መልሷት አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነውና፡፡”** (አን-ኒሳእ ፡ 86)፡፡

ግዴታ የመሆኑ መነሻ የሚከለክለው አንዳች ከልካይ ካልከለከለው ነው፡፡ ከዑለሞች መካከል አንዱ ብቻ ካልሆኑ በስተቀር ይህን ሃሳብ በጋራ ሃሳብነት ሁሉም አስተላልፈውታል፡፡ ከእነዚህ ዑለሞች መካከል፡- ኢብን ሐዝም፣ ኢብን ዐብዱ-ልበር ፣ ሸይኽ ተቂይዩ-ድዲንና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡ አዳቡ-ሸሸርዒየህ ቅጽ፡ 1 ገጽ ፡ 356፡፡ የአር-ሪሳለህ ድርጅት እትም፡፡

السلام عليكم ورحمة الله وبركاته

**በላጩ የሰላምታና የምላሽ ቃል እንዲሁም መሉ የሆነው የሰላምታ ቃል፡- “አስሰላሙ ዐለይኩም ወረሕመቱ-ልላሂ ወበረካቱሁ፡፡” ነው፡፡ ይህ መልካሙና ሙሉው ሰላምታና፡፡**

ኢብን አል-ቀይዩም -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ « -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አስተምህሯቸው ሰላምታን «ወበረካቱሁ» እስከሚለው ድረስ ማጠናቀቅ ነው፡፡» ዛዱ-ልሚዓድ ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 417፡፡

**ሰላምታን ማሰራጨት፡-** ነቢያዊ ፈለግ ሲሆን ትልቅ ትሩፋት ስላለውም ይበረታታል፡፡ አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ነፍሴ በእጁ በሆነችው እምላለሁ! እስክታምኑ ድረስ ጀነት አትገቡም፡፡ እስከምትዋደዱ ድረስ አታምኑም፡፡ ከፈጸማችሁት የምትዋደዱበትን አንዳች ነገር ላመላክታችሁን? በመካከላችሁ ሰላምታን አሰራጩ፡፡”**

## 2 ችግር እስካስገደደ ድረስ ሰላምታን ሶስት ጊዜ መደጋገም፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላምታ ሲያቀርብለት ሙስሊም የሆነው ሰው መስማቱን ከተጠራጠረ ሁለት ጊዜ መደጋገሙ የተወደደ ነው፡፡ ካልሰማም ሶስት ጊዜ፡፡ ብዙ ሰዎች የተሰበሰቡበት ቦታ ሲገባም እንዲሁ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ትልቅ ስብሰባ መካከል ሲገባ ሰዎቹ በርካታ ከሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰላምታ ሲያቀርብ በመጀመሪያው ረድፍ ካሉት በስተቀር ሌሎች አይሰሙትም፡፡ ስለዚህ በስብሰባው ውስጥ ያሉትን ሁሉ ለማጠቃለል ሶስት ጊዜ መደጋገም ያስፈልጋል፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አንዳች ቃል ከተናገሩ ሰዎችን ከእሳቸው እስኪረዷቸው ድረስ ሶስት ጊዜ ይደጋግሙት ነበር፡፡ ወደሰዎች ስብስብ ሲመጡ ሰላም ይሏቸዋል፡፡ ሶስት ጊዜም ሰላም ይሏቸዋል፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (95) ላይ ዘግበውታል፡፡

ከአነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ችግር እስካስገደደ ድረስ አንድ ቃል መረዳትን እስከያገኝ ድረስ ሶስት ጊዜ እንደሚደጋገመው ሰላምታን ሶስት ጊዜ የመደጋገምን ነቢያዊ ፈለግነት ጭብጥ መውሰድ እንችላለን፡፡

## 3 በምታውቀውም ሆነ በማታውቀው ሰው ላይ ሰላምታን ማዳረስ፡፡

ዐብዱላህ ኢብን ዐምር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «አንድ ሰው የአላህ መልእክተኛን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ‹ከኢስላም የትኛው ነው በላጩ?› አላቸው፡፡ እሳቸውም፣ **“ምግብ ማብላትህ፣ በምታውቀውና በማታውቀው ሰው ላይ ሰላምታ ማቅረብ ነው፡፡”** አሉት፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (12)፣ ሙስሊም በቁጥር (39) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 4 ሰላምታን መጀመር ነቢያዊ ፈለግ የሚሆነው መጀመሩ በነቢያዊ ፈለግ ላይ በሰፈረው ሁኔታ ሲጀመር ነው

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ጋላቢ የሆነ በእግረኛ ላይ ፣ እግረኛ የሆነ በተቀመጠ ሰው ላይ፣ ጥቂቶች በብዙዎች ላይሰላምታን ያቅርብ፡፡” ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (2633)፣ ሙስሊም በቁጥር (2160) ላይ የዘገቡት ሲሆን በቡኻሪ ሌላ ዘገባ ላይ ደግሞ፣ “ትንሽ ልጅ ለትልቅ ሰው፣ አላፊ በተቀማጭ፣ “ጥቂቶች በብዙዎች ላይ ሰላምታን ያቅርቡ፡፡” የሚል ተዘግቧል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (6234) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሰላምታን በቅድሚያ ማቅረብ እዚህ ላይ ለመቃረን ሳይሆን ይህንኑም መተግበር ምንም ችግር የለውም፡፡ ይሁን እንጂ ተቃራኒው ማለትም ትልቁ ለትንሹ፣ እግረኛው በጋላቢው ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ሁኔታ መተግበር ቅደሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡

## 5 ለሕጻናት ሰላምታ ማቅረብ ነቢያዊ ፈላግ ነው፡፡



አነስ ኢብን ማሊክ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ከአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ጋር እየሄድኩ ነበር፡፡ በሕጻናት አጠገብን አለፍን፡፡ እሳቸው ሰላምታ አቀረቡላቸው፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (6247)፣ ሙስሊም በቁጥር (2168) ላይ ዘግበውታል፡፡

ይህ ለሕጻናት ሰላምታ ማቅረብ ነፍስ መተናነስን እንድትለምድ ሃላፊነት ማሸከምና ሕጻናት ይህን እሴት እንዲላመዱና ሕያው እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚረዳ ነው፡፡

## 6 ወደቤት ሲገቡ ሰላምታ ማቅረብ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



ይህ ተግባር በሁሉም የሰላምታ ዓይነቶች ላይ ይካተታል፡፡ ይህም ግለሰቡ ጥርሱን ከፋቀ በኋላ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደቤት ሲገቡ ጥርስን መፋቅ (መፋቂያ መጠቀም) ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህ መፋቂያ ነቢያዊ ፈለግ መሆኑንን የሚያረጋጠው አራተኛው ስፍራ ነው፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ ላይ ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ « ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ቤታቸው ሲገቡ ጥርሳቸውን መፋቅ ይጀምራሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (253) ላይ ዘግበውታል፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ቤታቸው ሲገቡ ጥርሳቸውን በመፋቅ ይጀምሩ ነበር፡፡ ከዚያ ለቤተሰቦቻቸው ሰላምታ ያቀርቡ ነበር፡፡ የተወሰኑ ዑለሞች፣ «ወደቤት ስትገባ ሰላምታ ማቅረብህና የትኛውም ቤት አንድም ሰው ባይኖርም ሰላምታ ማቅረብህ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ ይህም አላህ እንዲህ በማለቱ ነው፣ **“ቤቶችንም በገባችሁ ጊዜ ከአላህ ዘንድ የኾነችን የተባረከች መልካም ሰላምታ በነፍሶቻችሁ ላይ ሰላም በሉ፤ እንደዚህ አላህ አንቀጾችን ለናንተ ያብራራል፤ ልታውቁ ይከጀላልና፡፡”** (አን-ኑር ፡ 60)፡፡

ኢብን ሐጀር -አላህ ይዘንላቸው-፣ «በራስ ላይ ሰላምታን ማቅረብ ሰላምታን በማሰራጨት ሥር ይጠቃለላል፡፡ ይህም አንድም ሰው በሌለበት ሥፍራ የገባም ቢሆን ማለት ነው፡፡ ይህም አላህ እጅግ የላቀው ጌታ፣ **“ቤቶችንም በገባችሁ ጊዜ ከአላህ ዘንድ የኾነችን የተባረከች መልካም ሰላምታ በነፍሶቻችሁ ላይ ሰላም በሉ፤”** (አን-ኑር ፡ 60) ስላለ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ አል-ፈትሕ ሰላምታን በማሰራጨት ምዕራፍ ሥር ሐዲሥ ቁጥር (6235) ን ይመልከቱ፡፡

**ፋይዳ፡-** ከዚህ በላይ ከሰፈረው ወደቤት ሲገባ ሶስት ተግባራትን መፈጸም ነቢያዊ ተግባር ነው፡፡ እነርሱም፡-

1. **የመጀመሪያው፡-** ሌሊት ቢሆንም -እጅግ የላቀውን- አላህን ስም ማውሳት

   ጃቢር ኢብን ዐብዲላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውነ ይውደድላቸው- የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንድ ሰው ወደቤቱ ሲገባ በምግባቱና በምግቡ ላይ የአላህን ስም ካወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያና እራት የላችሁም ይላል፡፡ ሰውዬው ሲገባ በመግባቱ ላይ የአላህን ስም ካላወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያ አገኛችሁ፡፡ ” በምግቡ ላይ የአላህን ስም ካላወሳ ሸይጣን፡- ማደሪያና እራት አገኛችሁ፡፡ ይላል፡፡”** ሲሉ መስማታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ቁጥር (2018) ላይ ዘግበውታል፡፡

2. **ሁለተኛው፡-** ከዚህ በላይ በዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባወሩት ሐዲሥ መሰረት ጥርስን መፋቅ (መፋቂያ መጠቀም)፡፡

3. **ሶስተኛው፡-** ለቤተሰቡ ሰላምታ ማቅረብ፡፡

## 7 ሰዎች ተኝተው ሳለ አንድ ሰው ወደሰዎች ሲገባና ሰላምታ ሲያቀርብ ድምጹን ዝግ ማድረጉ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ምክንያቱም አል-ሚቅዳድ ኢብን አል-አስወድ -አላህ መልካም ስራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉት ሐዲሥ ላይ እንደሰፈረው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ ነበር ይፈጽሙ የነበሩት፡፡ አል-ሚቅዳድ በዚህ ሐዲሥ ላይ፣ «... ወተት እናሳልብና ሁሉም የየድርሻውን ይጠጣል፡፡ ለነቢዩም -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የድርሻቸውን እንሰጣቸው ነበር፡፡ ከሌሊቱ ባንድ ወቅት ላይ ይመጡና የነቃ ሰው የሚሰማውንና የተኛ ሰውን የማያነቃ ሰላምታን ሰላም ይሉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (2055) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 8 ሰላምታን ማድረስ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

አንድ ሰው፣ «እከሌን ሰላም በልልኝ፡፡» እንደሚለው ዓይነት ሰላምታን ማድረስ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“በርግጥ ጅብሪል ባንቺ ላይ ሰላምታ ያቀርባል፡፡”** አሏቸው፡፡ እሳቸውም፣ «በእሱ ላይ የአላህ ሰላምታና እዝነት ይሁን» አልኳቸው፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (3217)፣ ሙስሊም በቁጥር (2447) ላይ ዘግበውታል፡፡

ከዚህ የዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የጅብሪልን -የአላህ ሰላምታ በእሱ ላይ ይሁን- ሰላምታን ለዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳደረሱላቸው ሰላምታን ወደባለቤቱ ማድረስ ነቢያዊ ፈለግ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

## 9 በአንድ ስብሰባ ሥፍራ ላይና በመለያየት ወቅት ሰላምታ ማቅረብ እንዲሁ ነቢያዊ ፈለግ የሆነ ተግባር ነው፡፡

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ስብሰባን ሲያጠናቅቅ ሰላምታ ያቅርብ፡፡ ለመነሳት ሲፈልግ ሰላምታ ያቅርብ፡፡ የመጀመሪያዋ ከመጨረሻዋ ይበልጥ መብት ያላት አይደለችም፡፡”** ብለዋል፡፡ አሕመድ በቁጥር (9664)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (5208)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (2706) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒም ትክክለኛቱን አረጋግጠዋል፡፡ ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 132፡፡

## 10 ሲገናኙ ከሰላምታ ጋር መጨባበጥ ነቢያዊ ፈከለግ ነው፡፡



ይህ የሰሓቦች ተግባር ነው፡፡ **ለዚህም ማስረጃው፡-** ቀታዳህ -አላህ መላክም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ለአነስ መጨባበጥ በነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰሓቦች ውስጥ ነበርን?» በማለት ጠየቅኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ «አዎን፡፡» አሉኝ፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (6263) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 11 ሲገናኙ ፈገግ ማለትና መልካም ገጽታ ማሳየት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



አቢ ዘር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ከመልካም ነገር አንዳች ነገር አታሳንስ፡፡ ወንድምህን በመልካም ገጽታ መገናኘትን ቢሆን፡፡"** አሉኝ፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በቁጥር (2626) ላይ ዘግበውታል፡፡ አት-ቲርሚዚይ ከአቢ ዘር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"በወንደምህ ፊት ፈገግ ማለትህ ላንተ ሰደቃህ ነው፡፡"** ብለዋል፡፡ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (1956) ላይ ሲዘግቡት አል-አልባኒም ትክክለኛቱን አረጋግጠዋል፡፡ *አስ-ሰሒሐህ 572* ፡፡

## 12 መልካም ንግግር ሰደቃህ (ምጽዋት) በመሆኑ መተግበሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

በመገኛኘት ወቅትም ሆነ አብረው በሚቀመጡበት ወቅት ወይም በማንኛውም አጋጣሚ መልካም ንግግር ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰደቃህ (ምጽዋት) ነውና፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"መልካም ንግግር ሰደቃህ (ምጽዋት) ነው፡፡"** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (2989)፣ ሙስሊም በቁጥር (1009) ላይ ዘግበውታል፡፡

በበርካታ ሰዎች አንደበት ላይ አብዛኛውን ጊዜ መልካም ንግግር አይጠፋም፡፡ ይሁን እንጂ ምንዳን ቢያስቡ ኖሮ በርካታ ምንዳዎችን ከመጎጸፋቸው ባሻገር እጅግ በርካታ ምጽዋትን (ሰደቃዎችን) ባካበቱ ነበር፡፡

ሸይኻችን ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው-፣ «መልካም ንግግር ማለት ለአንድ ሰው፣ ‹እንዴት ነህ? ጤናህ እንዴት ነው? ወንድሞችህ እንዴት ናቸው?

ቤተሰቦችችህ እንዴት ናቸው? እና ወ.ዘ.ተ ማለትህ ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ቃላት ወዳጅህ ደስታን ያሰርጻሉ፡፡ እያንዳንዱ መልካም ቃል አላህ ዘንድ ምጽዋትህ (ሰደቃህ)፣ ምንዳህና ሽልማትህ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ *ሸርሑ ሪያዱ-ስሳሊሒን ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 996 በመገናኘት ወቅት መልካም ንግግርና መልካም ገጽታ የተወደደ ሰእለመሆኑ ምዕራፍ፡፡*

## 13 በስብሰባ ሥፍራ -በእጅጉ የላቀውን- የአላህን ስም ማውሳት ስለመወደዱ፡፡



የመሰብሰብን ትሩፋቶች የሚያመለክቱ በርካታ ሐዲሦች ተዘግበዋል፡፡ ከእነዚህ ሐዲሦች መካከልም አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ለአላህ እሱ የሚወሳበትን ስፍራ የሚፈልጉ የሆኑ፣ የተከበሩና ተጓዥ የሆኑ መላእክት አሉት፡፡ ዚክር ያለበትን ስብሰባ ካገኙ ዚክር ከሚያደርጉት ሰዎች ጋር አብረው ይቀመጣሉ፡፡ አንዳቸው አንዳቸውን በክንፎቻቸው ያቅፋሉ፡፡ በመካከላቸው በምድራዊ ሰማይ መካከል ያለውን ስፍራ እስከሚሞሉ ድረስ በክንፎቻቸው ያካብቧቸዋል፡፡”** ቡኻሪ በቁጥር (6408)፣ ሙስሊም በቁጥር (2689) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 14 ስብሰባን (በስብሰባ ማካካሻ) ማጠናቀቅ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

سُبْحَانَكَ اللّهُمَّ وَبِحَمْدِكَ أَشْهَدُ أن لاَ إِلَهَ إِلاّ أَنْتَ، أَسْتَغْفِرُكَ وَأَتُوبُ إِلَيْكَ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንድ ባልቱ የበዛበት ስብሰባ ውስጥ ተቀምጦ (ታድሞ) ከዚያ መቀመጫው ሳይነሳ በፊት፡- ሱብሓነከ-ልላሁምመ ወቢሐምዲከ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልላ አመተ አስተግፊሩከ ወአቱቡ ኢለይክ፡፡** /በምስጋናህም ከከንቱና ወድቅ ከሆነው ንግግር በእጅጉ የጠራህ የሆነው አላህ ሆይ! ከአንተ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፣ ምሕረት እጠይቃለሁ፡፡ ወዳንተም በንሰሐ እመለሳለሁ፡፡/ **ካለ በዚያ መቀመጫው ሳለ ምሕረት ተደርጎለታል፡፡”** አት-ቲርሚዘይ በቁጥር (3433) የዘገቡት ሲሆን ኢብን ሐጀር -አላህ ይዘንላቸው- በአል-ፈትሕ የመጨረሻው ማብራሪያ ላይ፣ «የሰገባ ሰነዱ ጠንካራ ነው፡፡» ብለዋል፡፡ አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ *ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 1065፡፡*

## ሶስተኛ፡- በአለባበስና የመዋብ ያሉ ሱንናዎች



### 1 ጫማ ሲጫሙ በቀኝ መጀመር ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

አንድ ሙስሊም ጫማዎቹን ለመጫማት ሲፈልግ በቀኝ መጫማት መጀመሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ በተቃራኒው ሲያወልቅ በግራው ማውለቅ መጀመሩ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



**ለዚህም ማስረጃው፡-** አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ከተጫማ በቀኙ ይጀምር፡፡ ሲያወልቅ ደግሞ ግራው ያውልቅ፡፡ ቀኝ እጁ በመጫማት ላይ ቀዳሚ ይሁን፡፡ በማውለቅ ላይ ደግሞ መጨረሻ ይሁን፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በቁጥር (5856) ላይ ዘግበውታል፡፡

**በእነዚህ ሁለት ሐዲሦች ውስጥ ሶስት ነቢያዊ ፈለጎችን እናገኛለን፡፡ እነርሱም፡-**

1. ሰጫሙ በቀኝ መጀመር
2. ሲያወልቁ በግራ መጀመር
3. የሁለቱንም እግር ጫማ መልበስ ወይም አንድ ጫማ ብቻ ተጫምተው እንዳይሄዱ ሁለቱንም ጫማዎች ማውለቅ፡፡ ይህም በሌላ ዘገባ ላይ፣ **“አንዳችሁ በአንድ ጫማ አይሂድ፡፡”** በሚል ሐዲሥ መከልከሉ ተዘግቧል፡፡


## 2 ነጫጭ የሆኑ ልብሶችን መልበስ ነቢያዊ ፈለግ ነው



የዚህ ርዕስ መልእክት አንድ ሰው ካሉት በተለያዩ ቀለማት የተቀለሙ ልብሶች መካከል (ነጭ) ልብስ መልበሱ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው የሚል ነው፡፡ ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ከልብሶቻችሁ ነጩን ልብስ ልበሱ፡፡ በእርግጥ መልካሙ ልብሳችሁ ነው፡፡ በእርሱም ሙታኖቻችሁን ከፍኑ፡፡”** ብለዋል፡፡ አሕመድ በቁጥር (2219)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (3878)፣ አት-ቲርሚዚይ በቁጥር (994) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን ዘግበውታል፡፡ ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 267፡፡

ሸይኻችን ኢብን ዑሠይሚን -አላህ ይዘንላቸው- እንዲህ ብለዋል፣ «ይህ ሐዲሥ እንደቀሚሶች፣ ሸርጦች፣ ሱሪዎች ያሉትን ነጭ ልብሶችን ያጠቃለለ ነው፡፡ ሁሉም ግን ነጭ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ይህ በጣም ተመራጭ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ካሉት ልብሶች መካከል ሌላ ቀለም ያላቸውን ልብሶች ቢለብስ ምንም ችግር የለውም፡፡ የሚለብሳቸው ልብሶች ግን ለሴቶች ተብለው የተለዩ አለመሆናቸው በመስፈርተነት የተቀመጠ ነው፡፡» ሸርሑ ረያዱ-ስሳሊሒን ቅጽ ፡ 2 ገጽ ፡ 1087፡፡

## 3 ሽቶ መቀባት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡



አነስ -አላህ መልካም ሠራዎቻቸውን ይውደዳቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ከምድራዊው ዓለም በእኔ ዘንድ ሰቶች፣ ሽቶ እጅግ የተወደዱ ተደርገውልኛል፡፡ የዓይን ማረፊያዬ በሰላት ውስጥ እንዲሁ ተደርጎልኛ፡፡”** ብለዋል፡፡ አሕመድ በቁጥር (12293)፣ አን-ነሳኢይ በቁጥር (3940) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ በሰሒሑ አን-ነሳኢይ ውስጥ ሐዲሡን «ሐሰኑን ሰሒሕ» ብለዋል፡፡

ነገር ግን፣ **“ከምድራዊው ዓለማችሁ በእኔ ዘንድ ሶስት ነገሮች የተወደዱ ተደርገውልኛል፡፡”** የሚለው ዘገባ የሐዲሡ ደረጃ ደካማ ነው፡፡

**ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከእሳቸው ላይ መጥፎ ጠረን መኖርን ይጠሉ ነበር፡፡** ቡኻሪ ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ረዥም ሐዲሥ ውስጥ ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከእሳቸው ላይ ሽታን ማግኘት ይበረታባቸው ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ «ሽታን ማግኘት ይበረታባቸው ነበር፡፡» ማለት ጥሩ ያልሆነ ሽታን ማግኘት ማለት ነው፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6972) ላይ ዘግበውታል፡፡

## 4 ሽቶን መመለስ ይጠላል

አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሽቶን አይመልሱም ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2582) ላይ ዘግበውታል፡፡



## 5 ጸጉርን በሚያበጥሩበት ወቅት በቀኝ መጀመር ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

ጸጉርን በሚያበጥሩበት ወቅት በቀኝ ጎን መጀመርና ከዚያም በግራ መቀጠል ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ጸጉራቸውን በሚያበጥሩበት፣ ዉዱእ በሚያደርጉበትና በሁሉም ነገሮቻቸው በቀኝ መጀመር ያስደስታቸው ነበር፡፡» ብለዋል፡፤ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (168)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (268) ላይ ዘግበውታል፡፡

## አራተኛ፡- በማነጠስና በማፋሸግ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች



### የማነጠስ ነቢያዊ ፈለጎች

**1 አንድ የሚያነጥስ ሰው ካስነጠሰው በኋላ "አልሐምዱሊልላህ" ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው**

الْحَمْدُ لِلَّهِ / يَرْحَمُكَ اللهُ / يَهْدِيكُمُ اللَّهُ ، وَيُصْلِحُ بَالَكُمْ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"አንዳችሁ ካነጠሰ ‹አልሐምዱሊልላህ› ይበል፡፡ ወንድሙ ወይም ባልንጀራው፣ ‹የርሐሙከልላህ፡፡ /አላህ ይማርህ፡፡/ ይበለው፡፡ አላህ ይማርህ ካለው፣ ያነጠሰው ሰው ‹የህዲይኩሙ-ልላሁ ወዩስሊሑ ባለኩም፡፡** /አላህ ቀጥተኛውን መንገድ ይምራችሁ፡፡ ሁኔታችሁንም ያስተካክልላችሁ፡፡/" ይበል፡፡" ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6224) ላይ ዘግበውታል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ካነጠሰ በኋላ የሚለውን ዚክር መለያየቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ስለዚህም አንዳንድ ጊዜ፣ «አልሐምዱ-ሊልላህ ዐላ ኩልሊ ሓል፡፡/ በሁሉም ሁኔታ ላይ ለአላህ ምስጋና ይገባው፡፡/ ይላል፡፡ በአቢ ዳዉድ ዘገባ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"አንዳችሁ ካነጠሰ አልሐምዱሊልላህ ዐላ ኩልሊ ሓል ይበል"** ብለዋል፡፡ አቢ ዳዉድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5031) ላይ የዘገቡት ሲሆን ኢብን አል-ቀይዩም -አላህ ይዘንላቸው- ዛዱ-ል-ሚዓድ በተሰኘው መጽሐፋቸው ቅጽ፡ 2 ገጽ ፡ 436 ላይ የሐዲሡ የዘገባ ሰነድ ትክክል ነው ብለዋል፡፡

የሚሰማው ሰው፣ **“የየርሐሙከ-ልላህ፡ ፡ /አላህ ይማርህ፡ ፡/”** ይለዋል፡፡ ያነጠሰው ሰውም እንዲህ ላለው ሰው፣ **“የህዲይኩሙ-ልላሁ ወዩስሊሑ ባለኩም፡ ፡** /አላህ ቀጥተኛውን መንገድ ይምራችሁ፡፡ ሁኔታችሁንም ያስተካክልላችሁ፡፡/” ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ከዚህ በላይ ያሳለፍነው የአቡ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ አመልክቷል፡፡

## 2 አንድ ሰው አነጥሶት አላህን ካላመሰገነ አላህ ይማርህ አለማለት ነቢያዊ ፈለግ ነው፡ ፡

ያስነጠሰው ሰው አላህን ካልመሰገነ አላህ ይማርህ ማለት ነቢያዊ ፈለግ አይደለም፡፡ በአንጻሩ አላህ ይማርህ አለማለቱ ነው ነቢያዊ ፈለጉ፡፡ አነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ሁለት ሰዎች ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- አነጠሱ፡ ፡ አንደኛውን አላህ ይማርህ ሲሉት ሌላኛውን አላሉትም፡፡ አንደኛው ሰውዬ፣ ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህን ሰው አላህ ይማርህ አሉት፤ እኔን ግን አላህ ይማርህ አላሉኝም፡፡› አላቸው፡፡ እሳቸውም፣ **“ይኸኛው አላህን አመሰገነ፣ አንተ ግን አላህን አላመሰገንክም፡ ፡”** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6225) ላይ ዘግበውታል፡፡ ይህ እንዲህ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የፈጸሙት ተግባር ነው፡፡ የተናገሩትን ቃል ደግሞ ሙስሊም ከአቢ ሙሳ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሐዲሥ ነው፡፡ በዚህ ሐዲሥ ላይ አቢ ሙሳ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ « የአላህ መልከእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ከእናንተ መካከል አንዳችሁ ካነጠሰና አላህን ካመሰገነ አላህ ይማርህ በሉት፡ ፡ አላህን ካላመሰገነ አላህ ይማርህ አትበሉት፡ ፡”** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2992) ላይ ዘግበውታል፡፡

ነገር ግን ልክ አባት ልጁን ወይም መምህር ተማሪውን እንደሚያስተምረው ወ.ዘ.ተ ዓይነት የማያውቀውን ሰው ይህን ነቢያዊ ፈለግ ለማስተማር ከሆነ **‹‹አልሐምዱሊልላህ፡ ፡››** በል ይለዋል፡፡

እንደዚሁ ሰውየው ጉንፋን የያዘው ከሆነ ከሶስተኛው ማስነጠስ በኋላ አላህ ይማርህ አይባልም፡፡ ሶስት ጊዘ ካስነጠሰ ግን አላህ ይማርህ ይባላል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን አይባልም፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-** አቡ ዳዉድ ሱነን በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ወንድምህን ሶስት ጊዜ አላህ ይማርህ በለው፡ ፡ ከዚያ በላይ ከጨመረ እሱ ጉንፋን ነው፡ ፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አቡ ዳዉድ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5034) ላይ የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ሐዲሡን መውቁፍና መርፉዕ ነው ብለዋል፡፡ *ሰሒሑ አቡ ዳዉድ ቅጽ ፡ 4 ገጽ ፡ 308፡፡*

ይህን ሐዲሥ ሙስሊም በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባቸው ከሰለመተ ኢብን አል-አክወዕ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደዘገቡት፣ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዘንድ አንድ ሰው ሲያነጥስ፣ **“አላህ ይማርህ፡ ፡”** አሉት፡፡ እንደገና አነጠሰ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሰውየው ጉንፋን የያዘው ነው፡ ፡”** ሲሏቸው ሰምተዋል የሚለው ሐዲሥ ይደግፈዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2993) ላይ ዘግበውታል፡፡

ከዚህ በላይ ከሰፈረው አንድ ያስነጠሰው ሰው በሁለት ሁኔታዎች አላህ ይማርህ አይባልም፡፡ እነርሱም፡-

1. -በእጅጉ የላቀውን- አላህን ካላመሰገነ፣
2. ከሶስት በላይ ካስነጠሰ፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው ጉንፋን ይዞታልና ነው፡፡

## የማፈሽግ ነቢያዊ ፈለጎች፡-

### ከማፋሸግ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል ማፋሸጉን መደበቅ ወይም በእጅ መመለስ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“”የሚያነጥሱ ሰዎችን አላህ ይወዳል፡፡ ማፋሸግንም ይጠላል፡፡ አንድ ሰው አነጥሶት አላህን ካመሰገነ ሲያስነጥስ በሰሙት በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ አላህ ይማርህ የማለት ግደታ አለባቸው፡፡ ማፋሸግ ግን በርግጥ እሱ ከሸይጣን ነው፡፡ በተቻለው አቅም ይመልሰው፡፡ ሰውየው፣ ‹ሃ…ህ› ካለ ሸይጣን በእሱ ይስቃል፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2663) ላይ ዘግበውታል፡፡

ሙስሊም ከአቢ ሰዒድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-በዘገቡት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳችሁ ካፋገ አፉን በእጁ ይያዝ፡፡ በርግጥ ሸይጣን ይገባልና ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2995) ላይ ዘግበውታል፡፡ ማፋሸግን መደበቅ አፍን በመዝጋት ይህም አፍ እንዳይከፈት በማድረግ ወይም ከንፈርን በጥርሶች አጥብቆ በመያዝ ወይም እጅን አፍ ላይ በማድረግ ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉት ሊፈጸም ይችላል፡፡

ለሚያፋሽግ ሰው ሲያፋሽግ ድምጹን ማድረግ የለበትም፡፡ ለምሳሌ፣«ህ...ሃ....አህ» ወይም «አአአአ.....ህ» ወ.ዘ.ተ እንደመሳሰሉት ዓይነቶችን ድምጽ በማውጣት ማፋሽግ የለበትም፡፡ ይህ ሸይጣን በእሱ ላይ እንዲስቅበት የሚያደርገው ጥሪ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

አቢ ሁረያራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ማፋሸግ ከሸይጣን ነው፡፡ አንዳችሁ ካፈሸገ በተቻለው አቅም ይመልሰው፡፡ ‹ሃ....ህ› ካለ ሸይጣን ይስቃል፡፡”** ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3298)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2994) ላይ ዘግበውታል፡፡

ማሳሰቢያ፡- አንዳንድ ሰዎች ከፋሸጉ በኋላ ከሸይጣን በአላህ መጠበቅ ልማዳቸው አድርገውታል፡፡ ነገር ግን ይህ ምንም ዓይነት ማስረጃ የሌለውና የነቢዩን -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ፈለግን መቃረንን የሚያስከትል ተግባር ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች እዚህ ቦታ ላይ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ያላሉትን ዚክር በራሳቸው ፈጥረው አምጥተዋልና ነው፡፡



## አምስተኛ፡- ሌሎች እለታዊ ሱንናዎች



### ወደመጸዳጃ ቤት ሲገቡና ሲወጡ በሐዲሥ የተዘገቡ ዚክሮችን ማለት፡፡

ወደመጸዳጃ ቤት የሚገባ ሰው በትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባዎች የሠፈሩት ቃላት ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

اللَّهُمَّ إِنِّي أَعُوذُ بِكَ مِنَ الْخُبثِ وَالْخَبَائِثِ

ከአነስ-አላህመልካምሥራዎቻቸውንይውደድላቸው- እንደተወራው፣ ‹‹የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደመጸዳጃ ቤት ሲገቡ፣ **“አልላሁምመ ኢንኒ አዑዙ ቢከ ሚነልኹቡሢ ወልኸባኢሢ፡፡** /አላህ ሆይ! እርኩስ ከሆኑ ወንድ፣ እርኩስ ከሆኑ እንስት ሸይጣኖች ባንተ እጠበቃለሁ፡፡/” ይሉ ነበር፡፡›› ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6322)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (375) ላይ ዘግበውታል፡፡



**‹‹ኹቡሥ››** ማለት ወንድ ሸይጣኖች ማለት ሲሆን ‹‹ኸባኢሥ›› ደግሞ እንስት (ሴት) ሸይጣኖች ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጥበቃ የሚያስፈልገው ከወንድ ሸይጣኖችና ከሴት (እንስት) ሸይጣኖችም ነው፡፡

ቃሉ **‹‹ኹብሥ››** ተብሎ ከተነበበ ትርጉሙ እርኩስና መጥፎ ከሆኑ መናፍስት እንዲሁም ከተንኮልና ከተንኮለኞች ጥበቃን መጠየቅ ማለት ይሆናል፡፡ ስለዚህ በዚህ መልኩ ማለቱ ሁሉንም የሚያጠቃል በመሆኑ ተመራጭ ነው፡፡

### ከመጸዳጃ ቤት የሚወጣ ሰው ሲወጣ የሚከተለውን ማለቱ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡-

**غُفْرَانَكَ**

ሙስነድ በተሰኘው የአሕመድ የሐዲሥ መድብል ላይ እንዲሁም በአቢ ዳዉድና አት-ቲርሚዚይ የሐዲሥ ዘገባ ላይ እንደሰፈረውና አል-አልባኒይ ትክክለኛቱን ባረጋገጡት የዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ዓኢሻ፣ ‹‹የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ከመጸዳጃ ቤት ሲወጡ፣ “ጉፍራነክ፡፡ /ጌታዬ ሆይ! ምሕረትህን ለግሰኝ፡፡/” ይሉ ነበር፡፡ አሕመድ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (25220)፣ አቡ ዳዉድ በቁጥር (30) እንዲሁም አት-ቲርሚዚ በቁጥር (7) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ ተሕቂይቁ ሚሽካቱ-ል-መሳቢይሕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ፡ 116፡፡

### ኑዛዜን መጻፍ ነቢያዊ ፈለግ ነው



ማንኛውም ሙስሊም በሕመም ላይ ሳለም ሆነ በጤንነት ላይ እያለ ኑዛዜውን መጻፉ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “ማንኛውምኑዛዜ ሊያደርገው የሚፈልገው አንዳች ነገር ኖሮት በእሱ ዘንድ ኑዛዜው ተጽፎ ካልሆነ በስተቀር ሁለት ሌሊቶችን ማሳደር የሙስሊም መብት አይደለም፡፡” ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2783)፣ ሙስሊም በቁጥር (1626) ላይ ከኢብን ዑመር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡ በዚህ ሐዲሥ ውስጥ ሁለት ሌሊቶችን መጥቀሳቸው ጊዜውን ለመገደብ ሳይሆን፣ የተፈለገው ሃሳብ ኑዛዜው ሳይጻፍ ጥቂት ቀናት እንዳያልፉት ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሰው መቼ ይሙት ስለማይታወቅ ነው፡፡ ይህ ሁሉም ሊተገብረው የሚገባ ነቢያዊ ፈለግ ነው፡፡

እንደዘካት፣ ሐጅና ማካካሻ ዓይነት በእሱ ላይ ያሉ የአላህ ሐቆችን ወይም እንደእዳና አደራን መመለስ ዓይነት በእሱላ ላይ ያሉ የሰው ልጅ ሐቆች ካሉ እንዲፈጸምለት ኑዛዜ መተው ነቢያዊ ፈለግ ሳይሆን ግዴታ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሁኔታ ግዴታ የሆኑ ሐቆችን ከመወጣት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው፡፡ ዋና መሰረታዊ መመሪያ ቃሉ ደግሞ [ግዴታ የሆነ ተግባር ከእሱ በስተቀር የማይሟላ ከሆነ ይህ ሁኔታ በራሱ ግዴታ ነው፡፡] የሚለው ነው፡፡

## በግብይት ላይ ልስላሴንና መልካምነት መላበስ



ይህም በግብይት ወቅት ሻጭም ሆነ ገዥ መልካምነትንና ልስላሴን መላበስ ይኖርባቸዋል። ዋጋ በመስማማት ላይ አንዱ በሌላው ላይ መበርታትና መከራከር የለበትም። ይልቁንም መልካም መሆን አለባቸው።

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ጃቢር ኢብን ዐብዱላህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ሲሸጥ፣ ሲገዛና ሲድዳኝ መልካም የሆነን ሰው አላህ አዘነለት።"** ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2076) ላይ ዘግበውታል።

የራሱን ሐቅ ሲጠይቅ እንደዚሁ ነው። የራስን መብት ከሌላው ሲጠይቁ ገር በሆነ ሁኔታና በለሰለሰ አኳኋን ማድረጉ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል ነው። ምንክያቱም ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ «ሲድዳኝም» ብለዋልና ነው።

## ከእያንዳንዱ ዉዱእ በኋላ ሁለት ረከዐህ ሰላት መስገድ



ይህ ተግባር በቀን ውስጥ ታላላቅ ምንዳዎች ከሚመዘገብባቸው ነቢያዊ ፈለግ ከሆኑ ተግባራት መካከል አንዱ ነው። ይህ ታላቅ ምንዳም ጀነት መግባት ነው። አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በፈጅር ሰላት ወቅት፣ **"ቢላል ሆይ! በኢስላም ውስጥ ከተሰራሃቸው ሥራዎች መካከል በጣም የላቀውን ሥራ ንገረኝ። እኔ በእርግጥ የጫማዎችህን ኮቴ ድምጽ ጀነት ፊት ሰምቻለሁ።"** አሉ። ቢላልም፣ ‹ሌሊት ወይም ቀን ላይ ዉዱእ ካደረግኩ በኋላ በዚያ ዉዱእ እንድሰግድ የተጻፈልኝ ይህል ከመስገዴ በስተቀር በእኔ ዘንድ የላቀ ሥራ አልሠራሁም።› አላቸው።» ብለዋል። ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር (1149)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁር (2458) ላይ ዘግበውታል።



### ሰላትን መጠባበቅ

ሰላትን መጠባበቅ በቀን ውስጥ ታላላቅ ምንዳዎች ከሚመዘገብባቸው ነቢያዊ ፈለግ ከሆኑ ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡፡

**ለዚህም ማስረጃው፡-**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳቸሁ ሰላት እስካሰረችው ድረስና ከሰላት በስተቀር ወደቤተሰቡ እንዳይመለስ ሌላ ነገር ከሌለ ሰላት ውስጥ ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ ሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (659)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (649) ዘግበውታል፡፡ ይህ ሰው ሰላትን በመጠባበቁ ምክንያት የሰላትን ምንዳ ያገኛል፡፡

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንዳቸሁ ዉዱእ እስካላበላሸና በመስገጃው ላይ እስካለ ድረስ መላእክቶች፣ ‹አላህ ሆይ! ወንጀሉን ማርለት፡፡ አላህ ሆይ! እዘንለት፡፡›በማለት ዱዓ ያደርጉላታል፡፡ አንዳቸሁ ሰላት እስካሰረችው ድረስና ከሰላት በስተቀር ወደቤተሰቡ እንዳይመለስ ሌላ ነገር ከሌለ ሰላት ውስጥ ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ ሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (659)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (649) ላይ ዘግበውታል፡፡ በሙስሊም ሌላ ዘገባ፣ **“በዚያ ላይ እስካልተጎዳ፣ በዚያ ላይም ወዱእ እስካለበላሸ ድረስ፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (649) ላይ ዘግበውታል፡፡

ይህ ማለት ምንዳው በተቀመጠበት ሥፍራ ላይ እንዳች ጎጂ ነገር አለማጋጠምና ወዱእ ለአመፍታት (አለመበላሸት) በሚሉት መሥፈርቶች የተሳሰረ ነው፡፡

### መፋቂያ



መፋቂያ በጊዜ ካልተገደበና በማንኛውም ጊዜ ሊተገበሩ ከሚችሉ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “በመፋቂያ ላይ አበዛሁባችሁ፡፡” እስከሚሉ ድረስ በእሱ ላይ በብዛት ያነሳሱ ነበር፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ቁጥር (888) ከአነስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- “መፋቂያ ለአፍ ንጽሕናን መጠበቂያ ለጌታ ማስደሰቻ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አን-ነሳኢይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (5) ከዓኢሻህ -አላህ መልካም ሥራዎቻችሁን ይውደድላቸው- የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይም የሐዲሡን ትክክለኛነት አረጋግጠዋል፡፡ አል-ኢርዋእ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 105፡፡

የመፋቂያ ነቢያዊ ፈለግነት የሚበረታው ከዚህ በላይ በሳለፍናቸውና ሌሊት እንደመነሳት፣ ዉዱእ በሚደረግበት ወቅት፣ በእያንዳንዱ ሰላት ወቅትና ወደቤት በሚገባበት ወቅት በመሳሰሉት በቀንና በምሽት በሚደጋገሙ ሥፍራዎች ላይ ነው፡፡ -አላህ ይበልጥ ዐዋቂ ነው-፡፡

## ለእያንዳንዱ ሰላት ዉዱእን ማደስ



አንድ ሙስሊም ከእያንዳንዱ ሰላት ዉዱእ ማድረጉ ነቢያ ፈለጎችን እንደመከተል ይቆጠርለታል፡፡ ለምሳሌ ለመግሪብ ሰላት ዉዱእ ካደረገና በዚሁ ዉዱእ የመግሪብ ሰላት ከሰገደ በኋላ ዉዱእ ያለው ቢሆንም የዒሻእ ሰላት ከደረሰ ዉዱእ ማድረጉ ነቢያዊ ፈለግን እንደመተግበር ይታሰብለታል፡፡ ነቢያዊ ፈለጉ ለእያንዳንዱ ሰላት አዲስ ዉዱእ ማድረጉ ነው፡፡

**ለዚህ ማስረጃው፡-**

ቡኻሪ እንደዘገቡት፣ «ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በእያንዳንዱ ሰላት ዉዱእ ያደርጉ ነበር፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በቁጥር (214) ዘግበውታል፡፡

እንደዚሁም ማንኛውም ሙስሊም ቀኑን ሙሉ ንጹሕ መሆኑ ከነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሠውባን -አላህ መልካም ሥራዎቻቸው ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሙእሚን ካልሆነ በስተቀር ንጽሕናን አይጠብቅም፡፡”** ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አሕመድ በቁጥር (22434)፣ ኢብን ማጀህ በቁጥር (277)፣ አድ-ዳረሚይ በቁጥር 655) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡ 1 ገጽ ፡ 225፡፡

## ዱዓእ

**አንድ ሙስሊም ዱዓእ ለማድረግ ሲፈልግ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ነቢያዊ ፈለጎች፡፡ ከነቢያዊ ፈለጎቹ መካከል፡-**

### 1 ንጹሕ ሆኖ ዱዓእ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

አቡ ሙሳ አል-አሽዐሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ነቢዩ -የአላህ እዝነተና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደአውጣስ ጦር ሲልኳቸው ከአጎታቸው ከአቢ ዓሚር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ጋር የነበራቸውን ታሪክ እንዳስተላለፉት አቢ ዓሚር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ተገደሉ፡፡ ከመሞታቸው በፊት ለነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላምታ እንዲያደርሱላቸውና ዱዓእ እንዲያደርጉላቸው አቢ ሙሳ አል-አሽዐሪይን አደራ አሏቸው፡፡ አቡ ሙሳም -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው-፣ «የኛንና የአቢ ዓሚርን ዜና ነገርኳቸው፡፡ «አላህ ወንጀሎቼን እንዲምርልኝ እንዲጠይቁልኝ ንገራቸው፡፡» ብሎኛል ብዬ ነገርኳቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛም ውሃ

እንዲመጣላቸው አደረጉ፡፡ ከውሃውም ዉዱእ አደረጉ፡፡ ከዚያ የብብታቸውን ንጣት እስከማይ ድረስ እጆቻቸውን አነሱና፣ **“አላህ ሆይ! ለዑበይድ ወንጀሎቹን ማርለት፡፡ ለዓሚር አባት፡፡” አሉ፡፡ አያይዘውም፣ “አላህ ሆይ! በትንሳኤ እለት ከበርካታ ፍጡራንህ በላይ አድርገው፡፡”** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (4323)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2498) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 2 ወደቂብላህ አቅጣጫ መዞር

ዐብዱላህ ኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዲህ አሉኝ፣ «በበድር ጦርነት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላማታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ወደአጋሪያን ተመለከቱ፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ሰሐቦቻቸው ደግሞ ሶስት መቶ አስራ ዘጠኝ ናቸው፡፡ የአላህ ነቢይ ወደቂብላ ዞሩ፣ ከዚያም እጆቻቸውን አንስተው፣ **“አላህ ሆይ! ቃል የገባህልኝን ፈጽምልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ቃል የገባህልኝን ስጠኝ፡፡ አላህ ሆይ! ከኢስላም የሆኑ እነዚህ ቁጥራቸው ጥቂት የሆነ ታጋዮች ቢጠፉ በምድር ላይ አትመለክም፡፡”** በማለት ጌታቸውን ተለማመጡ፡፡ እጆቻቸውን አንስተው፣ ወደቂብላህ ዞረው ከትከሻቸው ላይ ያለው ጭርቃቸው እስኪወድቅና አቡ በክር ከእሳቸው ጋር በመሆን **‹‹የአላህ ነቢይ ሆይ! ጌታህን መጠየቅህ ይብቃህ፡፡ እሱ ቃል የገባልዎን ይፈጽምልዎታል፡፡...››** እስከሚሏቸው ድረስ ጌታቸውን ከመማጸን አልታከቱም፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1763) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 3 እጅን ማንሳት

ከዚህ በላይ ባሳለፍነው የኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ውስጥ፣ «የአላህ ነቢይ ወደቂብላ ዞሩ፣ ከዚያም እጆቻቸውን አነሱ፡፡» የሚለው የሚገኝ ሲሆን ከዚህ ሌላ ይህን ነቢያዊ ፈለግ በተመለከተ በርካታ ሐዲሦች ተዘግበዋል፡፡

### 4 ዱዓእን -በእጅጉ የላቀውንና የተከበረውን- አላህን በማወደስና በመልእክተኛው -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ላይ ሰለዋት በማድረግ መጀመር፡፡

አት-ቲርሚዚይ ከፉዳለህ ኢብን ዑበይድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣«ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ተቀምጠው ሳለ አንድ ሰው መጣና ሰገደ፡፡ በሰላቱ ውስጥም፣ ‹አልላምመ ኢግፊር ሊ ወርሐምኒ፡፡ /አላህ ሆይ! ወንጀሎቼን ማርልኝ፣ እዘንልኝም፡፡/› አለ፡፡ የአላህ መልእክተኛም -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- **“አንተ የምትሰግድ ሰው ሆይ! ቸኮልክ፡፡ ስትሰግድ ከተቀመጥክ አላህን እሱ የምስጋና ባለቤት ሆኖ ሳለ አመስግን፡፡ በእኔ ላይም ሰለዋት አድርግ፡፡ ከዚያ ለምነው፡፡”** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን አት-ቲርሚዚይ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3476) የዘገቡት ሲሆን አል-አልባኒይ ትክክለኛነቱን አረጋግጠዋል፡፡ ሰሒሑ-ልጃሚዕ ቅጽ ፡1 ገጽ ፡172፡፡

### 5 -በእጅጉ የላቀውን- አላህን መልካም በሆኑት ስሞቹ መለመን

ሰውየው መልካም ከሆኑት የአላህ ስሞች መካከል ከዱዓው ጋር የሚስማማና የሚጣጣም ይመርጣል፡፡ -ውድቅና ከንቱ ከሆኑ ንግግሮች በእጅጉ የጠራውን- አላህ ሲሳይ ከጠየቀ፣ **‹‹ሲሳይ ሰጪ የሆንከው ጌታ ሆይ!››** በማለት ይላል፡፡ -በእጅጉ የላቀውን- አላህ እዝነት የሚጠይቀው ከሆነ፣ **‹‹እጅግ በጣም አዛኝ እጅግ ሩሕሩሕ የሆንከው ጌታ ሆይ!»** ይላል፡፡ -በእጅጉ የላቀውንና የተከበረውን- አላህ ክብር የሚጠይቅ ከሆነ፣ **‹‹እጅግ የተከበርከው ጌታ ሆይ!››** ይላል፡፡ -በእጅጉ የላቀውንና የተከበረውን- አላህ ምሕረት የሚጠይቅ ከሆነ፣ «እጅግ መሐሪ የሆንከው ጌታ ሆይ!» ይላል፡፡ ጤናን የሚጠይቀው ከሆነ፣ **‹‹አዳኝ የሆንከው ጌታ በሆይ!››** ይላል፡፡

እንደዚሁ በእጅጉ የላቀው አላህ፣ **"ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት፤"** (አል-አዕራፍ ፡ 180) ባለው መሠረት፣ ከዱዓቸው ጋር በሚስማማው ዱዓእ ያደርጉ ነበር፡፡

### 6 ደዓእን መደጋገምና በእሱም ላይ መለማመጥ

በዚህ ላይ ከዚህ በላይ ያሳለፍነው የኢብን ዐብባስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ሐዲሥ ማስረጃ ይሆናል፡፡ በዚህ ሐዲሥ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"አልላሁምመ አንጂዝ ሊ ማ ወዐድተኒ፣ አልላሁምመ አቲ ማ ወዐድተኒ፡፡** / አላህ ሆይ! ቃል የገባህልኝ ፈጽምልኝ፡፡ አላህ ሆይ! ቃል የገባህልኝን ስጠኝ፡፡" ሲሉ ከትከሻቸው ላይ ያለው ጭርቃቸው እስኪወድቅና አቡ በክር ከእሳቸው ጋር በመሆን «የአላህ ነቢይ ሆይ! ጌታህን መጠየቅህ ይብቃህ፡፡» እስከሚሏቸው ድረስ ጌታቸውን ከመማጸን አልታከቱም ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1763) ላይ ዘግበውታል፡፡

እንደዚሁ ቡኻሪና ሙስሊም ከአቢ -ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- በዘገቡት ሐዲሥ ላይ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ለዱሥ ጎሣ ባደረጉት ዱዓእ ላይ፣ **"አላህ ሆይ! የዱስ ጎሳዎችን ቀጥተኛውን መንገድ ምራቸው፡፡ አምጣቸውም፡፡ አላህ ሆይ! የዱስ ጎሳዎችን ቀጥተኛውን መንገድ ምራቸው፡፡ አምጣቸውም፡፡"** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2937)፣ ሙስሊም በቁጥር (2524) ላይ ዘግበውታል፡፡

እንደዚሁ በሙስሊ ትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ፣ **"ጉዞ በሚያስረዝም፣ ፀጉሩ የተቆጣጠረና አቧራ የለበሰ ሆኖ እጁን ወደሰማይ ዘርግቶ ጌታዬ! ጌታዬ! ይላል፡፡"** የሚል ተዘግቧል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (1015) ላይ የዘገቡት ሲሆን ይህ በመደጋገም መለመን ነው፡፡

ነቢያዊ ፈለጉ ሶስት ሶስት ጊዜ ዱዓእ ማድረጉ ነው፡፡ ኢብን መስዑድ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ባስተላለፉትና ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሥ፣ «ዱዓእ ሲያደርጉ ሶስት ሶስት ጊዜ ያደርጉ ነበር፡፡ ከጠየቁም ሶስት ሶስት ጊዜ ይጠይቁ ነበር፡፡ ካሉ በኋላ ሶስት ሶስት ጊዜ፣ **"አልላሁምመ ዐለይከ ቢቁረይሽ፡፡** /አላህ ሆይ! በቁረይሽ ላይ ይሁንብህ፡፡/" አሉ፡፡» የሚል ይገኝበታል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (240)፣ ሙስሊም በቁጥር (1794) ላይ ዘግበውታል፡፡

### 7 ዱዓእን ድብቅ ማድረግ

ይህም እጅጉን የላቀው አላህ እንዲህ ስላለ ነው፡፡ **"ጌታችሁን ተዋርዳችሁ÷ በድብቅም ለምኑት፤"** (አል-አዕራፍ ፡ 55)፡፡ ዱዓእን መደበቅ ለአላህ ቅን ወደመሆን በእጅጉ የቀረበ ነው፡፡ ለዚህም ነው አላህ ዘከሪያን -የአላህ ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- እንዲህ በማለት ያወደሳቸው፣ **"ጌታውን የምስጢርን ጥሪ በተጣራ ጊዜ÷"** (መርየም ፡ 3)፡፡ ቅንነትን በመጠየቅ እንደሆነ በአንዳንድ የተፍሲር ኢማሞች ዘንድ ሰፍሯል፡፡

ፋይዳ፡- ምናልባት አንዳንድ ሰዎች፤ ዱዓዬ ውስጥ ምንድን ነው የምለው? ብለው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡



**መልሱ፡-** ምድራዊውንም ሆነ የወዲያኛው ዓለም ጉዳዮችን ጠይቁ፡፡ ጥቅል ይዘት ባላቸው ቃላት በዱዓችሁ ውስጥ ተበራቱ፡፡ እነዚህ ዱዓዎች በቁርአንና በሐዲሥ ላይ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ በውስጣቸው ለምድራዊውም ሆነ ለወዲያኛው ዓለም ጠቃሚ የሆኑ ዱዐዎች አሏቸው፡፡ ለነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- የቀረበውን ይህን ጥያቄ እስኪ አስተውሉ፡፡ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ለአንድ ሰው በምድራዊውና በወደያኛው ዓለም ሊጠቅሙት በሚችሉ ታላቅ የሆኑ ቃላት ነበር ምላሻቸውን የሰጡት፡፡ እነዚህ ቃላት ምነኛ የላቁ ስጦታዎች ናቸው፡፡ ታዲያ እናንተም አጥብቃችሁ ልትይዟቸውና ልታስተነትኗቸው ይገባል፡፡

اللَّهُمَّ اغْفِرْ لِي ، وَارْحَمْنِي ، وَعَافِنِي ، وَارْزُقْنِي

አቢ ማሊክ አል-አሽጀዒይ ከአባታቸው -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ « አንድ ሰው ወደየአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- መጣና፡- ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አላህን ስጠይቅ ምን ልበል?› በማለት ሲጠይቃቸው እሳቸውም፣ **"አልላሁምመ ኢግፊር ሊ ወርሐምኒ ወህዲኒ ወዓፊኒ ወርዙቅኒ፡፡** /አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማርልኝ፣ እዘንልኝ፣ ቀጥተኛውን መንገድ ምራኝ፣ ይቅር በለኝ፣ ሲሳይም ስሰጠኝ፡፡/ አሉና ከአውራ ጣታቸው በስተቀር ሌሎች ጣቶቻቸውን ሰበሰቡና፣ **"እነዚህ ቃላት በምድራዊ ሕይወትህና በወዲያኛው ዓለም ሕይወትህ የሚጠቅሙህን ነገሮችን ሁሉ በእርግጥ ይሰበስቡልሃል፡፡"** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2697) ላይ ዘግበውታል፡፡

እሳቸው ባስተላለፉት ሌላ ዘገባ ደግሞ፣ ‹‹አንድ ሰው ኢስላምን ከተቀበለ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሰላትን ያስትምሩት ነበር፡፡ ከዚያም በእነዚህ ቃላት ዱዓእ እንዲያደርግ ያዙታል፣ **“አልላሁምመ ኢግፊር ሊ ወርሐምኒ ወህዲኒ ወዓፊኒ ወርዙቅኒ፡፡** /አላህ ሆይ! ወንጀሌን ማርልኝ፣ እዘንልኝ፣ ቀጥተኛውን መንገድ ምራኝ፣ ይቅር በለኝ፣ ሲሳይም ስሰጠኝ፡፡/” ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2697) ላይ ዘግበውታል፡፡

- ሌላኛው ፋይዳ፡- ማንኛውም ሰው በስውር ልቦው ለወንድሙ ዱዓእ ማድረጉ ነቢያዊ ፈለግ የሆነ ተግባር ከመሆኑም ባሻገር በአላህ ፈቃድ ተቀባይነትን የሚያገኝ ነው፡፡ ዱዓእ ለሚያደርገው ሰው የላቀ ትሩፋት አለው፡፡ ሙስሊም ትክክለኛ በሆነው የሐዲሥ ዘገባ ከአቢ ደርዳእ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደዘገቡት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዘነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “አንድ ሙሰሊም የሆነ ሰው በስውር ልቦናው ለወንድሙ የሚያደርገው ዱዓእ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በየራሱ ጫፍ ላይ ተወከለ መልአክ አለ፡፡ ለወንድሙ በመልካም ዱዓእ ባደረገ ጊዜ በእሱ ላይ የተወከለው መልአክ፡- አሚን ላንተም በአምሳያው፡፡ ይላል፡፡” ብለዋል፡፤ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2733) ላይ ዘግበውታል፡፡



- በዚህ በራስ መጠመዶችና ዝንጋቴዎች በበዙበት ዘመን ልብቃህ ከነፍስህ ጋር ከሰዎች ገለል ብለህ ነፍስህን ቁጭ ብለህ ስራን ለመተሳሰብህ መፈለግህና ጌታህን ማውሳትህ ምን ያህል የላቀ ተግባር ነው፡፡

## በእጅጉ የላቀውን አላህ ማውሳት እለታዊ ከሆኑ ነቢያዊ ፈለጎች መካከል አንዱ ነው፡፡

**የላቀው፡-** የአላህ ንግግር የሆነውን ቁርኣንን ማንበብ ነው፡፡ እሱን በመቅራት አምልኮታዊ ተግባር የቀደምት መልካም ትውልዶች ዓይኖች በርካታ ሌሊቶችን ካለ እንቅልፍ አሳልፈዋል፡፡ መኝታዎቻቸውንም ረስተዋል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፤ **"ከሌሊቱ ጥቂትን ብቻ ይተኙ ነበር፡፡ በሌሊት መጨረሻዎችም እነሱ ምሕረትን ይጠይቃሉ፡፡"** (አዝ-ዛሪያት ፡ 17 – 18)፡፡ እነዚህ ትውልዶች ሌሊታቸውን ቁርኣን በመቅራትና ሌሎች በአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ሐዲሥ የተዘገቡ አዝካሮችን በማለት ከንጋቱ ጋር ያገናኙ ነበር፡፡ አላህ ምስጋና ይገባው በባለቤቶቹ ምን ያህል ያማረ ሌሊት ነው! እኛስ አላህ ይሁነን፡፡ ስንትና ስንት ሌሊቶችን ዘንግተን ከስረናል፡፡ ሌሊቶቻችንን ምሽቶቻችንን በከንቱ በማሳለፉችንና በእነሱ ላይም በማጓደላችን ከስረናል፡፡ ምናልባት ከእኛ መካከል ጌታችን ያዘነለት ካልሆነ በስተቀር አምላካችንን መወንጀላችንን ለእሱ አሳልፈን ሰጥተናል፡፡

*ሐምማድ ኢብን የዚድ እንዳስተላለፉተና ዐጣእ ኢብን አስ-ሳኢብ እንዳወሩት አባ ዐብዱርረሕማን እንዲህ ብለዋል፤ "ቁርኣንን አስር አንቀጽ ከተማሩ በኋላ በእነሱ ሳይተገብሩ ወደሌሎች አስር አንቀጾች ከማይሻገሩት ሕዝቦች ተምረናል፡፡ቁርኣንን ከተግባር ጋር እንማር ነበር፡፡ ከእኛ በኋላ ቁርኣንን እንደውሃ መጠጣት የሚጠጡና ሥሮቻቸውን ላይ የማይደርስ የሆኑ ሕዝቦች ይወርሱታል፡፡" ሰየር አዕላሙ-ንኑበላእ ቅጽ፡ 4 ገጽ ፡ 269፡፡*

## ዚክር በውስጡ ለልቦና ሕይወት አለው



በተለይ በአሁኑ ሩጫዎች በበዙበት ዘመን አብዛኛዎቻችን የልቦናችንን መዛግና አላህን ከማስታወስ መዘናጋት አስመልክተን ስሞታ እናቀርባለን፡፡ ልቦና ሕይወት የሚኖረው አላህን በማውሳት (በዚክር ) ነው፡፡ ከአቡ ሙሳ አል-አሽዐሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፤ **"ጌታውን የሚያወሳና የማያወሳ ምሳሌ እንደሕያውና ሙት ነው፡፡"** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ዘግበውታል፡፡ በሙስሊም የሐዲሥ ዘገባ ደግሞ ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፤ **"በውስጡ አላህ የሚወሳበት ቤትና የማይወሳበት ቤት ምሳሌ እንደሕያውና ሙት ነው፡፡"** ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6407)፣ ሙስሊም በቁጥር (779) ላይ ዘግበውታል፡፡

**-በእጅጉ የላቀውና የተከበረው- አላህ እሱን በማውሳት ላይ በበርካታ ሥፍራዎች ላይ አደራ ብሏል፡፡ ከአብነት ያህልም፡-**

1. -በእጅጉ የላቀው- አላህ ባሪያዎ እሱን ማስታወስን እንዲያበዙ አደራ ብሏቸዋል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፣ **"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት፡፡ በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻም አጥሩት፡፡"** (አል-አሕዛብ ፡ 41 – 42)፡፡

2. -በእጅጉ የላቀው- አላህ እሱን የሚያወሱ ወንዶችንና ሴቶችን በምሕረት፣ በላቀ ምንዳና ሽልማት ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፣ **"አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም አላህ ለነረትሱ ምሕረትንና ታላቅ ምንዳን አዘጋጅቶላቸዋል፡፡"** (አል-አሕዛብ ፡ 35)፡፡

3. አላህ -በእጅጉ የላቀውና የተከበረው- ከመናፍቃን መገለጫ ባሕሪያት አስጠንቅቆናል፡፡ መናፍቃን -በእጅጉ የላቀውና የተከበረው- አላህን ያስታውሳሉ፡፡ ነገር ግን እሰኪ ምን ያህል እንደሚያስተውሱት ከእኔ ጋር አስተውል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፣ **"መናፍቃን አላህን ያታላሉ፤ እርሱም አታላያቸው ነው፤ (ይቀጣቸዋል)፤ ወደሰላትም በቆሙ ጊዜ ታካቾች ሰዎችን የ፣የሚያሳዩ ኾነው ይቆማሉ፤ አላህንም ጥቂትን እንጂ አያወሱም፡፡"** (አን-ኒሳእ ፡ 142)

4. -እጅጉን የተከበረውና የላቀው- አላህ በሃብትና በልጆች እሱን ከማስታወስ እንዳንዘናጋ አስጠንቅቆናል፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፣ **"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያጣሉዋችሁ፤ ይህንንም የሚሠሩ ሰዎች እነዚያ ከሳሪዎቹ ናቸው፡፡"** (አል-ሙናፊቁን ፡ 9)

5. እስኪ ይህን ታላቅ ትሩፋት፣ ታላቅ ክብር ከእኔ ጋር አስተውል፡፡ -በእጅጉ የላቀው አላህ- እንዲህ ብሏል፣ **"አስታውሱኝ አስታውሳችኋለሁ" በሐዲሥ አል-ቁድሲይ ላይ ደግሞ እንዲህ ብሏል፣ "እኔ ባሪያዬ በእኔ ላይ እንደጠረጠረኝ ነኝ፡፡ ካወሳኝ እኔ ከእሱ ጋር ነኝ፡፡ በራሱ ካስታወሰኝ በራሴ አስታውሰዋለሁ፡፡** ከሰዎች ጋር ካስታወሰኝ ከእነሱ ከተሻሉት ጋር ሆኜ አስታውሰዋለሁ፡፡" ሐዲሡን ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (7405)፣ ሙስሊም በቁጥር (2675) ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ዘግበውታል፡፡

**ዚክርን አስመልክቶ ከነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- በሐዲሥ የተዘገቡ በርካታ ናቸው፡፡ ከእነርሱም መካከል፡-**

1. **لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ، وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ**

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አንድ መቶ ጊዜ ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ወሕደሁ ላ ሸሪይከ ለህ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር አስር ጫንቃዎችን ነጻ ከማውጣት ጋር ምንዳው ሲስተካከልለት አንድ መቶ ምንዳዎች ይጻፉለታል፣ አንድ መቶ ሐጢአቶችም ይሰረዩለታል፣ ይህች ቃልም በዚያ ቀን እስኪያመስ ድረስ ከሸይጣን ጥበቃ ትሆንለታለች፡፡ እሱ ከሰራው ሥራ የተሻለ ሥራ ሰርቶ ማንም አይመጣም እሱ የሰራውን ዓይነት ሥራ አብዝቶ ሰርቶ ከሚመጣ ሰው በስተቀር፡፡ በቀን ውስጥ አንድ መቶ ጊዜ ሱብሓነ-ልላህ ወልሐምዱሊ-ልላህ ያለ ሐጢአቶቹ የባሕር አረፋ ያህል ቢሆኑም ይሰረዩለታል፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (3293)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2691) ላይ ዘግበውታል፡፡

2. **لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللهُ وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ، لَهُ الْمُلْكُ وَلَهُ الْحَمْدُ وَهُوَ عَلَى كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ**

አቢ አዩብ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት ነቢዩ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“አስር ጊዜ በመደጋገም ላ ኢላሀ ኢልለልላህ ወሕደሁ ላ ሸሪክ ለሁ ለሁልሙልኩ ወለሁልሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸይኢን ቀዲይር ያለ ከኢማዒል ልጆች አራት ነፍሶችን ነጻ እንዳደረገ ነው፡፡”** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6404)፣ ሙስሊም ደግሞ በቁጥር (2693) ላይ ሐዲሡን ዘግበውታል፡፡

3. ሰዕድ ኢብን አቢ ወቅቃስ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «ከአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ዘንድ ነበርን፡፡ እንዲህም አሉን፣ **“አንዳችሁ በየእለቱ አንድ ሺህ ምንዳዎችን ማግኘት ይሳነዋልን?”** አሉ፡፡ አብረውን ከተቀመጡት ሰዎች መካከል አንዱ ጠያቂ፣ ‹አንዳችን እንዴት ሆኖ ነው አንድ ሺህ ምንዳዎችን ሊያገኝ የሚችለው?› በማለት ጠየቃቸው፡፡ እሳቸውም፣ **“አንድ መቶ ተስቢሖችን ያደርጋል፡፡ አንድ ሺህ ምንዳዎችም ይጻፉለታል ወይም አንድ ሺህ ሐጢአቶች ይሰረዩለታል፡፡”** አሉ፡፡» ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2698) ላይ ዘግበውታል፡፡

4 سُبْحَانَ اللهِ وَبِحَمْدِهِ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ ሱብሓነ-ልላህ ወቢሐምዲሂ ያለ ሐጢአቱ የባሕር አረፋ ያህል ቢሆኑም ይሰረዩለታል፡፡"** ብለዋል፡፡ ቡኻሪ በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6405)፣ ሙስሊም በቁጥር (2692) ሐዲሡን የዘገቡት ሲሆን በሌላ የሙስሊም ዘገባ፣ **"ሲያነጋና ሲያመሽ መቶ ጊዜ፣ ሱብሓ-ልላሂ ወቢሐምዲሂ ያለ በትንሳኤ እለት ከእሱ የተሻለ ሥራ ሰርቶ የሚመጣ ሰው አይኖርም እርሱ ያለውን ካለ ወይም በእሱ ላይም ጨምሮ የመጣ ሰው ካልሆነ በስተቀር፡፡"** ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2692) ላይ ዘግበውታል፡፡

لاَ حَوْلَ وَلاَ قُوَّةَ إِلاَّ بِاللهِ

የዚክርን ዓይነቶችና ትሩፋቶች የሚወሱ ሐዲሦች በርግጥ በቁጥር እጅግ በርካታ ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ዚክርን አስመልክቶ ከተዘገቡት ሐዲሦች ሁሉ ይበልጥ ትክክለኛውና ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ዚክርን አስመልክቶ ከዚህ ሐዲሥ ሌላ በርካታ ሐዲሦች ተዘግበዋል፡፡ አቢ ሙሳ አል-አሽዐሪይ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **"ከጀነት ሃብቶች መካከል ከሆኑት ላመላክትህን?"** አሉኝ፡፡ እኔም፡- እንዴታ! አልኳቸው፡፡ እሳቸውም፣ **"ላ ሐውለ ወላ ቁውወተ አልላ ቢላልህ፡፡** /ብልሐትም፣ ብርታትም በአላህ ካልሆነ በስተቀር በሌላ የለም፡፡/" በል አሉኝ፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (4202)፣ ሙስሊም በቁጥር (2704) ላይ ዘግበውታል፡፡

سُبْحَانَ اللهِ ، وَالْحَمْدُ للهِ ، وَلاَ إِلَـهَ إِلاَّ اللهُ ، وَاللهُ أَكْبَرُ

አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንዳስተላለፉት የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ "ስብሓነ-ልላሂ ወልሐምዱሊልላሂ ወላ ኢላሀ ኢልለልላሁ ወልላሁ አክበር ማለቴ በኔ ዘንድ ጸሐይ ከወጣችበት ቀን ይበለት እጅጉን ተወዳጅ ነው፡፡" ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2695) ላይ ዘግበውታል፡፡

**ኢስቲግፋር (ከአላህ ምሕረት መጠየቅ) እንዲሁ የዚክር ዓይነቶች ነው፡፡** ከዚህ በላይ በሙስሊም ከአል-አገርር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- የተዘገበው ሐዲሥ ተጠቅሷል፡፡ እንዲሁም፣ "ብልቀልቢ፣ **በርግጥ በቀን ውስጥ መቶ ጊዜ አላህን ምሕረት እጠይቃለሁ፡፡"** ብለዋል፡፡ ሙስሊም ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2702) ላይ ዘግበውታል፡፡

ይህ የነቢዩ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን- ተግባር ነው፡፡ በአንደበታቸውም በኢስቲግፋር (ምህረትን ከአላህ በመጠየቅ) ላይ አነሳስተዋል፡፡ በሙስሊም ትክክለኛ የሐዲሥ ዘገባ ከአል-አገርር -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- እንደተላለፈው የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“ሰዎች ሆይ! ወደአላህ በንሰሃ ተመለሱ፡፡ በቀን ውስጥ በርግጥ እኔ መቶ ጊዜ ወደርሱ በንሰሃ እመለሳለሁ፡፡”** ብለዋል፡፡ ሙስሊም በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (2702) ላይ ዘግበውታል፡፡

ቡኻሪ ከአቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው በዘገቡት ሐዲሥ አቢ ሁረይራህ፣ «የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝንትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ **“በአላህ እምላለሁ! በቀን ውስጥ በርግጥ ከሰባ ጊዜ በላይ አላህን ምሕረት እጠይቃለሁለ፣ ወደርሱም በንሰሃ እመለሳለሁ፡፡”** ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡» ብለዋል፡፡ ቡኻሪ ሐዲሡን በሐዲሥ ዘገባ ቁጥር (6307) የዘገቡት ሲሆን ማንኛውም የአላህ ባሪያ ከአላህ ምሕረትን ከመጠየቅ መዘናጋት አይገባውም፡፡

سُبْحَانَ اللّٰه وَبِحَمْدِهِ، سُبْحَانَ اللّٰهِ الْعَظِيمِ

የዚክር ነቢያዊ ፈለግን -እንዲሁም ሁሉንም እለታዊ የሆኑ ነቢያዊ ፈለጎችን- በቡኻሪና በሙስሊም ዘግበውታል፡፡ ዚክሩም አቢ ሁረይራህ -አላህ መልካም ሥራዎቻቸውን ይውደድላቸው- ያስተላለፉት ሲሆን የአላህ መልእክተኛ -የአላህ እዝነትና ሰላምታ በእሳቸው ላይ ይሁን-፣ “በምላስ ላይ ቀላል፣ በሚዛን ላይ ከባድ፣ እጅግ በጣም አዛኝ በኾነው ጌታ ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የሆኑ ሁለት ቃላት፡- ሰብሓነ-ልላሂ ወቢሐምዲሂ፣ ሱብሓነ-ልላሂ-ልዐዚይም ናቸው፡፡” ብለዋል፡፡ ሐዲሡን ቡኻሪ በሓዲሥ ዘገባ ቁጥር (6406)፣ ሙስሊም በቁጥር (2694) ፣ላይ ዘግበውታል፡፡

**በጸጋዎቹ መልካም የሆኑ ነገሮች የሚሟሉ ለሆኑት አላህ ምስጋና ይሁን**

Amharic


መቅድሞች



ከአል-ፈጅር ሰላት ወቅት በፊት ያሉ ሱንናዎች



የአል-ፈጅር ሰላት ወቅት ሱንናዎች




የአዝ-ዙህር ሰላት ወቅት ሱንናዎች



የአል-ዐስር ሰላት ወቅት ሱንናዎች



የአል-መግሪብ ሰላት ወቅት ሱንናዎች



የአል-ዒሻእ ሰላት ወቅት ሱንናዎች



የአመጋገብ ሱንናዎች



በሰላምታ፣ በመገናኘትና አብሮ በመቀመጥ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች



በአለባበስና የመዋብ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች



በማንጠስና በማፋሸግ ውስጥ ያሉ ሱንናዎች



ሌሎች ሱንናዎች




# የነቢዩ

-በእሳቸው ላይ የአላህ ሰላምና እዝነት ይሁን-

# ፈለጎችና እለታዊ አዝካሮች

اللغة الأمهرية
AMHARIC LANGUAGE

جميع لغات المشروع
ALL LANGUAGES